እንዲሁ ሲጓዙ ለንበቱና ደቢ በሚደርሱበት ቀን ጠዋት ባሻ ቅጣውና ከሱ ጋር የነበሩ የአንድ ጭፍራ ወታደሮች አንድ ሳርማ ሜዳ በንጥቀው ሲያልፉ ሳሉ የነጋበት አውሬ አቋርጧቸው ሲሄድ አዩ ። አውሬው እንደ አንበሳ ፣ እንደ ዝሆን ፣ እንደ አውራሪስና እንደ ተኩላ የገዘፈና በሰው ላይ አደጋ ለመጣል የሚችል ቢሆን ኖሮ እንኳ ያን ያህል ጫጫታና ሁካታ ባላስነሣ! አውሬው ግን ውሻ የሚያህልና ውሻም የሚመስል ነበር- ጸጉረ ቢጫ ። ጭራው ወርቃማ በመሆኑ የጠዋት ፀሐይ ሲያርፍበት የእሳት ነበልባል መስሎ ይታይ ነበር ።

“ቀበሮ! ቀበሮ !” እያሉ ተጯጯሁ ፣ ጦረኞቹ ።

“ቀበሮ! ቀበሮ !”እንዳያመልጣችሁ...!”

ቀበሮ ፍየልና በግ ሲያገኝ ፣ አለዚያም ሕፃን ልጅ ሲያጋጥመው ይተናኮላል እንጂ ዐዋቂን በተለይም መሣሪያ የያዘን ሰው አይደፍርም ። ጦረኞቹ ይኸንን አጥተውት አይደለም እንዲያ የተጯጯሁትና የተራኮቱት ፣ ቀበሮ አቋርጦት የሄደ ክፉ ዕድል ያጋጥመዋል የሚል ልማዳዊ እምነት ስለነበረ እንጂ ።

አቋርጧቸው የሄደው አውሬ እንዳያመልጣቸው እየሮጡ ተከተሉት ። ቀበሮውም የደረሰበት አጋጣሚ ዱብ ዕዳ ሆኖበት እግሬ አውጪኝ ሽሽቱን ቀጠለ ። “ጠበንጃዬን! ጠበንጃዬን ወዲህ በል !” እያለ ተጣራ ፣ ባሻ ቅጣው ። ተመስገን ከተቀሩት እግረኞች ጋር ቀበሮውን ተከትሎ ሲሮጥ ነበር ። “ጠበንጃዬን ! ጠበንጃዬን ወዲህ በል !”ሲል እንደ ገና ተጣራ ባሻ ቅጣው ። ተመስገን በሁለተኛ ጊዜ ሰምቶት ወደ እሱ እየሮጠ መጥቶ ጠበንጃውን ከትከሻው አንሥቶ ሰጠው ። ባሻ ቅጣው ጥርዳ በቅሎውን በተረከዙ ኰርኲር አደረገው ። ጥርዳ



ተጕዞ የማይጠግብ ፣ ሄዶ የማይደክም ፣ እጥንተ ጠንካራ ወርቾ ብርቱ በቅሎ ነበር ። እጥብቆ ሲኰረኩረውና ዛቡን ነጠቅ ነጠቅ ሲያደርግበት ሥግሪያውን ትቶ ሶምሶማ ይረግጥ ጀመር ። ባሻ ቅጣው ግን አሁንም እንዲፈጥንለት ስለ ፈለገ ግራና ቀኝ ጐኑን በይበልጥ ኰረኰረው ። ጥርዷ በቅሎውም ሶምሶማውን ለቅቆ ደንገላሳ ይጋልብ ጀመር ። እንዳይሸመጥጥ ፈረስ ሆኖ አልተወለደ !

ቀበሮው ዓይኑን ጨፍኖ ምጥሚጣ አፉን ወደ ፊት፣ ጸጉራማ ጅራቱን ወደ ኋላ ቀስሮ እግሬ አውጪኝ ሽሽቱን ቀጠለ ። ባሻ ቅጣው ቀበሮውን ቀድሞ ወደ መጣበት ለመቀልበስ የነበረው ተስፋ እየመነመነ ሲሄድ ሊተኰስበት ወሰነ ። ጠበንጃውን አመቻችቶ ዒላማውን አይቶ የቃታውን ምላስ ሳበው ። ተኩሱ ብም ሲል በቅሎው ደንብሮ በድንገት ቆሞ ወርቾቹን ወደ ሰማይ ሰቅሎ መልሶ ምድር ላይ ሲጥል ባሻ ቅጣው ተሽቀንጥሮ ለመውደቅ ምንም ያህል አልቀረው ። ሆኖም የበቅሎውን ጋማና የልጓሙን ዛብ በአንድ ላይ አፈፍ አድርጎ ስለ ያዘ ከመውደቅ ዳነ ። ተኩሱ ዒላማውን ስቶ ስለ ነበረ ቀበሮው ተሽሎክልኮ እጅብ ካለ ሣር ውስጥ ገብቶ ተሠወረ ። ባሻ ቅጣውም ሊገድለው ስለወሰነ አሁንም ደንገላሳ እየጋለበ ተከተለው ።

ቀበሮው እጅብ ያለውን ሣር አልፎ ራሱን ብቅ ሲያደርግ ባሻ ቅጣው አየውና ጠበንጃውን እንደገና አስተካክሎ ይዞ ሁለተኛ ተኩስ አሰማ ። ጥይቱ በዚህ ጊዜ ዒላማውን በትክክል መታ ። ቀበሮው ማጅራቱን ስለተመታ ምድር ዞረበት ። ተቀስሮ የነበረው ወርቃማ ጅራቱ ቀድሞ መሬት ነካ ። የተቀረ ሰውነቱ ጭራውን ተከትሎ ወደ መሬት ወረደ ። በመጨረሻም የተመታ

ጭንቅላቱ መሬት ላይ ዐረፈ ። ለአጭር ጊዜ እግርና ወርቾቹ ተወራጩና መላ አካሉ ጸጥ አለ ።

"ነጃሳ!" ሲል ተራገመ ባሻ ቅጣው ። በቅሎውም እንደሱ "ነጃሳ!" ለማለት እንደ ፈለገ ሁሉ በአፉም በአፍንጫውም "እፍ ! እፍ !"ይል ገባ ። እግረኞችም ጦረኞች ከቦታው ደርሰው የሞተውን ቀበሮ ከብበው ቆመው "ነጃሳ ! ነጃሳ !" እያሉ ይራገሙ ጀመር ። ልማዳዊ እምነት... !

፯

ጦረኞቹ ወደ ማታ ጊዜ ደሴ ከተማ ገቡ ። ከተማ ተባለ እንጂ በ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ደሴ ከገጠር መንደር እጅግም የተለየ አልነበረም ። ከዓመት ዓመት የማያድግ የማይሰፋ ፣ የማይሻሻል ፣ የሣር ቤቶች ብቻ የሚታዩበት በጉብታዎችና በኮረብታዎች ላይ የተመሸገ ወጣ ገባ የሆነ አነስተኛ የገጠር ከተማ ነበር ።

ጦረኞቹ በከተማው ውስጥ አመቺ ሥፍራ መርጠው ድንኳናቸውን ተካከሉና ለእራት መዘገጃጀት ጀመሩ ። መሰንበቻውን ሲጓዙ ስለ ደከሙና ምግባቸውም እንደ ጭኮ ፣ በሶና ቋንጣ የመሳሰለ ደረቅ ምግብ ስለ ነበረ ፣ የጦር ሚኒስትሩ ራስ ሙሉ ጌታ ሠራዊቱን ለማስደሰት ስለፈለጉ በሺህ የሚቈጠር የእርድ ከብት ለየአለቃውና ጭፍራው አከፋፍለው ሰጡ ።



ባሻ ቅጣውና ጭፍሮቹ የተሰጣቸውን ድልብ በሬ አርደው ገፈፈው ብልት አውጥተው ሲጨርሱ እጃቸውን ተጣጥበው ከአንድ ሰፊ የድንኳን አዳራሽ ውስጥ ገቡ ። አዳራሹ ከላይ በብረት ዘንጎች በተንጠለጠሉ ፋኖሶች ወገግ ብሎ በርቷል ። መቀመጫ ስለሌለ አንዳንዶቹ ዘማቾች እግራቸውን አጣምረው መሬት ላይ ቁጭ አሉ ። አንዳንዶቹ ግንድ መሳይ ፈላልገው እዚያ ላይ ተቀመጡ ። ባሻ ቅጣው ግን በኮርቻው ላይ የነበሩትን ግላሶች አውልቆና ሸብልሎ ምቹ መቀመጫ አብጅቶ ተቀመጠ ።

ከጦረኞቹ የተውጣጡ አሳላፊዎች የተጣጠፈ እንጀራ ፣ ሙዳ ሥጋ ፣ ቢላዋ ፣ ኩባያ ሚጥሚጣ ፣ አዋዜ እና ለግብዣው አስፈላጊ የሆነ ሌላ ሌላውንም እያመጡ ያድሉ ጀመር ።

ባሻ ቅጣው እንጀራውን ንቆ ትቶት አንዳች የሚያህል ሙዳ ሥጋ አንሥቶ ተጠየቅ ይለው ጀመር ። አዲስ ጩቤ እያለው ለቢላዋ አልተቸገረም ። እፍ የሚሞላ ያህል ከጉማጁ እየቆረጠ በአዋዜ እያረመደ አሁንም ተጠየቅ ይለው ገባ ። ቁርጥ መብላት የሚያውቅ ሰው አበላሉ ደስ ይላል ። ባሻ ቅጣው በሙያው ተወዳዳሪ አልነበረውምና አሁንም አሁንም እፍ የሚሞላ ያህል እየቆረጠ በአዋዜ እያረመደ መጋበዙን ቀጠለ ። አዋዜው እንደ መልኩ ጣዕሙም ደስ የሚል ቢሆንም እንደ ሚጥሚጣ አይፋጅም ነበርና ባሻ ቅጣው ኮስታራነቱን ለማሳየት እንደ ፈለገ ሁሉ አዋዜውን ትቶ ብር ንዶውን በሚጥሚጣ እያረመደ መብላቱን ቀጠለ ።

ተጐማምዶ የታደለው ሙዳ ሥጋ ሲያልቅ አሳላፊዎቹ ሙሉ ብልት የወሳንሳ ተሸክመው ከተጋባዦቹ ፊት ቀርበው ያስቆርጡ ጀመር ። ባሻ ቅጣው አንዳች

የሚያህለውን ጉማጅ አጠናቅቆት ስለ ነበረ ተመስገንና አረሩ የወሳንሳ የተሸከሙትን ታላቅ ከፊቱ ሲያቀርቡለት በዓይኑ አማትሮ በጩቤው ጫፍ በስላች ወግቶ አዟዙሮ ከተመለከተ በኋላ ሌላ ጉማጅ ሥጋ ቆርጦ አንሣለት ። ሙሉ በቅቶት ስለ ነበረ የቆረጠው ጉማጅ ቀይ ብርንዶ ነበር ። እንደ በፊቱ አፍ የሚሞላ ያህል እየቆረጠ ሚጥሚጣ እያላሰ አፉ ውስጥ ወርውሮ ሁለት ሦስት ጊዜ በጥርሱ ወጋ ወጋ እያደረገ ወደ ጉሮሮው ይሰደው ጀመር ።

የጊዜው ሰው ረዳቶቹን አይረሳም ነበርና ባሻ ቅጣውም ተመስገንንና አረሩን በየተራ በዓይን ጥቅሻ እየጠራ ከፊቱ ከነበረው ማለፊያ ሥጋ ደጋግሞ ያጉርሳቸው ነበር ።

ግብግቡ ቀጠለ ። ባሻ ቅጣውም በልቶ ሲጨርስ ከፊቱ የነበረውን ትልቅ ኩባያ አንሥቶ ጠጁን ጉሮሮው ውስጥ አንቆረቆረው ። በመጠጡም በኩል ተመስገንንና አረሩን የሚገባቸውን አልነፈጋቸውም ።

ባሻ ቅጣው በልቶ ጠግቶ ሲጨርስ ዙርያውን ይቃኝ ጀመር ። ግብግቡ ገና ከፍጻሜ አልደረሰም ነበር ። በአጠገቡ የተቀመጠውና ሸዋርካብሽ የተጠመቀች ዕለት ጠበል ጠዲቅ ለመቅመስ ከመጡት ጓደኞቹ አንዱ የነበረው በጋሻው ገና መጀመሪያ ያነሣውን ሥጋ አላገባደደም ነበር ።

“ቁርጥ መብላት አታውቅበትም ፣ ቀውሌ” አለው ባሻ ቅጣው ። በጋሻው መለል ብሎ የወጣ በጣም ረጅም ሰው ከመሆኑ የተነሣ ጓደኞቹ ሁሉ ቀውሌ ብለው ይጠሩት ነበር ።



“አብዝተህ አታኝክ” አለው ባሻ ቅጣው ፣ ቀጠል አድርጎ ፣ “አለዚያ አይበላልህም”

“ሳላኝክ ውጬ እንድታነቅልህ ነው ፣ ባሻ ?”

“ወጋ ወጋ አድርገህ መዋጥ እንጂ…ቁርጥ መብላት ፈጽሞ አታውቅበትም !”

“ሆሆ! እኔስ ሳላኝክ ውጬ ለመታነቅ አልፈልግም ባሻ !”

“በል እሺ ተወው ። እንደ ሕፃን ልጅ ማፍተልተሉን ከመረጥህ እኔ ምን ቸገረኝ !”

“ጀሬ አምራ መሰልኩህ እንዴ ፣ ባሻ ? ጀሬ አምራ ብቻ ነው ሳያኝክ የሚውጥ ።”

“እንኳን ማኘክ አታመነዥገውም ከፈለግህ ?”

“እንደ ከብት ?”

“እንግዲያ ምን መልስ ልስጥህ ፣ ቀውሌ !” አለና መሣቅ ጀመረ ። በአካባቢው የነበሩትም በጋሻው ራሱ ጭምር ይሥቁ ጀመር ።

“ዛሬ ጠዋት ቀበሮውን መግደልህን ግን አድንቄ ልሃለሁ ፣ ባሻ” አለው በጋሻው ። ቀጠል አድርጎ ፣ “እንዲያ አቋርጠን ሄዶ ቢሆን ኖሮ…”

“እስካሁን ድረስ ክፉ ወሬ ሳንሰማ የቀረነው ለዚህ ሳይሆን ይቀር ብለህ !”

ቅስማቸው እንዳይሰበር በምስጢር ተያዘ እንጂ አለቆቻቸው የሰሙት ክፉ ወሬስ ነበር ። በራስ ሙሉ ጌታ የበላይ አዛዥነት የሚመራው መሐል ጦር ወደ ደሴ ይገሰግስ በነበረበት ወቅት ጂኔራል ደቦኖ ያድዋ

ይዞታውን አጠናክሮ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ገፍቶ በመምጣት አዲግራትን ፣ አክሱምንና ፣ መቀሌን በየተራ በቦምብ ደብድቦ ይዟቸው ነበር ። እነዚህን ከተሞች በያዘበት ወቅት ተከላካይ ጦር እጅግም አላጋጠመውም ። እንዲያውም ይባስ ብሎ በሰላም ጊዜ አገረ ገዥዎች፣ ከወረራው ወዲህ የጦር አዝማቾች ከነበሩት መሐከል አንደኛው ለጠላት እጁን መስጠቱ ተሰማ ።

ይህ የፊውዳል ገዥ በመሐል መንግሥት ላይ ቁርሾ ነበረው ። አባቱ የመላ ትግራይ ገዥ ሆነው ከኖሩ በኋላ እሳቸው ሲያርፉ በእሳቸው እግር ተተክቶ መላውን ትግራይ ለመግዛት ምኞት ነበረው ። ይሁን እንጂ ይህ ባላባት የሥራ ልምድ ስላልነበረውና ችሎታውም የተረጋገጠ ስላልነበረ መላ ትግራይን ሳይሆን ምሥራቅ ትግራይን ብቻ እንዲገዛ ተሹሞ ነበር ። እሱ ግን መላ የአባቴን አገር እንዳልገዛ ተከለከልሁ ፣ ተበደልሁ በማለት በመሐል መንግሥት ላይ ቅሬታ አድሮበት ነበር ።

የኢጣሊያ ጦር መቀሌን መደብደብ በጀመረበት ወቅት እንደ ታዘዘው አደጋ ጥሎ በመሸሸ ፈንታ ጣሊያኖች ካሸነፉ የመላው ትግራይ ገዥ ያደርጉኛል ብሎ በማመንና በጊዜው በነበረውም የሥልጣን ሽሚያ ሰበብ በሺህ የሚቈጠሩ ተዋጊዎችን እንደያዘ ለጣሊያን ገባ ።

የዚህ ባላባት ክህደት ጣሊያኖችን በሁለት ረገድ ጠቀማቸው ። አንደኛ ሰተት ብለው ገብተው መቀሌን ለመያዝ አስቻላቸው ። ሁለተኛ ለፕሮፓጋንዳ አመቺ ሁኔታ ፈጠረላቸው ። በዚህ የተነሣ የኢትዮጵያ ባላባቶች ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ለማሠልጠን ያላትን ተልዕኮ ፈቅደው ተቀብለዋል የሚል ወሬ በመላው ዓለም ይነዙ ጀመር ።





የቤኒቶ ሙሶሎኒ ስም በመላው ኢጣሊያ ገነነ ። በሮማ ፣ በፍሎሬንስ በቬኒስና ዝና ባተረፉት በሌሎችም የኢጣሊያ ከተሞች ውስጥ ዱቼ ! ዱቼ ! ዱቼ ! የሚል ጩኸት በረከተ ። ቤኒቶ ሙሶሎኒ የኢጣሊያን ስም ለማደስ ከጥንት ሮማውያን ታሪክ ጋር የሚወዳደር አዲስ ታሪክ ለመሥራት የተነሣ ሕልው ቄሣር ተሰኘ። እሱም አመነበት ። ተኩራራበት ።

ሙሶሎኒን እንደ ጣዖት የሚያመልኩት የፋሺስት ፓርቲ አባሎች ብቻ ቢሆኑም ፣ ፋሺስት ያልሆኑትም የኢጣሊያ ዜጎች የፋሺስት መንግሥት ባስገኘው ድል በልባቸው ደስ ሳይላቸው አልቀሩም ። አገራቸው በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. አድዋ ላይ በደረሰባት ውርደት ምክንያት አንገታቸውን ደፍተው ይኖሩ የነበሩት የጣሊያን መሳፍንትና መኳንንት ፋሺሽቶች አድዋን በመያዛቸው አንገታቸውን ቀና ቀና ማድረግ ጀመሩ ። የኢጣሊያ ከበርቴዎች በሚሊዮን የሚቈጠር ካፒታላቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ በንግድ ሥራ አውለው ፈጣን ትርፍ ለመሰብሰብ አሰፈሰፉ ። በየመንገዱ ሲንከራተቱ ይኖሩ የነበሩ የጣሊያን ሥራ ፈቶች ወደ አዲሱ ቅኝ ግዛታቸው ሄደው ሥራ የማግኘት ተስፋቸው እየበረታ ሄደ ። በአጠቃላይ የትግራይ ክፍለ ሀገር በጣሊያን እጅ መውደቅ በሕዝቡ አእምሮ ያልታሰበ ሕልም ፈጠረ ።

ይህ ሁሉ ሕልምና ተስፋ ውጊያው እንዲፋጠን ምክንያት ሆነ ። ቤኒቶ ሙሶሎኒም መላ ኢትዮጵያን ለመያዝ ተቻኰለ ! በሕልሙም በውኑም የኢትዮጵያ ለም መሬት ፣ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብት—የቡና ቡና ፣ የሐረር

ሠንጋ ፣ የሲዳሞ ወርቅ በዓይነ ሕሊናው ይታዩት ነበርና ። በሌላም በኩል ውጊያው ቢራዘም የአውሮጳ ኃያላን መንግሥታት በተለይም ፣ የዓለም መንግሥታት ማኅበር በኢትዮጵያና በጣሊያን መሐከል በነበረው ሁኔታ ጣልቃ ይገቡብኛል የሚል ፍራቻ ነበረበት ። ስለዚህ ጀኔራል ደቦኖን አስጠርቶ "የኢጣሊያ ማርሻል" የሚል የማዕርግ ስም ሰጥቶ ከሥራው አሰናበተውና በጭካኔው ወደር የሌለውን ማርሻል ባዶሊዮን የበላይ ጦር አዛዥ አድርጎ ሹሞ ጦርነቱን እንዲያፋጥን ላከው ።



# ክፍል ሦስት

## ፈተና

ጀኔራል ደቦኖ ሄዶ ማርሻል ባዶሊዮ ከተተካ በኋላ በርከት ያሉ ግልጽ ውጊያዎች በርከት ባሉ ሥፍራዎች ተካሄዱ ። በሰሜን ግምባር በቀይሃታ...በእዲ አቢ...በተከዜ ወንዝ አካባቢና በሌሎችም ሥፍራዎች.. በደቡብ ምሥራቅ ግምባር በቆራሄ...በዶሎ...በነገሌና በሌሎችም ሥፍራዎች ።

ከነዚህ ሁሉ ይልቅ አስከፊ የነበረው ግን የአምባራዶም ውጊያ ነበር ።

በራስ ሙሉጌታ የበላይ አዛዥነት ይመራ የነበረው የመሐል ጦር ቀድሞ ቦታ ለመያዝ ወደዚያው አመራ እየፎከረ...እየሸለለ...

"ወንድ ልጅ ተወልዶ ካልሆነ እንዳባቱ
ሰጡት አመልማሎ ይፍተል እንደናቱ

ዘራፍ ! ዘራፍ ! ዘራፍ !" እያለ እያቅራራ... እየሸለለ...

እምባራዶም በሰሜን ኢትዮጵያ እንደሚገኙት ሌሎች ተራሮች ሁሉ ሰማይ ጠቀስ ፣ ጉም ለበስ ነበር—

ግራና ቀኙ ገደል ፥ በስተሰሜንም በኩል ገደል ሆኖ በስ ተደቡብ ብቻ ከሜዳ የሚያደርስ መንገድ ያለው ። ርዝ መቱ አንድ ሰዓት ተኩል ያህል ፥ ጐኑ ግማሽ ሰዓት ያህል የሚያስኬድ ፥ በጣም ሰፊና በውስጡም ለመጠለያ የሚሆኑ ዋሻዎች ያሉበት ጋራ ነበር ።

"ይምጣ ሶልዳቶ ! " አሉ ራስ ሙሉጌታ ጦራቸ ውን አስከትለው ከሜዳ ደርሰው የቦታውን አመቺነት በዓይናቸው ካዩ በኋላ ። "ይምጣ ! ማንነታችንን እናሳ የዋለን !" ሲሉ ፎከሩ ።

ማርሻል ባዶሊዮ በበኩሉ የኢትዮጵያን ጦር ከአ ምባራዶም አስወጥቶ ተራራውን መያዝ በጣም አስቸ ጋሪ እንደሚሆንበት ቀደም ብሎ ያውቅ ነበር ። ይሁን እንጂ ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆን ፥ ያለቀው ወታደር ቢያልቅ ፥ የጠፋው መሣሪያ ቢጠፋ ፥ ተራራውን አስለ ቅቆ ለመያዝ ቆርጦ ነበር ፤ የአምባራዶም መያዝ የመ ላውን ጦርነት መልክ እንደሚለውጠው ያውቅ ነበርና።

በሰው ብዛት የማርሻል ባዶሊዮ ጦርና የራስ ሙሉጌታ ጦር እቻ ለእቻ ነበሩ — በእያንዳንዱ ወገን ሰባ ሺህ ወታደር ። ሆኖም የጣሊያን ጦር በቅጡ የሠ ለጠነ ፥ የታጠቀ ፥ የለበሰ ፥ የጠገበ ዘመናዊ ጦር ሆኖ ሳለ፥ የኢትዮጵያ ጦር አብዛኛው በዘመናዊ ሥልት ያልሠለ ጠነ ፥ ያልታጠቀ ፥ ያለበሰና ያልጠገበ ጦር ነበር ።

ለአምባራዶም ውጊያ ብቻ የጠላት ጦር ሁለት መቶ ሰማንያ መድፍ ነበረው ። የኢትዮጵያ ጦር ግን አሥር ብቻ ።

ለዚሁ ውጊያ የጠላት ጦር መቶ ሰባ የጦር አውሮ ፕላኖች አዘጋጅቶ ነበር ። በኢትዮጵያ በኩል ግን አንድ እንኳ ቦምብ ጣይ ወይም ተዋጊ አውሮፕላን አልነበረም ።



የጠላት ጦር በሺህ የሚቈጠሩ የመጓጓዣ ካሚዮ ኖች ነበሩት ። በኢትዮጵያ በኩል የነበረው መጓጓዣ ግን ዘጠና በመቶ የሚሆነው የጋማ ከብት ነበር ።

ባጭሩ ለአምባራዶም ውጊያ በኢጣሊያና በኢት ዮጵያ መሐከል የነበረው የጦር አሰላለፍ ከላይ ያለውን ይመስል ነበር ።

ማርሻል ባዶሊዮ ጦሩን ከፍሎ በሁለት አቅጣጫ ሰደደ ። አንደኛው ክፍል በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ፥ ሁለተኛው ክፍል በደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ ተጕዞ ተራራውን ግራና ቀኝ እንዲከብ ፤ የሁለቱም ግምባር ጦሮች ከተራራው በስተደቡብ ያለውን መውጫ መግ ቢያ በር እንዲይዙና ከመቶ ሰባ የማያንሱት ተዋጊና ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በአየር ላይ ሆነው ውጊያ ውን እንዲከፍቱ አዘዞ ነበር ። ማርሻል ባዶሊዮ የጦር መላ የሚቸግረው ሰው አልነበረም!

፳

የጣሊያን ምድር ጦር አምባራዶምን ከብቦ ከያዘ በኋላ የአየር ኃይሉ ጦርነቱን ከፈተ ። ከ፲፪ እስከ ፳ የሚደርሱ የጠላት አውሮፕላኖች በሰልፍ እየበረሩ ከአምባ ራዶም ተራራ ላይ ባለው አየር ማንዣበብ ጀመሩ ። አው ሮፕላኖቹ ተራራውን እየዞሩ ዒላማቸውን እየመረጡ የቦ ምብ ናዳ እያወረዱ ማረፊያቸው ወደ ነበረው ወደ መቀሌ ተመልሰው ሲበሩ በምትካቸው እንደገና ከ፲፪ እስከ ፳

የሚሆኑ ሌሎች የጦር አውሮፕላኖች በሠልፍ እየበረሩ መጥተው እነሱም በተራቸው ጋራውን ዞረው ዒላማቸ ውን መርጠው የቦምብ ናዳ ጥለው ተመልሰው ወደ ግረሬያ ማቢያቸው ይበርሩ ገቡ ።

የቦምቡ ጩኸት ጆሮን ያደነቁራል ። ተራራው ከሥሩ የሚነቃነቅ ይመስላል ። የእሳት ነበልባል እዚ ህም እዚያም ቡልቅ...ቡልቅ...ይላል ። በአካባቢው ያሉ ወፎች ጎጆአቸውን ለቅቀው ይሸሻሉ ። የዱር እራዊ ትም ከጉሬአቸው ወጥተው ተራራውን ለቅቀው እግሬ አውጪኝ ይላሉ ።

የኢትዮጵያ ጦረኞች ጆሮአቸውን በጣታቸው ደፍ ነው ባሉበት አድብተው ይጠብቃሉ ።

"ምን ማድረግ ይሻላል ?" አለ ቢጋሻው ።

"ምን ይደረጋል ! ዝም ብሉ መጠበቅ ነው እንጂ..."

"የፈሪ ውጊያ !" ብሉ ጆሮውን ደፍኖ ዝም ብሎ ተቀመጠ ቢጋሻው ።

የኢትዮጵያ ጦረኞች ይህ ዓይነት ውጊያ ይደርስ ብናል ብለው ፍጹም አላሰቡም ነበር ። የጥንት ርግው ያን ጀግኖች ነበሩ ፤ ጠላታቸውን ፊት ለፊት ይገጥሙ ነበርና ። በ፲፰፻፹፰ ዓ. ም. እንኳ የጄኔራል ባራቲዬሪ ወታ ደሮች የኢትዮጵያን ጦር ፊት ለፊት ተጋፈጡት እንጂ የድብብቆሽ ውጊያ አልተዋጉም ። የሙሶሊኒ ወታደሮች በየካቲት ወር ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ጭካኔያዊ ጦርነት ግን በዘ መን አመጣሽ መሣሪያ አማካይነት ተመሳሳይ የሆነ መከላከያ መሣሪያ በሌላቸው የኢትዮጵያ ጦረኞች ላይ የቦምብ ናዳ ማውረድንና የመርዝ ጢስ ማዝነብን የዕ ለት ተዕለት ተግባራቸው አድርገው ያዙት ።



አሁንም እንደገና ከ፲፪ እስከ ፳ የሚደርሱ የጠ ላት የቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች በአዲስ ጉልበት እየ መጡ የቦምብ ናዳ ማውረዳቸውን ፤ እነዚህ ተልእኳቸ ውን ፈጽመው ሲመለሱ እንደገና የአንበጣ መንጋ የመ ሰሉ ሌሎች የጦር አውሮፕላኖች በሠልፍ መጥተው የኢትዮጵያን ጦር ማጥቃታቸውን ቀጠሉ ።

የአውሮፕላኖቹ ሩምሩምታ እየባሰ ሄደ ። ድምፁ ብቻ ናላ የሚያዞርና ሐሞት የሚያፈስ ሆነ ። ቦምብ ይፈነዳል ። ጭሚ አለቶች እየተደረመሱ ይወድቃሉ ። የድንጋይ ስብርባሪ አዲስ መጣሪያ እየሆነ ግራና ቀኙ ፈትና ኋላ እየተወነጨፈ በወገን ጦር ላይ አደጋ ይጥላል ። አንድ እንኳ ጥይት ሳይተኩሱ የሚያልቁ የኢትዮጵያ ጦረኞች ቍጥር ጥቂት አልነበረም ።

"ይህ የፈሪ ውጊያ አብቅቶ የጀግና ውጊያ መቼ ይጀመር ይሆን ?" አለ አደላ ፤ የአነ ባሻ ቅጣው ሌላው ባልደረባ ።

"ማን ያውቃል!" ሲል መለሰለት ባሻ ቅጣው ።

የአየሩ ውጊያ ጋብ በማለት ፋታ እየባሰ ሄደ ። አውሮፕላኖቹ ይመጣሉ ። ጋራውን ይዞራሉ ። ዒላማ ቸውን ይመርጣሉ ። የቦምብ ናዳ ያወርዳሉ ።

"እነዚህ ፋሺስቶች ጋራውን ለመደርመስ ነው ዕቅ ዳቸው?" አለ ቢጋሻው ።

"ሳይሆን ይቀር ብለህ !" አለው ባሻ ቅጣው ።

የጣሊያን አውሮፕላኖች መደዳውን ሁለት ቀን እንዲሁ እየተመላለሱ የቦምብ ናዳ ማውረዳቸውን ቀጠሉ። በሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያ ጦረኞች ሕይወታቸውን

እጡ ። በሕይወት ያሉትም ርስ በርሳቸው መጠያየቃቸውን ቀጠሉ ።

"እኒህ አውሮጵላኖች ማለቂያ የላቸውም እንዴ ?"

"ማለቂያ ቢኖራቸውማ እስካሁን ባለቁ ! "

"ጣሊያኖች ምን ያህል ቦምብ ይዘው ቢመጡ ነው ይህንን ያህል ጊዜ ሲያፈነዱ የማያልቅባቸው ? "

"ማን ያውቃል ! ማን ያውቃል ! "

"የፈሪ ውጊያ ! "

ቦምብ በፈነዳ ቍጥር የኢትዮጵያ ጦር እየተቀነሰ ፣ እያነሰ ይሄድ ነበር ። የቦምብ ፍንጣሪ ወይም ፍንጣሪው ያበረረው የድንጋይ ስብርባሪ አናቱን ሲፈነክተው ፣ ልቡን ሲመታው ጦረኛው ፣ "ወይኔ...አበላሸኝ !" እያለ ጭጭ ይላል ። ከቆሰለም ከወደቀበት ሥፍራ ሆኖ "እህህ!" እያለ ያቃስታል ።

የጣሊያን ምድር ጦር በአየር ኃይሉ አጥቂነት የልብ ልብ ስለ ተሰማው ጋራውን መከበቡና መውጫ መግቢያ በር መያዙ አንሶት የኢትዮጵያን ጦር ይበልጥ ለማስጨነቅ የከበባ ቀለበቱን እያጠበበ ይበልጥ እየተጠጋ ሄደ ። የኢትዮጵያ ጦር በእርግጥም በወጥመድ የተያዘ አንበሳ ሆነ ።



## ፫

የኢትዮጵያ መሐል ጦር ለሁለት ቀናት ሙሉ በቦምብ ሲደበደብ እንደ ቆየና በጠላት ጦር ተከብቦ መፈናፈኛ ማጣቱን በክብር ዘበኞች ታጅበው በደሴ የመሸጉት ንጉሠ ነገሥቱ ሰሙ ። በሌሎች ጦር አዝማቾች ይመሩ የነበሩት የሰሜን ክፍላተ ሀገር ጦረኞች ወደ አምባራዶም ተጠግተው የኢጣሊያንን ጦር ከበስተኋላው እንዲወጉትና የራስ ሙሉጌታን ጦር ከከበባው እንዲያስለቅቁ ትዕዛዝ ተላለፈ ። በሰሜን ግምባር ጀብዱ ሥሩ ተብለው ከሚነገርላቸው አንዱ የነበሩት ራስ እምሩ ትዕዛዙን በጊዜ ሳይሰሙ ቀሩ ። ሌላው የጦር አዛዥ ራስ ካሣም ትዕዛዙ ዘግይቶ ደረሳቸው ። ራስ ሥዩምም እንዲሁ ። የራስ ሙሉጌታ ጦር ዙሪያውን የተከበበ በመሆኑ የነበረው ምርጫ ከበባውን ሰብሮ መውጣት፣ አለዚያም ባለበት ማለቅ ብቻ ሆነ ።

ራስ ሙሉጌታ ያሉበትን አስጨናቂ ሁኔታ ከተረዱ በኋላ ጥሩምባ እንዲነፋና ጦራቸው ከየተጠለለበት ዋሻ ወጥቶ የጠላትን የምድር ጦር ፊት ለፊት እንዲገጥም ትዕዛዝ ሰጡ ። በዚህ ጊዜ የኢትዮጵያ መሐል ጦር እየተመመ ወጥቶ እንደተርብ ይናደፍ ጀመር ።

መትረየስ ይንበቀበቃል ። መድፍ ያጓራል ። ጥይት ይንጣጣል ። የኢትዮጵያ ጦረኞች በቀጣ ሲቃ ተይዘው ጠላታቸውን ፊት ለፊት ሲያገኙት እንደ ተራበ አውሬ ዘልለው ሄደው ይተናነቁታል ። ጐራዴ የሚመዘዘው፣ ጦር የሚወረውረው ፣ ጠመንጃ የሚተኰሰው ፣ የእጅ ቦምብ የሚወረውረው ፣ ሳንጃ ወድሮ ወደ ፊት የሚወረወረው... እያንዳንዱ በየፊናው የያዘውን መሣሪያ ይዞ ከጠላት

ጋር ይጋደላል ። "ተርትረው" ይላል አንዱ ። "ውጋው !" ይላል ሌላው ። "በለው... ! አትማረው... ! ጨርሰው ...!"

በሁለቱም ወገን የሚወድቀው ተዋጊ ወታደር ስፍር ቍጥር የለውም ። ግማሹ ደረቱን ይዞ ከመሬት ላይ ይነጠፋል ። ግማሹ ቆሞ ይወዛወዛል ። የቆሰለው በሚያሠቅቅና በተለያየ ሁኔታ የሥቃይ ጩኸት ያሰማል ። መሣሪያው ያስካካል ።

ድው ድው...
ጭጭ...
ሲጢጥ ሲጢጥ...
ጭጭ...
ብም ብም...
ጭጭ...
እልቂቱ ይቀጥላል ።

ባሻ ቅጣው እንደ ሌላው የወገን ጦር ሁሉ ጠመንጃውን ደግና ሲያንጣጣና የጠላትን ወታደር ሲያረግፍ ቆየ ። ከተኮሱ ብዛት የተነሣ የቃታ ምላጭ የሚስብበት ጣቱ እየዛለ ሲሄድ ተሰማው ። በዝናሩ የነበረ ጥይት አልቆ ጠበንጃው የጐረሰው አንድ ካርታ ጥይት ብቻ ቀርቶታል ። በዚህ ጊዜ በድንገት አንድ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ፋሺስት ከቅርብ ቦታ ቆሞ ጥይት ሲያንካካ ያያል። ጣሊያኑ በቁመቱም በውፍረቱም እቻው ይመስላል— በስፖርት የተገነባ ሰውነት ያለው ። ጣሊያኑ በአቅራቢያው ቆሞ የወገን ጦር ሲያረግፍ ማየቱ በባሻ ቅጣው ላይ የቍጣ ማዕበል አስነሣበት ። አድፍጦ የቆየው ውስጣዊ ኃይል ከመላ አካሉ ሲንቀሳቀስ ተሰማው ። የቀ



ሩትን አምስት ጥይቶች ላለማባከን ቆርጦ በወገቡ ሻጥ አድርጎት የነበረውን ጩቤ መዞዞ ወደ ጣልያኑ ራመድ አለ ። ጣሊያኑ ወዲያውኑ ነቃበት ። ባሻ ቅጣው ልቡን ሊወጋው ሲሰነዝር ጣልያኑ በሚያስገርም ፍጥነት ቀድሞት የባሻን እጅ በእግሩ መትቶ ጩቤውን አስጣለው። የጁዶ አዋቂ ኖሯል ! ለአንድ አፍታ ጣሊያኑና ባሻ ቅጣው ዓይን ለዓይን ተፋጠጡ ። ጥፍራቸውን አውጥተው፣ አፋቸውን ከፍተው ፣ ጥርሳቸውን አግጠው ለመናከስ እንደ ተዘጋጁ የዱር አውሬዎች ።

ባሻ ቅጣውና ጣልያኑ እንዲሁ ከተፋጠጡ በኋላ፣ ሁለቱም ወደፊት ራመድ ራመድ ብለው ክንድ ለክንድ ተያያዙ ፣ ቀጥሉም ወገብ ለወገብ—ፍቅረኞች እንደሆኑ ሁሉ ...

ባሻ ቅጣው ባህላዊ ትግል ያውቅ ነበር ። የጣሊያኑን ወገብ ጥርቅም አድርጎ እንደያዘ ቀኝ እግሩን ሰድዶ በጣሊያኑ ግራ እግር ላይ ጠምጥሞ ወደፊት ነጠቅ ሲያደርገው ጣልያኑ ከመሬት ወርዶ ተዘረገፈ ። ባሻ ቅጣውም በላዩ ላይ ወደቀበት ። ከሥር የነበረው ጣልያን ያለ የሌለ ኃይሉን ሰብስቦ ባሻ ቅጣውን እንደገና ከሥር ፣ ራሱን ከላይ አደረገ ። እንዲሁ ከላይ የነበረው ከታች ፣ ከታች የነበረው ከላይ እየሆኑ ምድር ለምድር እየተንከባለሉ ይዳቆሱ ገቡ ። የሁለቱም ፊት አቧራ ለበሰ ። የሁለቱም ፊት ደምቷል ።

በመጨረሻም ባሻ ቅጣው እንደ ብረት በጠነከሩ እጆቹ የጣልያኑን ጉሮሮ አንቆ ይዞ ከመሬት ጋር ሰፋው ። ጣልያኑ ግን ዋዛ ሰው አልነበረም ። ከታች ሆኖ ባሻ ቅጣውን በእግሩ ወደ ላይ መትቶ ሲያስፈንጥረው፣ ወደ አየር ተወርውሮ በጣሊያኑ ራስጌ በኩል ወደቀ ። ወዲያውኑ

መሬት ላይ ነጥሮ እንደሚነሣ ኳስ ነጥሮ ተነሣና እጁን መሬት ወድቆ ወደ ነበረ ጨቤው ሰደደ ። ጨቤውን እንሥቶ ወደ ጣሊያኑ ዘሎ ሄዶ በጀርባው ላይ ቀበቀበበት። የጩቤው ስለት አጥንት ነክቶ ሲጢጥ አለ ። የስለቱ ሲጥሲጥታ ግን በአካባቢያቸው ይወድቅ በነበረ ቦምብ ፍንዳታ ተዋጠ ። ባሻ ቅጣው ጩቤውን ስቦ እንደገና እጁን ወደ ጣሊያኑ ሲሰድ ስለቱ አጥንት ከሌለው ሥጋ ውስጥ ሰተት ብሎ ገባ ። ጣሊያኑ እንደታረደ በሬ ያጓራ ጀመር—የተወጋ ሆዱን በእጁ ይዞ ። ትኩስ ደሙም ቡልቅ ቡልቅ እያለ ወጥቶ ዩኒፎርሙን አለበሰው ። ባሻ ቅጣው ጩቤውን እንደገና መዝዞ በጠላቱ አንገት ሲሸጠው ፣ ጣሊያኑ እግርና እጁን መሬት ላይ እንጥፎ ጭጭ ፣ ጸጥ አለ ።

ባሻ ቅጣው የጠላቱን ከባድ ጠበንጃና አንድ ዝናር ጥይት ማርኮ ራመድ ሲል ተዞስ ሰማ ። ጥይቱ በእጁ ጡንቻ ውስጥ ሰርጎ ሲገባ የሚያንቀጠቅጥ ቅዝቃዜ ተሰማው…

፩

በባሕር ላይ የሚጓዝ መርከብ ውኃውን ግራና ቀኝ እየከፈለ እንደሚያልፍ ሁሉ የራስ ሙሉጌታም ጦር ከበባውን ሰብሮ የጠላትን ጦር መሐል ለመሐል ሰንጥቆ ግራና ቀኝ እያገለለ ወደ ደቡብ አቅጣጫ ማፈግፈግ ጀመረ ። የጠላት መሣሪያ በሰማይም በምድርም አሁንም ይንጐደጐዳል ። የወገን ጦር ጠላት ሲጠጋው ዞሮ እየተኩሰ፣ ሲርቀው በጉዞው እያተኰረ ፣ እየተበታተነ ፣ መልሶ እየ ተሰበሰበ እንደ ገና እየተዘራዘረ ማፈግፈጉን ቀጠለ—ወደ ደቡብ አቅጣጫ ።

ከአምባራዶም በስተደቡብ ያለው አገር ዛፍና ከለላ የሌለው ጭው ያለ ሜዳ በመሆኑ ወደ ኋላ በማፈግፈግ ላይ ያለው የወገን ጦር ከመቼውም የበለጠ ለጠላት አየር ኃይል ተጋለጠ ። ከለላ እስኪያገኝ ድረስ ፈጥኖ ከመሸሽ በስተቀር ፣ ሌላ አማራጭ አልነበረውም ። የጠላት አውሮፕላን አብራሪዎችም ይህንን በመገንዘብ ጦሩን እያሳደዱ ማጥቃታቸውን ቀጠሉ ።

እነ ባሻ ቅጣው በሩቅ ጫካ ታያቸውና ወደዚያ በመጣደፍ ላይ ፣ ሳሉ ፌንጣ የመሰለ አንድ የጠላት አውሮፕላን ዝቅ ብሎ ወርዶ ቦምብ ለመጣል ሲዘገጃጅ ወደ ላይ ተኰሱበት ። በተራ ጠበንጃ የተተኰሰ ተራ ጥይት የመምዘግዘጊያ ርቀቱ አጭር ስለሆነ አውሮፕላኑን አላገኘውም። አውሮፕላን አብራሪውም ቦምቡን ወደታች ለቅቆ የአውሮፕላኑን አፍንጫ ወደ ላይ በመሰቀል በረራውን ቀጠለ ። ቦምቡ ዒላማውን አልመታም ። እነባሻ ቅጣውን አልፎ ሄዶ ፈነዳ ። አረሩ ግን አህዮቹን እየነዳ ፊት ፊት ቀድሞ ይሮጥ ስለነበረ ከአደጋው ለማምለጥ አልቻለም ። ቦምቡ በእግሩ ሥር ሲፈነዳ ወደ ሰማይ ጉኖ ተመልሶ ምድር ላይ ተፈጠፈጠ—አንድ እግሩ ተጐርዶ ወዲህ ሌላው እግሩ ተጐርዶ ወዲያ ። አህዮቹም እስከነጭነታቸው ብትንትናቸው ወጣ ። ይህ ሁሉ ሲሆን ባሻ ቅጣው በጋሻው አደላና ተመስገን በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ ነበሩ—የቀጣ ሲቃ እየተናነቃቸው አየሩን ለመዒጠጥ እየቃጣቸው ።

ባሻ ቅጣው ዋርዳ በቅሎው ላይ ነበር—ከገደለው ፈረንጅ የማረከውን አዲስና ከባድ ጠበንጃ በእጁ ይዞ ።

ተመስገን እርጌውን ምንሽር በትከሻው አጋድሞ የበቅሎውን ደጋሬይ በግራ እጁ ይዞ ከበቅሎው ጋር እኩል ይሠግር ነበር። እስካሁን ድረስ አደጋ ያላገኘው አዲላ እና ወጊያው ተፋፍሞ በነበረበት ወቅት ጃርው ቆስሎ የነበረው ቢጋሻው ከእነ ባሻ ቅጣው ፈንጠር ብለው ሲጓዙ ነበሩ—ግራና ቀኝ ወደ ሰማይም እየተመለከቱ።

ተጉዘው ተጉዘው ሜዳውን ጨርሰው ከደን አፋፍ ሲደርሱ ትንሽ እፎይታ ተሰማቸው—ከአሁን ወዲያ እስከዚህም የሚያሠጋቸው ነገር አልነበረምና። የኢጣሊያ አውሮፕላን አብራሪዎች ፈንጂ በከንቱ ለማባከን ካልፈለጉ በስተቀር ጥቅጥቅ ካለ ጫካ ውስጥ በምብ ቢጥሉ በአጋጣሚ አውሬ ይገድሉ እንደሆነ እንጂ ኢላማ አይተው በወገን ጦር ላይ አደጋ ለማድረስ ፈጽሞ ከማ ይቻላቸው ሁኔታ ደርሰው ነበር።

"መሣሪያ ተኩሰህ ታውቃለህ?" ሲል ባሻ ቅጣው ተመስገንን ጠየቀው፣ ከበቅሎው ወርዶ ጫካው ውስጥ በእግር ሲጓዙ ሳሉ።

"ተኩሻለሁ፣ ባሻዬ።"

"የት? መቼ?"

"ዱሮ ባላገር እኖር በነበረ ዘመን።"

"ባላገር ኖረህ ታውቃለህ?"

"አዎን፣ ባሻዬ።"

"ከዱሮም ጀምሮ የከተማ ልጅ ትመስለኝ ነበር፣ ተመስገን" አለው ባሻ ቅጣው። "እና፣ መሣሪያ ተኩሰህ ታውቃለህ?" ሲል በድጋሚ ጠየቀው።

"አዎን፣ ባሻዬ።"



"ማን ሰጥቶህ?"

"የቀድሞ ጌታዬ ናቸው፣ ባሻዬ።"

"ምን ልትሠራበት?"

"አውሬ ላድንበት…በአካባቢያችን ብዙ የዱር አውሬዎች ነበሩ፣ ባሻዬ። በአዝመራ ወቅት መንጋ ሆነው እየመጡ እህል ያበላሹ ነበር። እንደዚህ የከርከሮ መንጋ ከጫካ ወጥቶ በተከመረ እህል ላይ እየተንከባለለ ሲያረግፈው አንድ ግዳይን ጨፍኜ አነጣጥሬ ተኩሼ ነድዬ ጣልኩት" አለ በኩራት መንፈስ።

"እንግዲያ ቀደም ብለህ ለምን አልነገርከኝም?" ብሎ ቆጣ አለና፣ "እሱን ጠበንጃ እስከነጥይቱ ሸልሚሃለሁ። ፋሺስቶች አረፉን እንዴት እንደገደሉት በዓይንህ አይተሃል። የጓደኛህን ደም ሳትበቀል አንተም በፋሺስት እጅ ከመውደቅህ በፊት አንድ ፋሺስት ባትገድል እንዳትሞት፣ ሸልሚሃለሁ። ከአሁን ወዲያ ከእኛ እንዱ ሆነህ እንድትዋጋ?

ተመስገን ለማመን ስላልቻለ መልስ አልሰጠውም።

"ሰምተኸኛል!" አለው ባሻ ቅጣው፣ "እሱን ጠመንጃ ሸልሚሃለሁ።"

"እሺ፣ ባሻዬ። ከፈቀዱልኝ እዋጋለሁ።"

"ለመሆኑ አዲስ አበባ እንዴት አድርገህ መጣህ?"

"የቀድሞ ጌታዬ ቤት ልጅ በትዳር የቀድሞ ጌታዬ ለእሷ ሰጡኝ። ባሏ የአዲስ አበባ ሰው ስለ ነበረ እሷን ተከትዬ መጣሁ። ከዚያ በኋላም ዕድሜ ለመንግሥት ነጻነቴን አገኘሁ፣ ባሻዬ።"

ተመስገን አማርኛ ይነገር በነበረበት አካባቢ ተወልዶ ያደገ ስለ ነበረ ቋንቋው አይቸግረውም ነበር ። ስለዚህም አብዛኛዎቹ የቀድሞ አገልጋዮች ምላሳቸው ይተሳሰር እንደነበረው የሱ ምላስ አይተሳሰርም ነበር ። እንደ ማንኛውም የአማርኛ ተናጋሪ አፉን ሳይዘው አሳምሮ ይናገር ነበር ።

ባሻ ቅጣው የተመስገን ጨዋታ ስለጣመውና ሐሳቡንም ስለከፈለለት ፣ "የቀድሞ ጌታህ ምን ያህል ቢያምንህ ነው ለመሆኑ ጠበንጃ የሰጠህ !" ሲል ቀጠለ።

"ያምኑኝ ነበር ። አባቴንም ያምኑት ነበር ። በዚያ ላይ ደግሞ ታሪካችንን ያውቁ ነበር ።"

"ታሪካችንን...? "

"አዎን ፣ ባሻዬ ። ታሪካችንን ጨርሰው ያውቁ ነበር።"

ባሻ ቅጣው ግር ብሎት ተመስገንን አተኩሮ ተመለከተው ።

"ምነው ተገረሙ ፣ ባሻዬ ? "

"ታሪካችንን ማለትህ...! "

"የጥንት አባቶቻችን አገልጋዮች አልነበሩም ፣ ነጻ ሰዎች ነበሩ ማለቴ ነው ፣ ባሻዬ ። "

"እንዴት ? "

"ቅድመ አያቴ ጦረኛ ነበሩ ። በጦርነት ተማርከው አገልጋይ ሆኑ ። ከዚያ በኋላ ነው መላ ዝርያቸው አገልጋይ የሆነው ። "

"ማነው እንዲህ ብሎ የነገረህ ? "



"አባቴ ነዋ ፣ ባሻዬ ። አባቴም ከአባቱ ፣ ከኔ አያት ፣ አያቴም ከአባቱ—ከኔ ቅድመ አያት የሰሙት ነው ። "

ታሪኩ ለባሻ ቅጣው ጀር እንግዳ ቢሆንም ፈጠራ አልነበረም ። በቀድሞ ጊዜ የእርስ በርስ ጦርነት ይካሄድ በነበረበት ዘመን ፣ ተሸናፊው ወገን ተማርኮ ባርያ ይሆን ነበር ። ገንዘብ ከፍሎ አርነቱን ካላገኘ በስተቀር ባርያ ሆኖ ይኖር ነበር ። ባሮቹም እየተዋለዱ ፣ ቊጥራቸው እየተበራከተ የየቤተሰቡም ይዞታ እየጨመረ ሲሄድ ፣ የባርያ አሳዳሪዎች ከአገልጋዮቻቸው አንዳንዶቹን ለዘመድ አዝማድ በስጦታ መልክ ይሸልሟቸው ጀመር ። ቀጥሎም ባርያ መሸጥ ተጀመረ ። የባርያ ንግድ እየተስፋፋ ሲሄድም የጦር ምርኮኞችና የእነሱ ውልዶች ብቻ ሳይሆኑ ባርያ ፈንጋዮች ሌሊት ቤት ሰብረው ገብተው ቀንም ከብት ከሚውልበት ሜዳ በእረኝነት የሚያገለግሉ ሕፃናት ልጆችን አፍነው እየወሰዱ ይሸጧቸው ጀመር ። በዚህ ምክንያት የባርያ ሥርዓት ባህል ለመሆን በቅቶ ነበር—ሥርዓቱ በዐዋጅ እስከ ተከለከለበት ጊዜ ድረስ ።

"ቅድመ አያትህ ጦረኛ እንደ ነበረ አላውቅም ነበር" አለ ባሻ ቅጣው ፣ ወደ ተመስገን እያየ ። "ለማንኛውም ከአሁን ጀምሮ አንተም ጦረኛ ለመሆን ዕድል ስላገኘህ አንድ ፋሺስት ሳትገድል በፋሺስት እጅ እንዳትወድቅ" ሲል መከረው ። ተመስገንም አዲስ ሕይወት እንዳገኘ ሁሉ ልቡን በጣም ደስ ብሎት፣ "እሺ ባሻዬ፣ ዕድል ከሰጡኝ እዋጋለሁ ። ደሞም አያፍሩብኝም" አለው፣ መላ ገጽታው ወገግ ብሎ ።

## ፳

እነ ባሻ ቅጣው ገፍተው ሄደው ከማኮው መሐል ሲደርሱ ፣ የጠራ የምንጭ ውኃ አገኙ—ከከፍታው የነሆት በቀጭን መስመር ወርዶ ከጉድባ ተጠራቅሞ አለፍ ሄዶ በሌላ ቀጭን መሥመር የሚፈስና የ "ቀ" ቅርጽ ያለው ኩል የመሰለ ውኃ ። በዛፎች ጥላ ከፀሐይ ሙቀት የተከለለ በመሆኑ ቀዝቃዛ — በጣም ቀዝቃዛ— የምንጭ ውኃ ነበር ፤ ረጋ ብሎ ሲታይ ኩል የሚመስል ሲንጠለጠል ግን እንደ አዲስ ብር የሚያብረቀርቅ ። ምንጩ ውኃ መሆን ቀርቶ ወተት ወይም ብርዝ ጠላ ወይም ጠጅ ቢሆን ኖሮ እነ ባሻ ቅጣው ትሬታ ሳይሰማቸው ባልቀረ ፤ ከምንም ዓይነት መጠጥ ይልቅ የሚያስጐመጅ የጠራና የቀዘቀዘ ምንጭ ነበርና ። ጥም አቃጥሏቸው ስለ ነበረም ውኃውን በእፍኞቻቸው እያነሡ አከታትለው ተጐንብሰው በአፋቸው ይስቡት ገቡ ። ጥማቸውን ካረኩም በኋላ በፊታቸውና በአንገታቸው በራሳቸውና በደረታቸው ረጩት ፣ ይህም ሲበቃቸው ቁስላቸውን ያጣጥቡበት ጀመር ።

እነ ባሻ ቅጣው የቁስላቸው ሕመም በይበልጥ የተሰማቸው ዕረፍት ባገኙበት በአሁኑ ወቅት ነበር ። ቢጋሻው የተሸረከተ ጆሮውን ይዞ ፣ "አመመኝ... ጆሮዬን አመመኝ" አለ ። ባሻ ቅጣውም የሚቆጠቁጥ ስሜት ተሰምቶት የክንዱን ቁስል ይመለከት ጀመር ። ጥይቱ በግራ ክንዱ ጡንቻ ገብቶ አጥንት ሳይነካ በስቶ ወጥቶ ነበር ።

የውኃ ጥማቸውን እንዳረኩ ከወራጅ ውኃው አቅራቢያ ከሚገኝ መስክ ላይ ጋደም ብለው የተረፉቸውን ጥሬጥሬ ከየኪሳቸው እያወጡ ይቆረጥሙ ጀመር ። የመድፉ ድምድምታ ፣ የቦምቡ ብምብምታ ፣ የተኩሱ ጣሽ



ጣሽታ ፣ የሞተሩ ሩምሩምታ አከትሞ ስለ ነበረ በአካባቢያቸው ፍጹም ጸጥታ ሰፍኖ ነበር—አልፎ አልፎ ጆሮን ከሚዳስስ ከአእዋፍ ዝማሬ በስተቀር ።

ይህን የመሰለ እርጋታ ባለው ሥፍራ ላይ አረፍ ብለው ሳሉ ፣ ቢጋሻው ኪሱን ደባብሶ አንድ አነስተኛ የወርቅ ቀለበት አውጥቶ በጣቱ ሞካከረውና ፣ «አይሆነኝም ! የገደልኩት ፋሽስት ገና ጢም ያላወጣ ልጅ እግር ነበር» አለ ።

«ቀለበቱ የራስህ መስሎኝ!»አለው አዱኛ።

«የራሴ አይደለም ። ጆሮዬን ከሸረከተኝ ፋሽስት ጣት ላይ ነው ያገኘሁት» አለ ። አዱኛና የተቀሩትም የተተረተረ ጆሮውን እየተመለከቱ ይሥቁበት ጀመር ።

«ምን ያሥቃችኋል ? ተሸረከተ እንጂ ተጐርዶ አልወደቀ ! ቁስሉ ሲደርቅ መልሶ ይይዛል» አለና ፣ «የሆነ ሆኖ ፋሽስቱን ለዚህ ድፍረቱ ደህና አድርጌ ቀጣሁት ። በጉራዴዬ ቀልቼው ራሱና የተቀረ ሰውነቱ ለየብቻ ሲወድቅ ፣ ይህ ቀለበት በጣቱ ላይ ሆኖ ሲብረቀረቅ ታየኝ ። ከጣቱ አውልቄ ኪሴ ከተትኩት» አላቸው ።

«አበጀህ!» አለው አዱኛ ፤ «ባሕር ተሻግረው ፣ አገር አቋርጠው ወደዚህ መምጣታቸው የእኛን ንብረት ለመዝረፍና የእኛን ሕይወት ለማጥፋትም አይደል ! አበጀህ ! አበጀህ !»

«ሌላም ነገር አለኝ» አለና ቢጋሻው ፣ «ባሻስ ? ከጠላት ንብረት ምን ደረሰህ ?» ሲል ጠየቀው።

«ምንም ! ይህንን ውብ ጠመንጃ ከመማረክ በስተቀር...»

«ሌላ ምንም አልደረሰህም ? እንግዲያውስ ይህንን ልስጥህ» ብሎ በሲጋራ የታጨቀ የሲጋራ መያዣ ማጥን ከኪሱ አወጣ ።

«ምን ነካህ ቀውሴ ? ትምባሆ እንደማል ወድ እያወቅህ...!»

«ትምባሆ እንደማትወድማ ዐውቃለሁ ። ልስጥህ ያልኩህ ሲጃራውን ሳይሆን መያዣውን ማጥን ነበር» አለና፡«ለመሆኑ ሲጃራ የሚፈልግ አለ?» ሲል ጠየቀ ፡ ዓይኑን ወደ አዴላ አዞረ ።

አዴላ ፊቱን አጠቀረበት ። እሱም ሲጋራ ይጠላ ነበር ። «በተስኪያን ያወገዘችው... የእር የስ ምንትስ...» አለ በማንጓጠጥ ።

«በል እሺ ተወው» አለና በጋሻው ፊቱን ወደ ተመስገን አዞረ ፡ «አንተስ ?» ሲል ጠየቀው ።

«እ...?»

«ሲጃራ ትፈልጋለህ ?»

«ከሰጡኝማ ፡ ጌታዬ...»

በጋሻው በሲጋራዎቹ ማጥሪያዎች ዙሪያ የነበሩትን አብረቅራቂ ወረቀቶች በጥሞና አስ ተዋላቸውና ፡ «እንካ» አለው ። ተመስገን እጅ ነሥቶ ሲጋራዎቹን ተቀበለው ።

በጋሻው የሲጋራዎቹን ማጥን ለባሻ ሊሰ ጠው እጁን ሲዘረጋ ባሻ ቅጣው ፡ «ምን ያረግል ኛል ? አልፈልገውም» አለው ።

«ከንጹሕ ብር የተሠራ ነው ፡ ባሻ ! ከፍተኛ ዋጋ ያለው...»

«እኔ የምፈልገው መሣሪያ ! ጠበንጃና ጥይት...!»



«እኔ ምን እንዳገኘሁ ታውቃላችሁ?» አለ አዴላ በዚህ ጊዜ ፤ «እዩትላችሁ ! በሊሬ የታጨቀ የገንዘብ መያዣ ቦርሳ !»

«ቦርሳውስ ይሁን ፤ ነገር ግን የጣሊያን ገን ዘብ ምን ሊፈጥርልህ ነው ? ፊላጊ የለውም» አለው በጋሻው ።

«ለሱ ግድ የለህም ! ወደ ሞቃዲሾ የሚሄድ ሰው አላጣም ። ጠገራ ብርና ግርሽ እኛ ዘንድ መለዋወጫ እንደሆኑ ሁሉ ፡ በኢጣሊያ ሱማሌ የመለዋወጫ ገንዘብ ሊሬ መሆኑን አታውቅም ?»

«እሺ ካልክስ...» ብሎ ተከዞ አለና በጋ ሻው ፡ «እኛም ዘንድ የሚፈለግበት ጊዜ ይመጣ ይሆናል ። ማን ያውቃል ! አያድርገው እንጂ...» አለ ።

«የሰውን ቅስም የሚሰብር ነገር አትናገር ቀውሌ» አለው ባሻ ቅጣው ፡ ነገሩ ዘግንኖት ።

«ጦርነቱ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ...»

«በልኮ በቃህ! ስለ እግዚአብሔር ብለህ የሰውን ቅስም የሚሰብር ነገር አትናገር ።»

ኢትዮጵያ ትሸነፋለች የሚል ሐሳብ በባሻ ቅጣው አእምሮ አንዳችም ጊዜ አድሮ አያው ቅም ነበር ።

እንዲህ እያረፉ ሲጨዋወቱ ሳሉ ከሩቅ ኮሽታ ሰሙ ። የጠላት አመጣጥ ዘዴው ስለማ ይታወቅ ፈጥነው በደረታቸው ተኝተው ድም ፃቸውን አጥፍተው መሣሪያቸውን ደግነው ይጠ ባበቁ ጀመር ። ኮሽታው እየተበራከተ ፡ እየጉላና እየተቃረበ ሲመጣ ፡ የጣሊያኖች ሳይሆን የጣሊ ያን ቅጥረኞች እንቅስቃሴ መሆኑ ታወቃቸው።

ወዲያው ጸጉራቸው የጎፈረና ቅቤ የጠገቡ ቁመናቸው መለል ብሎ የወጣ ፣ የጠላት ተባባሪ ወንበዴዎች ብቅ አሉ ። ጣሊያኖች በገንዘብ ደልለው በየመንገዱ ተዳክሞ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ጦር አሳድደው እንዲገድሉ የላካቸው ነበሩ ።

እነ ባሻ ቅጣው የሰዎቹን ማንነት ሲረዱ ወዲያውኑ ተኩስ ከፈቱባቸው ። አሥሩም ወንበዴዎች ስለታቸውን እንደ ታጠቁ ፣ ጦራቸውን እንደ ጨበጡ መሬት ላይ ወርደው ተነጠፉ ። ከመካከላቸው አንዱ ብቻ ጦሩን ለመወርወር ጊዜ አገኘ ። ጦሩ በአደላ ላይ የተቃጣ ነበር ። አደላ በቶሎ ነቅቶ ዞር ስላለበት የጦሩ አፍሬ ከበስተኋላው በነበረ ቁልቋል ግንድ ውስጥ ገብቶ ተቀበቀበ ። ረጅም እጀታውም አየር ላይ ሲባበቅ ባለ ከቁልቋሉ ግንድ ወተት የመሰለ ነጭ ፈሳሽ ቁልቁል ወደ መሬት ይዝረበረብ ጀመር።

፯

የራስ ሙሉጌታን መውደቅ በዓይኑ ያየ አንድ ወረኛ ፈረስ ላይ ወጥቶ ወደ ደሴ አቅጣጫ መብረር ጀመረ ። ከፍጥነቱ የተነሣ ነጠላው ከሰውነቱ ተመንጥቆ ለመሄድ የፈለገ ይመስል ወደ ኋላው እየሸሸ ሲውለበለብ ነበር ።

እሱም በነፋሉ ግፊት ወደ ኋላ እንዳይወድቅ



እንደ ፈራ ሁሉ ሰውነቱ ወደ ፊት አዘንብሎ ጎይኑን በፈረሱ ጀርባ ትይዩ አድርጎ ሽምጥ ግልቢያውን ቀጠለ። ዳገትና ቁልቁለት ሲያጋጥመው ፈረሱን ገታ እያደረገ፣ አውላላ ሜዳ ሲገባ መልሶ ሽምጥ እየጋለበ ፣ ፈረሱን ሳያሳርፍ እሱም አንዳች ነገር ሳይቀምስ በባዶ ሆዱ እንዲሁ ሲጣደፍ ቀለና ጊዜው ለዓይን ሲይዝ ከአንድ መንደር ደረሰ ። "ቤቶች !" ብሎ ከማያውቀው ቤት ገብቶ ታሪኩን ተናግሮ እህል ውኃ ቀማምሶ ፈረስ ቀይሮ የሌሊት ጉዞውን ቀጠለ ።

በማግሥቱ ጥዋት ከሌላ መንደር ደርሶ አሁንም "ቤቶች !" ብሎ ከማያውቀው ቤት ገብቶ ታሪኩን ተናግሮ ትኩስ ፍርፍር ቀማምሶ አሁንም እንደገና ፈረስ ቀይሮ በአዲስ ኃይል ፣ በአዲስ ጉልበት ጉዞውን ቀጠለ ። ኸው ብሎ ሲያልፍ ላየው ሰው ረቂቅ መንፈስ እንጂ ሥጋ የለበሰ ሰው አይመስልም ነበር ።

እኩለ ቀን ላይ ካሰበበት ደርሶ ከፈረሱ ወርዶ ዱብ ሲል ከአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር ተገናኘ ። ባለ ሥልጣኑ የሰውዬውን የተረበሸ ገጽታ አስተውለው ከጦር ሜዳ የመጣ ወሬ ነጋሪ መሆኑም ገብቷቸው ፦

"ምን ደረሰ ? ፊትህ እንዲህ ለምን ጠቆረ ?" አሉት።

"የራስ ሙሉጌታ ጦር ተፈትቷል ፣ ጌታዬ" አላቸው።

"ተፈትቷል...!" አሉ ባለሥልጣኑ ደንገጥ ብለው፤

"ለመሆኑ ራስ ሙሉጌታ በአሁኑ ሰዓት የት ናቸው?"

"ራስ ሙሉጌታ ወድቀዋል ፣ ጌታዬ ።"

"ወድቀዋል... ?"

"አዎን ወድቀዋል...ሲወድቁም በዓይኔ አይቻለሁ።"

"የአጋጋታቸው ሁኔታ እንዴት ነው ?"

“ለራስ ሙሉጌታ ሞት ምክንያት የሆኑት ለጠላት ያደሩ ወንበዴዎች ናቸው ። የራስ ሙሉጌታ ልጅና በር ክት ያሉ ሌሎች ጦረኞች በመሸሽ ላይ ሳሉ መንገድ ላይ አደፍጠው አደጋ ጣሉባቸው ። ራስ ሙሉጌታም በል ጃቸውና በተቀሩትም ተከታዮቻቸው ላይ የደረሰውን አደጋ ለመበቀል ገዳዮቹን በመከታተል ላይ እንዳሉ የኢጣሊያ አውሮጵላን አብራሪዎች ድንገት ደርሰው መንገድ ላይ አስቀሯቸው ። በወንበዴዎቹ መዘዝ ነው ራስ ሙሉጌታ የሞቱት ፣ ጌታዬ ! ”

“በጣም የሚያሳዝን አደጋ ነው ። የእኚህ ታላቅ ሰው መውደቅ ኃይላችንን ይቀንሰዋል ። ለማንኛውም ይዘኸው የመጣኸውን መልእክት ለዋናው ጦር ሠፈር አሁኑኑ አስተላልፋለሁ” ብለው አሰናበቱት ።

ባለሥልጣኑ በጥድፊያ ወደ ዋናው ጦር ሠፈር ሄደው የሰሙትን አሳዛኝ ዜና ለከፍተኛ ባለሥልጣኖች አስተላለፉ ። ወዲያውኑ ጉባዔ ተደረገ ። ከመማክርቱ መሐከል ፣ መሐል ጦሩ ከተፈታ ፣ ራስ ሙሉጌታ ከወደቁ ፣ ሚስተር ሆርና ሚስተር ላቫል ቀደም ብለው ያቀረቡትን ሐሳብ መቀበል ሳይበጅ አይቀርም የሚል ሐሳብ የሰነዘሩ ነበሩ ።

ሚስተር ሆር የእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ፣ ሚስተር ላቫል የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ነበሩ ። እነዚህ ሁለት ሚኒስትሮች በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሐከል የተነሣውን ጦርነት ለማብረድ ኢትዮጵያ ትግራይንና ኡጋዴንን ለኢጣሊያ እንድትሰጥ ፣ ከኢጣሊያ ጋር የኢኮኖሚ ግንኙነት እንድትመሠርት ፣ ኢጣልያም በበኩሏ ከዚህ በላይ እንዳትጠይቅና ጦርነቱንም አቁማ ሰላም እንዲመሠረት የሚል ሐሳብ አቅርበው ነበር ።



“ኢትዮጵያ ከመሬቷ ቁርሳ አንድ ጋት እንኳ ቢሆን መስጠት አይገባትም” አሉ ወሬ ነጋሪውን ያነጋገሩት ባለሥልጣን ። “ቁርሳ ብትሰጥም እንኳ ጦርነቱን ሊያስቀር አይችልም ። ኢጣሊያ ትናንት የአገራችን በር የሆነችውን ኤርትራን ያዘች ። ይህ አልበቃት ብሎ መላውን ኢትዮጵያ ወረረች ። ዛሬ ትግራይና ኡጋዴን ቢሰጧት ነገ ሌላ ጦርነት አንሥታ ጐንደርና ጐጃም ካልተሰጡኝ ማለቷ አይቀርም ። ጐንደርና ጐጃም ቢሰጧት ከሸዋ በስተቀር የተቀሩት ግዛቶች ካልተሰጡኝ ብላ እንደገና ጦርነት እንዳታውጅ የሚያግዳት አይኖርም ። ከዚያም በኋላ ሸዋስ ለምን ይቅርብኝ ብላ ሌላ የጦርነት እሳት መጫሯ አይቀርም ። ስለዚህ ሆርም ሆነ ላቫል ያቀረቡት ሐሳብ ለጊዜው ጦርነቱን የሚያበርድ ቢመስልም ፣ ኢትዮጵያን የሚያዳክም ጣሊያንን የሚያጠናክር እንጂ ለችግሩ ዘላቂ መድን ሊሆን አይችልም ።”

“ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከምታጣ ሆርና ላቫል ያቀረቡትን ሐሳብ መቀበል ይሻል ይመስለኛል” አለ ከመማክርቱ አንዱ ፤ “ኢትዮጵያ የኢጣልያንን ኃይል ለመቋቋም እንደማትችል ጉልህ እየሆነ መጥቷል ፤ በዚያ ላይ ደግሞ የመሣሪያ እገዳው ካልተነሣ በስተቀር ኢትዮጵያ ምንም መሣሪያ መግዛት አትችልም ።”

የዓለም መንግሥታት ማኅበር በኢትዮጵያና በኢጣልያ መሐከል የተነሣውን ጦርነት ለማብረድ በሁለቱም አገሮች ላይ የመሣሪያ እገዳ እንዲደረግ ቢወስንም እንኳን ፣ የአውሮፓ ሕሊና ታውሮ ነው እንጂ እገዳው ጦርነቱን ሊያበርድ የሚችል አልነበረም ። ከዚያም አልፎ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ቅኝ ግዛት ለማድረግ የሚያመች ሁኔታ የሚፈጥርላት ነበር ። ኢትዮጵያ ከተራ ጥይት በስተቀር ሌላ ዓይነት ዘመናዊ መሣሪያ ሠርታ አታወጣም ነበር።

የቴክኒኩም ሆነ የገንዘብ አቅም አልነበራትም። ኢጣሊያ ግን ከተላለ መሣሪያ እንሥቶ እስከ ጦር አውሮፕላን ሠርታ ታወጣ ነበር። እገዳው ኢትዮጵያ ባላት ትንሽ የገንዘብ አቅም ከውጭ መሣሪያ እንዳትገዛና ጠላቷን እንዳትቋቋም የሚያደርጋት እንጂ ጣሊያንን የሚጐዳ ወይም ጦርነቱን የሚገታ አልነበረም።

በአማካሪዎቹ መካከል የተፈጠረው የሐሳብ ልዩነት ለረጅም ጊዜ ካከራከረ በኋላ የመጨረሻ ውሳኔ ተደረገ። በዠኔቭ ያሉት የኢትዮጵያ መልእክተኛ የዓለም መንግሥታት ማኅበር እገዳውን እንዲያነሣ በድጋሚ እንዲጠይቁ፣ የዓለም መንግሥታት ማኅበር የኢትዮጵያን ጥያቄ ለመቀበል ሳይፈቅድ ከቀረም ኢትዮጵያ ባላት መሣሪያና ኃይል አጥቂዋን እንድትከላከል ተቆርጦ ጉባኤው ሲነሣ አሸባሪ የሆነ ሩምሩምታ ተሰማ።

"ምንድነው ?" አለ አንድ ድምፅ።

"አውሮፕላን ነው" አለ ሌላ ድምፅ፣ "የጦር አውሮፕላን..."

በእርግጥም የጠላት አውሮፕላኖች ደሴ ከተማ ዙሪያው አየር ላይ እያንዣበቡ ከተማውን ለመደብደብ ዒላማ ሲመርጡ ነበረ።

ጠላት ዋናውን የጦር ሠፈር ከመደብደቡ በፊት እዚያ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር በአስቸኳይ ወደ ሰሜን ጉዞ እንዲጀምር፣ በሰሜን ክፍላተ አገር የነበሩ ጦረኞችና ከአምባራዶም ውጊያ በኋላ ወደ ደቡብ በመመለስ ላይ የነበረውም የራስ ሙሉጌታ ጦር ወደ ማይጨው እንዲገሰግስ በየአቅጣጫው መልእክትና ትዕዛዝ ተላለፈ። ማይጨው የኢጣሊያ ጦር የተከማቸበት በአምባራዶምና በደሴ መሐከል የሚገኝ የመጨረሻው የፍልሚያ ሜዳ እንዲሆን የታጨ ሥፍራ ነበር።



## ፯

የኢትዮጵያ ጦር ቀን ቀን አውሮፕላን እንዳያ ዩ ለማይታይበት እሳቸው አዛቸውን መንገድ እየመረጠ፣ ሌሊት ተናውን መንገድ በመጓዝ ሲጓዝ ወሩ እድር ከማይ ጨው አካባቢ ደረሰ።

ማይጨው ሸለቆዎችና ጉብታዎች ተፈራርቀው የሚታዩበት ዐቀበትና ቁልቁለት ያሸበረቀ እሳማ የሚዘ ምሩበት የቀንድ ከብቶችና ፍየል ከብቶች የሚግጡ በት አረንጓዴ ሣር ቅጠል የለመለመበት እንደ ምግድ ጠንካራ ሥራ አካባቢው የዓይን ማረፊያ የመንፈስ ማደሻ የእርምር ማሳረፊያ የሆነ የሰላም አካባቢ ነበር...

በመጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፰ ዓ. ም. ግን ጸጥታ ሰላ ታና ሰላም ወርቃቸውን ጠቅለው ከአካባቢው ወጥተው ነበር። ጦርነቱ ገና ሲቀድ ተጀመረ። በወገን ጦር በኩል የተመረመረው የሌሊት አደጋ በድንገት በጠላት ሠፈር ሲደርስ፣ ምድሪ ሩጫለት ተደናገጠ። ወዲያውኑ የጠላት ጦር እንዳውን በመመለስ የሌሊት አደጋ በወገን ጦር ሠፈር እንዲደርስ አደረገ። ከጥ ቂት ጊዜ በኋላ ጦርነቱ ተፋፋመ።

ረዘም ላለ ጊዜ የወገን ጦር የጠላትን ጦር ከመግ ፋት አልፎ ቀኝ እጅ ያገኘ መሰለ። የጠላት ጦር ምሽ ጉን እየለቀቀ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመረ። የወገን ጦር የምሥራቅ ብርታት አገኘ። ጠላትን እያጋደመ ይደበልል ይፎክር ገባ—ወጣው እየፈነቀለው።

የጠላት ምድር ጦር ማፈግፈግ ሲጀምር አየር ኃይሉ ደረሰ፣ "እያያሁ ! አልሁልሁ !" ይለው ጀመር። ይሁን እንጂ የጠላት አየር ኃይል አምባራዶም ላይ

እንደፈነጨ እዚህም እንደ ፈለገው ለመፈንጨት አልቻለም ። የክብር ዘበኛው ጦር ጥቂትም ቢሆን የአውሮፕላን ማውረጃ መሣሪያና ጥይት ነበረው ። ጦሩ ይህንኑ መሣሪያ ወደ ሰማይ ደግኖ ሲተኩስ አንድ የጠላት አውሮፕላን የበረራ ሚዛኑን ሳተ ። "ተመትቷል ! ተመትቷል !" እያሉ ይፈነድቁ ጀመር—ዓይናቸውን ወደ ሰማይ ሰቅለው ሲመለከቱ የነበሩ የወገን ጦር አባሎች ።

"ያውና ! ተመትቷል ! ተመትቷል !"

አውሮፕላኑ እየነደደና ጥቁር ጢስ እያትጐለጐለ ተምዘግዝጎ ሄዶ ከጦሩ ሜዳ አልፎ ምድር ላይ ተከሰከሰ ። የወገን ጦር እንደገና ሲተኩስ ሌላ አውሮፕላን በእሳት ተቀጣጥሎ እሱም እየተምዘገዘገ ሄዶ መሬት ወርዶ ይጋይ ጀመር ። የወገን ጦር አሁንም ይፈነድቅ ገባ ። ጦርነቱም በሰማይም በምድርም በበለጠ እየተጧጧፈ ሄደ ። አሁንም ሌላ አውሮፕላን ተመትቶ ተመሳሳይ ጥፋት ደረሰበት ።

ጦርነቱ ከሰዓት በኋላም ቀጠለ ። ባሻ ቅጣውና ባልደረቦቹ ከነጋ ጀምሮ አንዳችም ነገር ሳይቀምሱ በተጣጣፊ አንጀት ሲዋጉ ነበሩ ። ሆኖም ግን ሙሉ ሐሳባቸው በውጊያው ላይ ስለ ነበረ ረሃብ ፈጽሞ አልተሰማቸውም ። እንዲሁ ሲጋደሉ ሳሉ በዓይን የማይታይ ፣ ነገር ግን ሰናፍጭ ሰናፍጭ የሚሸት ነገር ከሰማይ ይወርድ ጀመር ። የወገን ጦር ጥይት ሳይመታው ፣ የቦምብ ፍንጣሪ ሳይነካው እንዲሁ መሬት ላይ ተጋድሞ የሥቃይ ጩኸት ያሰማ ጀመር ። ከጦር ሜዳው ውጭ ሣር ሲግጡ የነበሩትም የተሰማሩ ከብቶች የጦረኞች መጓጓዣ በቅሎዎችና ፈረሶች ሜዳ ላይ ተንደባልለው ያጓሩ ጀመር ። እነባሻ ቅጣውም የሸታው ምንነት አጠራጥሯቸው ። ሸሸት አሉ ።



"ምንድነው ? ምንድነው ?" እያሉ ፣ ርስበርሳቸው ተጠያየቁ ።

"መርዝ ነው !" ብሎ ጮኸ ፣ አንድ ጦረኛ ።

"ምን አልክ ?" አለው ሌላው ።

"ተበታትናችሁ መጠለያ ፈልጉ ። መርዝ ነው ! መርዝ ! " አለ ሰውዬው ቀጠል አድርጎ ፣ እሱም እየሸሸ ።

ጣሊያኖች መርዙን በሁለት መንገድ ይለቅቁት ነበር ። አንዳንድ ጊዜ በርሜል በመሰለ ነገር እንደ ቦምብ ይጥሉትና በርሜሉ ሲፈነዳ መርዙ ወጥቶ ሰውና ከብት ላይ ይረጭ ነበር ። በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ተባይ ማጥፊያ ከአየር ላይ ሆነው ወደታች ይረጩት ነበር ። ጠብታው በሰውነት ላይ ሲያርፍ ያረፈበትን ሰው ገላ እየበላ ፣ እየተስፋፋ ሄዶ አሠቃይቶ ይገድል ነበር ። በዓይንም ላይ ሲያርፍ ያረፈበትን ሰው ዓይን አቃጥሎ ያሳውረው ነበር ።

ፋሺስት ኢጣሊያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር በሕግ በከለከለው በመርዝ ጢስ ትጠቀማለች ብሎ ያሰበ ስላልነበረ የወገን ጦር የመከላከያ ሽፋንም ሆነ የመዳኛ መድኃኒት አላዘጋጀም ነበር ። በዚህ ምክንያት ከመርዙ ካፊያ ለመዳን ከመሸሽና መጠለያ ከመፈለግ በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበረም ።

የመርዙ ርጭት የወገንን ጦር ሞራል ፈጽሞ ሰበረው ። በዚያ ላይ የአውሮፕላን ማውረጃ ጥይት ስላለቀ የኢትዮጵያ ጦር እንደገና ለአየር ጥቃት ተጋለጠ ። የማይጨው ጦርነት እንደ አምባራዶም ጦርነት በመሣሪያ ኃይል ባልተመጣጠኑ ጦሮች መሐከል የሚካሄድ ውጊያ ሆነ ።

ማምሻው ላይ ወጊያው ጋብ ካለ በኋላ ጥናውን ጦር ተከትሎ መጥቶ ዜና ሲያጠናቅር የነበረው ጆን ብሉም ወደ ከፍተኛው ኢትዮጵያዊ አማካሪ ቀረበ፡—

"ምን መልእክት አለ፣ ጌታዬ ?" ሲል ጠየቃቸው ፤ የመንግሥት አፈ ቀላጤ እንደሆኑ ያውቅ ነበርና ።

"አንድ ጊዜ ቆየኝ" ብለውት ወደ አንድ በፍራሹ ያለው ቆየት ካሉ በኋላ ተመልሰው መጡ—ፊታቸውን ፈገግታ ጉም አስመስለው ።

"መልእክት አለዎት፣ ጌታዬ" ሲል ጠየቃቸው ጆን ብሉም በድጋሚ ።

"እምን...ብቻ መብራቱ ይታይሃል ?"

"በደምብ ይታየኛል...መልእክቱን ይንገሩኝ "

"መቼም አንተው ራስህ የኢትዮጵያ ሠራዊት በመርዝ ጢስ ተቃጥሎ ሲረግፍ በዓይንህ አይተሃል" አሉት ባለሥልጣኑ ፤ "የሠለጠነው ዓለም ይህንን የአረመኔ ወጊያ አይቶ ዝም ካለ፣ የዓለም መንግሥታት ማኅበርም ይኸን ጥፍዉና በቸልታ ከተመለከተው፣ ነገ በኔ ነውና በዚህ ምድር የፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ንጹሕ ደም ተፈንጥቆ ሄዶ አውሮጳን እንደሚያቃላው የዓለም መንግሥታት እንዲረዱት ያሻል ብለህ ጻፍ ። ይህንኑ የኢትዮጵያን መልእክት ማስተላለፍ አለብህ" አሉት ።

ሌሊቱ ጨለማ የበረከተበት ሆነ ። የማይጨው አካባቢ አውሬዎች በተለይም ጅቦቹ ሲሳይ ተርፏቸው ሲፈነጩ እመኝ ሲሉና ሲያስካኩ አደሩ ።

ሊነጋጋ አቅራቢያ የኢትዮጵያ ባለሥልጣናት ከከፍተኛ እስከ ዝቅተኛ ደረጃ ያሉት፣ እና የኢትዮጵያ



ጦረኞች ካደሩበት ተነሥተው ፊታቸውን ወደ አበቦ በት አቅጣጫ አዞሩ ፤ ከዚያ ወዲያ ግልጽ ጦርነት መጥጋት የሞኝነት እንጂ ብልሀነት ሆኖ አልታይ ብሏቸው ነበርና ። ደከምክም ያሉት ወደየቀዬአቸው ወደየሠፈራቸው ወደየመጡበት ከተማና ገጠር ሲያመሩ የተቀሩት ግን በየፊናቸው ተከፋፍለው ወደየሚኬው ወደ የበረሃው ወደየገመገሙ ይጓዙ ጀመር—ዘዴ ተይረው በአዲስ መልክ ጠላትን ለመቋቋም...

ማርሻል ባዶሊዮ በጣሊያን አሸናፊነት ጦርነቱ ያበቃ ቢመስለውም፣ ጥፍዉናው አላረካውም ነበር ። የአድዋን ቂም ለመበቀል ገና ሥፍር ቍጥር የሌለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጦር ሠራዊቱም ሆነ ሲቪሉ በይበልጥ መጨፍጨፍ አለበት ብሎ በግምት አየር ኃይሉ ማጥቃቱን እንዲቀጥል አዘዘ ።

የጣሊያን ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች እንደ ተለመደው ከ፲፪ እስከ ፳ እየሆኑ መብረር ጀመሩ ። ከማይጨው እንሥቶ በበተደበብ እስካለው አሸንጌ ሐይቅ ያለው አገር በቦምብ ይታረስ ጀመር ። "ቡም ! ቡም ! ቡም !" የገጠር ጎጆዎች ይጋያሉ ። ቤተክርስቲያናት ይጋያሉ ። ኮረብታዎች ሸለቆዎች ሜዳዎች ይጋያሉ ። በጣዩ ምድሩ አየሩ ይጋያል...

የበቀል ርምጃ ሰውን ከሰው የማይለይ በመሆኑ በዚህ እለቲት የተጎዱት በሽሽት ላይ የነበሩ ጦረኞች ብቻ ሳይሆኑ፣ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሰላማዊ ሰዎችም ጭምር ነበሩ...አዛውንቶች ባልቴቶች ሕጻናት ሴቶች ሌሎችም...

## ፳

ባሻ ቅጣው በጋሻውና አዴላ ከእልቂቱ ተርፈው መልስ ጉዟቸውን ጀመሩ—ወደ አዲስ አበባ ። ተመስገን ግን ከእነሱ ጋር አልነበረም ። የባሻ ቅጣው በቅሎ በመ ርዝ ጢስ ተቃጥሎ ሲሞት ካየ በኋላ የመጠበቁ ዕዳ ከትከሻው ወርዶለት እንደተቀረው ጦረኛ ሲዋጋ ነበር ። ጦሩ ከተፈታ በኋላ ግን ግርግር ስለ በዛ እነባሻ ጠፍ ተውበት ከሌሎች ጦረኞች ተደባልቆ በሌላ መንገድ ሲኳትን ነበር ።

መልስ ጉዟቸውን ቀጠሉ እነባሻ ። ከሰባት ወራት በላይ ሌትም ሆነ ቀን ከሰውነታቸው ያልወረደ ልብ ሳቸው ተቦጫጭቋል ፥ አድፏልም ። የእያንዳንዳቸው ልብስ ሽብሽባት የቅማል መራቢያ ሆኗል ። እነሱም ስንጥር ቢጤ ፈልገው ጀርባቸውን ማከክ ተጨማሪ ጣጣ ሆነባቸው ።

ደም ያስከረው የጣሊያን አየር ኃይል እንዳያያቸ ውና በየቦታው አድፍጠው የሚጠብቁትም ወንድ አዳኝ ወንበዴዎች እንዳያገኟቸው ፥ ቀን ቀን ከሠዋራ ስፍራ እየተኙ-ብየተራም ዘብ እየቆሙ ሌሊት ሌሊት ብቻ ችቦ አብርተው ፥ የገዛ ጥላቸውን እስክስታ እያስተዋሉ ይጓዙ ነበር ። የምግብ ችግር ነበረባቸው ። ባጋጠማቸው ጊዜ የዱር አውሬ እያደኑ አለዚያም የበልግ እሸት ካለበት ማሳ ሲደርሱ ጥሬ እሸት እየተመገቡ መንገዳቸውን ቀጠሉ ።

አዲስ አበባ ለመድረስ ገና ግማሽ መንገድ ያህል ሲቀራቸው አንድ ቀን ሌሊት ኃይለኛ ዝናብ ጣለ ። ዝናቡ ቢያበሰብሳቸውም የሌሊት ጉዟቸውን ቀጠሉ ።



ችቦ እንዳያበሩ ርጥበቱ ስለ ከለከላቸው በጭለማ ነበር እያሳበሩ የሚጓዙት ። እንዲሁ ሲሄዱ ሲሄዱ ቆዩና ከአ ንድ ጅረት ደረሱ ። ጅረቱ ጥልቅ ይሁን አይሁን ስላ ላወቁ ከዳር ቆመው ይመለከቱት ገቡ ።

በጋሻው ከተቀሩት ሁለት ባልደረቦቹ በጣም ይረ ዝም ስለ ነበረ ፥ "እኔ ልምራችሁና እንሻገር" አላቸው ።

"ዋና ትችላለህ ?" ሲል ጠየቀው አዴላ ።

"ዋና እንኳን አልችልም ። ዱጋ ስለ ተወለድሁ ዋና አልተማርኩም ። ሆኖም ጅረቱ እስከዚህም ጥልቅ አይመስልም ። "

"አይታወቅም ቀውሌ ! ከወደ መሐሉ ጥልቅ ሊሆን ይችላል" አለና ፥ "ቆይ ቆይ ! ምን ማድረግ እንደሚገ ባን እኔ ዐውቃለሁ ። ዘንግ ቆርጬ በዳበሳ ለመሻገር እሞክራለሁ ። ድንገት ውኃው ቢጥለኝ ውኃ ዋና ስለ ማውቅ ምንም ሥጋት የለም" ብሎ ዘንግ ለመቁረጥ ከጫካ ዘው አለ ። አጠና መሰስ የሆነ ረጅም ዘንግ ሰብሮ ቅጠሉን እየመለመለ ተመልሶ መጣ ።

ባሻ ቅጣው እስከዚህ ጊዜ ድረስ ዝም ብሎ ቆሞ ነበር ፥ የውኃውን ሁኔታ በሰማዩ ብልጭታ እያስተዋለ ። ከወደ ጋራው የዘነበው ዝናብ ጉርፍ ጅረቱን ቅራሬ ከማ ስመሰሉም በላይ ዝግ ወንዝ አሳክሎት ነበር ።

"ውኃው እስኪጐድል ድረስ ብንጠብቅ አይሻልም ?" የሚል ሐሳብ ሰነዘረ ባሻ ቅጣው ።

"በዚህ ዝናብ...በዚህ ብርድ...ውኃው እስኪጐድል ልንጠብቅ ?" አለው አዴላ በተቃውሞ ድምፅ ። ጉዟችንን ካልቀጠልን ብርዱ ያቆራፍደናል ፥ ባሻ ።"

"እንግዲያው ዳር ዳሩን ይዘን እንግባ! የመሻገሪያ የአጥር ድልድይ እስከናገኝ ድረስ..."

"ወንዙን ተከትለን ብንሄድ ወዴት እንደሚያመራን አናውቅም፤ ባሻ። ወደ ምንሄድበት ሥፍራ በማቅረብ ፈንታ እያራቀን ሊሄድ ይችላል።"

"ከምናውቀው ጅረት ውስጥ ከመግባት በሩቅ መንገድ በሰላም ወደ ቤታችን ብንገባ አይሻልም!"

"ምን ነው ያሠጋህ፤ ባሻ! ቀድሞ የምትጨነቀው እኔ! ድንገት አዳልጦኝ ብወድቅ እንኳ ውኃ ዋና ስለ ማውቅ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም፤ ባሻ። ጋሻዬ እየሽ ዳር ድምበሩን ጥሶ በሚጥለቀለቅበትና ግንድ በሚያንሳፍፍበት በነሐሴ ወር እንኳ በዋና ተሻግሬያለሁ። ታዲያ ይቺ ጅረት ምን አቅም አላት ብለህ!"

ባሻ ቅጣው ቀፈፈው። ብዙ ሞካሪዎች ዋና እንችላለን በማለት በድፍረት ገብተው ውኃ እንደሚወስዳቸው፤ ዋና የማያውቁት ግን ፈርተው ለእንደዚህ ዓይነት አደጋ እንደማይጋለጡ ያውቅ ነበር።

እዴላ ግን ጅረቱን በቆም ለመሻገር ቆርጦ በልበ ሙሉነት ወደ መግቢያው ቀረበ። ውኃው እስከ ደረቱ እንኳ የሚደርስ አልመሰለውም። ልብሶቹን አውልቆ ራሱ ላይ ጠመጠማቸው። መሄሪያውን በግራ እጁ ከፍ አድርጎ ይዞ በቀኝ እጁ ዘንጉን ወጋው ውኃው ውስጥ ገባ። ከትከሻው የተሻገ ሰውነቱ በረደ የኳ መሰለው። እየገፋ በሄደ ቁጥር ውኃው ከእግሩ ወደ ጉልበቱ፤ ከጉልበቱ ወደ ታፋው፤ ከታፋው ወደ ላይ እየተነሣ ሄደ። እሱም የሚሄድበትን በዘንጉ ወጋግቶ እየቀ ቀስ ብሎ መረማመዱን ቀጠለ። ሩብ መንገድ ያለ



ከዚያ በኋላ ቆም ብሎ ፊቱንም ወደ ኋላ ባልደረቦቹ አዞሮ፤ "ቅዝቃዜው አጥንት ሰርስሮ ይገባል" አላቸው፤ "በቃ እናንተም ልብሳችሁን አውልቃችሁ ለመሻገር ተዘጋጁ" ብሎ እንደገና ጀርባውን ሰጥቷቸው መንገዱን ቀጠለ።

ሰማዩ በረቀ። በመብረቁ ብርሃን የእዴላ ጀርባ ለባሻ ቅጣውና ለበጋሻው ወለል ብሎ ታያቸው። መብረቁ ድርግም ሲል ግን የሚያንበረክቀው ውኃ ድምፅ ይሰማቸው ነበር እንጂ እሱ ራሱ አይታያቸውም ነበር። እንዲሁ እንደ በዓይናቸው እንደ በጆሮአቸው ሲከታተሉት ቆይና ወደ መሐል ሲደርሱ ድንገት ደራሽ ፈረሰኝ ውኃ እዴላን ያጣድፈው ጀመር። ውኃው እንዲሁ ተነሥቶ ሲወድቅ እዴላን በጥሬ የሚያታግለው ይመስል ነበር። የውኃው ኀይል እየጠነከረ ሲሄድ እዴላ መንገዳገድ ጀመረ። አሁንም እንደ ገና ድንገት ደራሽ ውኃ ተነሥቶ ሲወድቅ የእዴላን ጀር ግንድ በጥሬ የሚያመለው መሰለ። እሱ ግን የሰውነቱን ሚዛን እየጠበቀ መረማመዱን ቀጠለ። ውኃው አሁንም እንደ ገና ወደ ላይ ተነሥቶ በራሱ ሲቸለስ በአፉ ገብቶ ትን እስኪለው ትንፋሹን ለመመለስ ሲጣጣር እየተናነቀው በውኃው ኀይልም እንዳይወድቅ እየታገለ ሲሄድ ሳለ ዘንጉ ከታች ገደል ሲል ተሰማው። ከሥር ያለው የውኃው ኀይል እጅግ የበረታ ስለነበረ እዴላ ዘንጉን በትክ ይዞ ለማቆየት ሳይችል ቀረ። ዘንጉንም መሄሪያውንም ለቀቅ እጆቹን ማወራጨት ጀመረ። ባሻ ቅጣውና በጋሻው ከዳር ቆመው እንደም ከማየታቸው ባሻገር እንደም በለ ማዩ ብልጭታ ሲመለከቱት ነበሩ። እዴላ ውኃውን በዋና ለመሻገር እጅና እግሩን ቢያወራጭም የጅረቱ ፍጥነት አይሎ ስለ ነበረ እጅና እግሩን በትክ ማንቀ

ባቀበ ሳይሆንለት ቀረ ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም ከባሻ ቅጣውና ከበጋሻው ዓይን ተሠወረ ። ውኃው ለማመን በሚያስቸግር ፍጥነት ይዞት ወረደ ። የውኃው ኃይል እንዳየለበት የተገነዘቡት ባሻ ቅጣውና በጋሻው ባሉበት ፈዝዘው ቀሩ ።

"ያራዳው ጊዮርጊስ ! ወሰደውኮ ፣ ባሻ ! ውኃው ወሰደው !" አለ በጋሻው ፣ ልቡ በደረቱ ውስጥ ድው ድው እያለበት ።

ባሻ ቅጣውም ጭንቅላቱን በእጁ ይዞ ፣ "አታድርገው ፈጣሪዬ! ይህንን እውነት አታድርገው !" እያለ ይማጸን ገባ ።

"ምን ማድረግ ይሻላል ፣ ባሻ ? በላውኮ ጅረቱ! በላው !" እያለ ጩኸቱን ለቀቀው በጋሻው ።

"አይደረግም ! አይደረግም ! " ሲል ጮኸ ባሻ ቅጣው ፣ በበኩሉ የተደረገውን በዓይኑ እያየ እንዳልተደረገ በመቍጠር ። "አዴላ ! አዴላ !" ሲል ተጣራ ቀጠል አድርጎ ። መልስ ግን አላገኘም ። በአዴላ ድምፅ ፈንታ የወራጁ ውኃ ጉርምርምታ የውሽንፍሩ ግርፍታ ነበር የሚሰማ ።

"ምን ማድረግ ይሻላል ፣ ባሻ ? ምን ማድረግ ይሻላል ? " ሲል ጮኸ በጋሻው እንደገና ጉሮሮውን አንቅ አንቅ እያደረገው ።

"ጊዜያችንን አጣምረን እዚህ ብንቆይ ዋጋ የለውም ። ጉዟችንን እንቀጥል " አለው ባሻ ቅጣው ።

ሌሊቱን ሙሉ የጅረቱን ግራ ዳርቻ ይዘው ሲጓዙ አደሩ ። አዴላ ከአንድ ሥፍራ ላይ አለት ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ አግኝቶ ይኸንኑ የሙጥኝ ብሎ እናገኘዋለን



የሚል ተስፋ ነበራቸው ። ይሁን እንጂ የሌሊቱ ጭለማ እየከበደ በመሄዱና የእየሩም ርጥበት ችቦ አላስበራ ብሏቸው ስለ ነበረ አዴላ የሙጥኝ የሚለውን ቢያገኝ ኖሮ እንኳ ሊያዩት ባልቻሉም ነበር ።

ሊነጋጋ ሲል የጦር ባልደረባቸውን መልሰው የማግኘት ተስፋቸው እየመነመነ ሄደ ። እነሱም በጉዞው ተዳክመው አድረው ስለ ነበረ ከአንድ ሠዋራ ቦታ ሲደርሱ እንቅልፍ አሸለባቸው ። ከወደቁበት ሳይነሡ መሸ ። እንደ ነቁም በኪሳቸው ተርፏቸው የነበረውን የሽንብራ አሸት እየበሉ የአዲስ አበባ ጉዟቸውን ተያያዙት ።

አዴላ ከዚያ ሁሉ የጠላት ቦምብና ቃጠሎ ፣ ከዚያ ሁሉ መድፍና መትረየስ ከዚያ ሁሉ መርዝና የሰላቢዎች ስለት ተርፎ መጥቶ ወራጅ ውኃ ወስዶት መቅረቱ እጅግ በጣም አስደነቃቸው !

"አዬ ጉድ ! አዬ ጉድ !" አለ በጋሻው አፉን በእጁ ይዞ ።

"የሰው መውደቂያው አይታወቅም !" አለ ባሻ ቅጣው በበኩሉ ፣ "በዚህ እሞታለሁ...በዚያ እሞታለሁ ብሎ መጨነቅ እንዲያው ከንቱ...! "

"ባይሆን እንኳ እቤቱ ደርሶ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ተቀላቅሎ ቢሆን ኖሮ እንዴት በተሻለ ነበር !"

"ለሞት መች ቀጠሮ አለው!"

ባሻ ቅጣውና በጋሻው እንደ ወትሯቸው ቀን ቀን እየተኙ ሌሊት ሌሊት እየተጓዙ ሰነበቱና ከእንጦጦ አፋፍ ላይ ሲደርሱ ስለ አዲስ አበባ ወሬ ለመጠየቅ ከአላና ቤት ጉራ አሉ ።

፱

አላና ፣ የድንቄ እንት ፣ በሃምሳና በስድሳ ዓመት ዕድሜ መሐከል ያሉ ፣ ፊተ ሰፊ ፣ ግምባራቸው የተሸበሸበ ፣ እንገታቸው ሐረግ በመሳሰለ ሥራ ሥር የተተበተበ ፣ ዕድሜ ልካቸውን ከተፈጥሮ ጋር ሲታገሉ የኖሩና በዚህ ምክንያት መላ ሰውነታቸው እንደ ጠፍር ብርቱ የሆነ ፣ በአዲስ አበባና በገጠር መሐከል ስለሚኖሩም ከፊል ከተሜ ከፊል ገጠሬ የሆኑ ፣ በጊዜው አነጋገር “የእግዜር ሰው” የሚባሉ ፣ የዋህ አዛውንት ነበሩ ። ከባለቤታቸው ከወርቂቱ ጋር ከሠላሳ ዓመት በላይ በፍቅር ቢኖሩም ፣ የልጅ ጸጋ ያልታደሉ ስለ ነበረ አንዱን የሙት ልጅ አሳድገው እንደ ወለዱት ልጃቸው ይንከባከቡት ነበር ።

ወርቂቱም ልበ ቅን ሴት ነበሩ ፣ ዓይናቸው እንባ ሳይቋጥር ዘወትር እንባ የቋጠረ የሚመስል ፣ ርኅሩኅና ሰው ወዳድ የቤት እመቤት ።

ባሻ ቅጣውና ቢጋሻው ጎጆው ውስጥ እንደ ገቡ ከአላናና ከባለቤታቸው ጋር ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳሙ ፣ ደገመው ደጋገመው ። ፍቅር የመላበት የሞቀ የቃል ሰላምታም ተለዋወጡ ።

“እስቲ ዐረፍ በሉ…ደርታችሁ የለም እንዴ !”

“ኧረ ደህና ነን ! መከሳት ደሞ ይነሰን ! እናንተስ እንዴት ናችሁ ፣ አብዩ አላና ? ”

“ክብሩ ይስፋ…ምን ጠፍቶ ! ምን ታጥቶ ! ሰሙ ሆኑ በሕይወት አላችሁ ? ” ብለው ፊታቸውን ወደ ባለቤታቸው አዞረው ፣ “ኧረ ፈጠን በይ ወርቂቱ ! እጥንትና



ቆዳ ብቻ ኮ ነው የቀራቸው ። እስቲ ፈጠን ብለሽ ምናምን አቅርቢላቸው ።»

«ውይ! እኔ አፈር ልብላላችሁ!» ብለው ከንፈራቸውን መጥጠው ከጎጆአቸው ውጭ ወደ ነበረ ማድ ቤት አመሩ—ወርቂቱ ።

«ከተማው እንዴት ነው ፣ አብዩ አላና?»

«እስቲ መጀመሪያ ትንሽ ዐረፍ በሉና ፣ እህልና ውኃ ቀማምሱና ከዚያ በኋላ ብንጫወት ይሻላል ።»

«እያረፍን እንጫወት የሚከለክለን ምን አለ ፣ አብዩ አላና ?»

«አይ እንዲያው…! ደስ የሚል ጨዋታ ቢኖር እንኳ ባልከፋ ፣ባሻ ።»

«ምነው ? ጣሊያኖች ከተማ ገቡ እንዴ ?»

«እስካሁን እንኳ አልዘለቁም ። ብቻ ሩቅ አይደሉም ይባላል ። ግምባር ጦራቸው እዚህ ሰንዳፋ ደርሷል ስለሚባል በዛሬና በነገ ከተማውን ሳይዙ አይቀሩም ይባላል ።»

«የከተማውስ ሁኔታ እንዴት ነው ?»

«ኧረ ባይወራ ይሻላል !»

«ምነው ? ክፉ ነገር ደርሷል ?»

«መንግሥት በሌለበት አገር ክፉ ነገር ደርሷል ወይ ተብሎ ይጠየቃል?» አሉና ፣ «ትናንትና ለጉዳይ ከተማ ወርጄ ነበር ። አራዳ አካባቢ እንኳ ደህና ነበር ፣ወደ ራስ መኮንን ድልድይ የሚወስደው መንገድ ግን…» ብለው ተክዘው አሉና፣

«በዚያ አካባቢ ያሉ ቤቶች አብዛኛዎቹ

ኃይተዋል ፡መላ ከተማው ዝርፊያ ብቻ ሆኗል ። እዚህም እዚያም ዝርፊያ…ብያለበት ሁሉ ዝርፊያ…» ብለው ምራቃቸውን ዋጥ ዋጥ አደረጉና፡-

«ዘራፊዎቹ ከየሱቁና ከየቤቱ የዘረፉትን ዕቃ…ምንጣፍ ፡ ብርድ ልብስ ፡ ሸሚዝ ፡ ካፖርት፡ ሱሪ ፡ ብር ፡ ወርቅ ምኑ ተዘርዝሮ ያልቃል !ይህንን የመሰለውን ሁሉ ዘርፈው ሲሯሯጡ ነበሩ። መላ አካባቢው ግርግር ላይ ነበር ። ለነገሩ እንግዳ ሆኜ ከአንድ ቦታ ቆሜ ሳስተውል ሳለሁ ሁለት ሰዎች ሲጨቃጨቁ ሰማሁ ። ሁለቱም ሞቅ ብሏቸው ነበር ። ቀደም ብለው ከአንድ ፈረንጅ ሱቅ ገብተው መጠጥ ዘርፈው የጠርሙሶቹን አንገት ሰብረው እስኪበቃቸው ድረስ ጠጥተው ኖሯል ! የጥሉ መነሻ ምን ይሆን ብዬ ብጠይቅ ሰዎቹ የተጣሉት በዘረፉት ዕቃ ምክንያት ነው ሲል ነገረኝ — በአጠገቤ የነበረ አንድ ጐበዝ ። ከዚያም በኋላ አንደኛው የዘረፉትን ብርድ ልብስ ጫፍ ይዞ ለኔ ይገባኛል ብሎ ሲጎትት ፡ ሁለተኛውም የብርድ ልብሱን ሌላ ጫፍ ይዞ ለኔ ይገባኛል ብሎ ሲጎትት ብርድ ልብሱ ለሁለቱም ሳይሆን በመካከላቸው ብጥስጥሱ ወጣ ። ከዚያም በኋላ ሰዎቹ አንገት ለአንገት ተያይዘው መናረት ጀመሩ ። በሌላ ሰው ንብረት ! ይህንን ጉድ ካየሁ በኋላ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ብዬ አማትቤ ወደ ጎጀዬ ጉዞ ጀመርኩ እላችኋለሁ !» አሉ ።

«ከተማው ውስጥ ሥርዓት ጠፍቷል !» አለ ፡ ባሻ ቅጣው ።

«የምን ሥርዓት ? ጃንሆይ አገር ለቅቀው ከወጡ በኋላ…»



ባሻ ቅጣው ደንገጥ ብሎ «አገር ለቅቀው ከወጡ በኋላ !» ሲል አቋረጣቸው ።

«መጀመሪያ ነገር መች ተመለሱ ?» አለ በጋሻው በበኩሉ ።

«እረ! አልሰማችሁማ !?»

«ገና መድረሳችንኮ ነው ፡ አብዬ እላና ።»

«እንግዲያውስ እህል ውኃ ከቀማመሳችሁ በኋላ ባጫውታችሁ ይሻላል» ብለው ፡ «ወርቂቱ…! ወርቂቱ…!» እያሉ ተጣሩ ።

«መጣሁ!» አሉ ወርቂቱ ከማድ ቤታቸው ሆነው ።

ወዲያውኑ የሚያሳድጉት ልጃቸው የእጅ ማስታጠቢያ ይዞ ገባ ።

«ይንገሩን ግድ የለም ። ይንገሩን» አለ ባሻ ቅጣው ፡ እጁን መታጠብ ሲጀምር ።

«እሳቸውማ የተመለሱት ከጥቂት ቀናት በፊት ነበር» አሉ አላና ፡ ያቋረጡትን ጨዋታ በመቀጠል ! «እና ፡ የሚያማክሩትን አማክረው ፡ የሚፈጽሙትን ፈጽመው በባቡር ተሳፍረው ሾለኩ አሉ ።»

«ወደ ውጭ አገር ለመሄድ ?»

«አዎን ።»

«እንዴት ተደርጎ ?»

«እኔ ምን አውቃለሁ ፡ ባሻ! የሰማሁትን ነው የምነግራችሁ ።»

«በጄ…!»

«እና ፡ አሁን እንዳልሁት የሚያማክሩትን አማክረው ፡ የሚፈጽሙትን ፈጽመው ሲያበቁ ፡ ከትናንት ወዲያ ጨለማ ለብሰው በሐረርጌ ባቡር

ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ አሉ… እና ፣ ከዚያ በኋላ በከተማው ውስጥ ቅልጥ ያለ ዝርፊያና ሽብር ትንግ እላችኋለሁ ። ይኸ ሁሉ ሲሆን እኔ ምንንም አልሰማሁም ። የአዲስ አበባ ሕዝብ ግን ወሬውን ወዲያው እንደ ሰማ ጆሮውን ሊያምን አልቻለም» ሲሉ ፣ ወርቂቱ ያዘጋጁትን የሚቀመስ ነገር ይዘው ገቡ ። ሙክክ ብሎ የበሰለ የጥቦት ሥጋ… ቀይ ወጥ… አልጫ… ድስቶቹን ከፊት ከፊት ሲያደርጓቸው መላ ጎጆው ምራቅ በሚያስውጥ መዓዛ ተሞላ ።

«በሉ እስቲ ያዙ… እኔ እፈር ልብላ… ! ያን ያህል ወራት ከዘመድ አዝማድ ተለይታችሁ ፣ እዚያ ወዲያ ጦር ግምባር… በሉኮ ያዙ…ፈራ ችሁት እንዴ ?» አሉ ወርቂቱ ።

«እስከዚህም አይጨነቁ ፣ እማማ ወርቂቱ » አሏቸው ባሻ ቅጣው ፣ «እንምረውም ! አይጨነቁ ።»

«እንዲያው እፈር ይብላኝና… ! በሉ እስቲ ቀማምሱት» ብለው ከቅቅሉም ፣ ከቀይ ወጡም ከአልጫውም ፣ እንጀራም እያነሡ ከፊት ፊታቸው ይደረድሩላቸው ገቡ ።

«እስቲ የሚጠጣ አምጪላቸው» አሉና ፣ አላና «እርጎ ይሁንላችሁ ወይንስ ትኩስ ወተት ?» ሲሉ ጠየቋቸው ። ባሻ ቅጣው እርጎ መረጠ ! በጋሻው ትኩስ ወተት ።

«አብራችሁን ብትበሉ ግን እንዴት ደስ ባለን ! » አለ ባሻ ቅጣው ።

«እዬ ባሻ ! ደሞ ብለህ ብለህ ለኛ ተጨነቅህ ! በሉ እስቲ ጉረስ ጉረስ አድርጉት ።»



"እየበላን ነን ፣ እብዬ እላና" አለና ባሻ ቅጣው "ስለ ከተማው ያወሩልን የነበረውን ግን አልጨረሱልንም" አሏቸው ።

"ዝርፊያውና ግርግሩ እየቀጠለ ነው ። ግቢ እንኳን ከመዘረፍ አልዳነም ።"

"እ… ? ግቢ ? "

"አዎ ። ግቢም አልተረፈ ። የመሣሪያው ቀሻ ተዘረፈ አሉ ።"

"ጦር ግምባር ያልሄዱትና ከተማውን እንዲጠብቁ እዚህ የቀሩት የአራዳ ዘበኞች ወዴት ሄደው ?"

"ግቢውን የዘረፈው ማን ሆነና ! በግቢው ቀሻ ውስጥ የነበረውን መሣሪያ የዘረፉት እነሱ ናቸው ፣ ባሻ ።"

"እንዴት ? "

"ጫካ ገብተን ትግሉን እንቀጥላለን ይላሉ አሉ ። ባላምባራስ አበበ ፣ የአራዳ ዘበኞች አዛዥ ፣ ትናንትና ወጡ አሉ ።"

"እንዲህ ይበሉን እንጂ ! " አለ ባሻ ቅጣው ፣ ደስ ብሎት ፤ "ጫካ ለመግባት ከሆነ ሐሳባቸው ድርጊታቸው ዝርፊያ ሊባል አይገባም ። አርበኝነት መጀመራቸው ነው" ብሎ ከመጋበዝ ገታ አለ ።

"ምነው ? ብሉ እንጂ" ብለው ወርቂቱ እጃቸው ያነሡላቸውን ያህል አንሥተው ወደ ባሻ ቅጣው አፍ መሩትና "በሞቴ…እፈር ስሆን…ይህቺን ብቻ" አሉት ። አላሳፈረቻቸውም ። አፉን ከፍቶ ተቀበላቸው ። ቀጥለውም ወደ በጋሻው ዞረው ያንኑ ያህል አንሥተው አጉ

ረሱት ፣ እንደ በሬቱ "በሞቴ…አፈር ስሆን…ይቺን
ብቻ" እያሉ ።

"እርጎና ወተትም ጨምሬላቸው" አሉ አላና ።
ወርቂቱም ጉርሻውን ደጋግሙአቸውና እርጎና ወተት
በድጋሚ ለማምጣት ጉድጉድ ማለታቸውን ቀጠሉ ።

አላናና ወርቂቱ ሀብታም አልነበሩም ። ነገር ግን
ጎጆአቸውን አሸንፈው በግብርና ሥራ በሰላምና በርጋታ
የሚኖሩ ነበሩ ። በቂ የእርሻ መሬት ነበራቸው ። በርከት
ያሉ ጥገቶችና የእርሻ በሬዎችም ነበሯቸው ። በዓመት
አንድ ጊዜ የሚለብሱትን ከመግዛት በስተቀር ማንኛውም
ለኑሮ አስፈላጊ የሆነ ነገር ሁሉ በማጀታቸውና በበረ
ታቸው ፣ በጐተራቸውና በጓሯቸው ነበራቸው ፣ እህል…
…ወተት… ቅቤ… አይብ… ቅጠላ… ቅጠል…የማገዶ እን
ጨት…

ዘመድ አዝማድ ሊጠይቃቸው ሲመጣ ብቻ ሳይሆን
ተላላፊ መንገደኛ ሲያገኙ እንኳ ጥሩ መስተንግዶ ያደ
ርጉለት ነበር ።

አንዳንድ ጊዜ የከተማ ወጣቶች ለሽርሽርና ጉል
በታቸውን ለመፈተሽ ከከተማ ተነሥተው በእግራቸው
ወደ እንጦጦ ይወጡ ነበር ። እዚያ በሚወጡበት ሰዓት
በድንገት አላና ሲያገኟቸው ፣ "ኑ ልጆቼ…ጠላ ጠጥታ
ችሁ ትወርዳላችሁ" እያሉ ይጋብዟቸው ነበር ። እንዳ
ሉትም ግብዣው ጠላ የሚሆንበት ጊዜ ነበር ። እርጎ
ወይም ትኩስ ወተት የሚሆንበት ጊዜም ነበር ።
ከዚህም አልፎ ሙሉ ምግብ የሚቀርብበት ጊዜም
ነበር ። ከተሜዎቹ ወጣቶች በግብዣው ደስ ይላቸው
ነበር ። ነገር ግን አንዳንዶቹን ያ ሁሉ ግብዣ በብላሽ
መሆኑ የሚያጠራጥራቸው ጊዜም ነበር ።



አንድ ቀን አንድ የከተማ ወጣት እንዲሁ ጠግቦ
በልቶ ጠግቦ ጠጥቶ ሲነሣ ፣ "ይቅርታ ያድርጉልኝ አባባ ።
ጎጆአችሁን አራቁቼ እንዲሁ አልሄድም" ብሎ ኪሱን
ሲደባብስ አላና አዩትና ፣ "እንዲህ ያለ ነገር ከተማ
ውስጥ ይደረግ ይሆናል ልጄ ፣ እዚህ ግን ነውር ነው"
አሉት ።

ወጣቱ አላናን ቅር በማሰኘቱ በጣም አዝኖ ይቅ
ርታ እንዲያደርጉለት ለመናቸው ።

"ግድ የለም…ይቅርታ አድርጌልሃለሁ" አሉት አላና፣
"የከተማችሁን ባህል በጥቂቱም ቢሆን ሳላውቀው አል
ቀረሁም" ብለው ፈገግ አሉለት ።

የእንጦጦዎቹ ባልና ሚስት በሚያውቋቸው ሰዎች
ዘንድ ሁሉ የተወደዱ በመሆናቸው አላናን ፣ "አብዬ"
ወርቂቱን ፣ "እማማ" የማይላቸው አልነበረም ።

፲

በልተው ፣ ጠጥተው ፣ ዐርፈው ፣ ተጫውተው ፣
አላናንና ወርቂቱን ተሰናብተው ወጡ—ባሻ ቅጣውና
በጋሻው ። ጊዜው መሽትሽት ብሏል ። የምዕራብ አድ
ማስ ፣ ነፋስ ዝግ ብሎ የሚያንቀሳቅሰው ባሕር መስ
ሏል ። በቀለማቀለማትም አሸብርቋል ። ጀምበር ልጥ
ለቅ አልጥለቅ በማለት እያመናመነች በምድርና በሰ
ማይ መጋጠሚያ ከንፈር ላይ የወርቅ አሉሉ መስላ ተን

ጠልጥላለች ። የዛፍ ጥላዎች እርስ በርሳቸው ተጠላለፈው በንጭና በጥቁር ሱፍ የተሠሩ ሥጋጃዎች መስለው ምድሩን አልብሰውታል ።

ባሻ ቅጣውና በጋሻው ጉልበታቸውን እጥፍ ዘርጋ እያደረጉ የእንጦጦን ቁልቁለት ሲወርዱ ሳሉ ፣ "ምነው ዝም አልክ ባሻ ?" ሲል ጠየቀው በጋሻው ።

"እኔ እንጃ...ቁንጣን ተጫጭኖኛል መሰለኝ ።"

"እንዲያነው እንጂ ምግብ ! በተለይ ቅቅሉ ! እንዲያው ሳይነኩት በገዛ ራሱ ከአጥንቱ ተለይቶ የሚወድቅ...!"

"እማማ ወርቂቱ ሰው በልቶ የሚጠግብ አይመስላቸውም ። ጉርሻቸው ነው ቁንጣን ያስያዘኝ ።"

"እረ ለመሆኑ ምን አሰብክ ፣ ባሻ ?"

"ስለ ምኑ ?"

"ስለ ወደ ፊቱ ነዋ ! ይኸው ከሞቀ ቤታችን ልንደርስ ነን ። እና ፣ ምን ለማድረግ አሰብክ ?"

"ቀድመህ ያንተን ብትነግረኝ አይሻልም ?"

"እኔማ ጊዜው እንደ ፈቀደው መኖር እንጂ ሌላ ምን አደርጋለሁ ! ጦርነቱ እንደሁ አብቅቷል ።"

"ጦርነቱ አላበቃም ! አላበቃም !"

"እውነቱን መካድ ለምን ይጠቅማል ፣ ባሻ ? ፋሺስቶቹን አልቻልናቸውም ። ጃንሆይም አገር ለቅቀው የሄዱት ይኸንኑ አምነው መሆን አለበት ።"

"ምን አስበው አገር ለቅቀው እንደ ሄዱ ገና እናውቅም ።"



"አብዬ አላና ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ አላሉንም ? ወደ ኢየሩሳሌም ከሄዱ በግዞት ለመኖር እንጂ ሌላ ለምን ሊሆን ይችላል ?"

"በአገራችን ታሪክ ውስጥ እንዲህ ያለ ነገር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም ። ታሪካችን እንደሚያረጋግጠው የኢትዮጵያን መሪ የሚያሸንፈው ሞት ብቻ ነው ። አፄ ቴዎድሮስ ጥይት ጠጥተው ሞቱ—በጠላት ከተሸነፉ በኋላ ። አፄ ዮሐንስ ጦር ሜዳ ላይ ወደቁ—ከደርቡሾች ጋር ሲፋለሙ ሳሉ ። ሌሎችም እንዲሁ እስኪሸነፉ ወይም እስኪያሸንፉ ድረስ ከመታገል በስተቀር በሕይወታቸው እያሉ የመሸነፍን ውርደት ተቀበሉ ሲባል ሰምተን አናውቅም ።"

"መሞትና ከአገር መሰደድ ምን ልዩነት አለው ብለህ ፣ ባሻ !"

"ልዩነት አለው ፣ ቀውሉ ። ጃንሆይ አገር ለቅቀው ቢወጡም ለምን እንደ ተሰደዱ እውነተኛውን ምክንያት ማወቅ አለብን ። ጦርነቱ ግን አብቅቷል እኛም ለዘለቄታው ተሸንፈናል ለማለት ከቶም አይቻልም ። በዚያ ላይ ከጦር ግምባር ወደ ቀዬአቸው ሳይመለሱ በረሃ የገቡት ጦርነቱን እንደሚቀጥሉ አትጠራጠር ። ወደ ቀዬአቸው ከተመለሱትም መሐከል ብዙዎቹ ተመልሰው ጫካ እንደሚገቡ አትዘንጋ !"

"እውነት ጫካ ለመግባት አሰብክ ፣ ባሻ ?"

"ያውም ባስቸኳይ ነዋ ! ወደዚህ የመጣሁት ለዝግጅት እንጂ ተዘናንቼ ለመኖር አይደለም ። ተዘናንቼ ልኑር የሚል ቢኖርስ ከአሁን ወዲያ ማን ያዘናናዋል ?"

በጋሻው ለአጭር ጊዜ ተከዝ አለና ፣ "እንግዲያውስ አልለይህም ፣ ባሻ" አለው ።

"ለመውጣት ከቆረጥህ ዝግጅትህን አፋጥን ። ብዙ ጊዜ የለንም" ብሎት እስከ መለያያቸው ድረስ በዝምታ ተጓዙ ። የበጋሻው ቤት ከባቡር ጣቢያ አጠገብ ስለ ነበረ የአንድ ሰዓት ያህል መንገድ ቀርቶት ነበር ። ባሻ ቅጣው ግን እቤቱ ለመድረስ አሥር ደቂቃ የሚያስኬድ መንገድ እንኳ አልቀረውም ነበር ።

"መቼ እንገናኝ ታዲያ ?"

"ምነው...? እቤት ጐራ አትልም ? "

"ባለቤቴና ልጆቼ ናፍቀውኛል ፣ ባሻ ። መንገዱን ብቀጥል ይሻለኛል ። "

"እንግዲያውስ ነገ ከነገ ወዲያ እንገናኝ ። ለአንተ እንደ ተመቸህ..."

ተጨባብጠው ወደየቤታቸው አቅጣጫ አመሩ ።



## ፲፩

"ምስጋና ይግባህ !" አለች ድንቂ ዓይኗን ወደ ሰማይ አቅንታ ፣ ባሻ ቅጣውን ገና በሩቅ ስታየው ። "ምንጊዜ የማይረሳንህ አንተ ምስጋና ይግባህ !"

ባሻ ቅጣው ለዘመቻ የሄደ ዕለት ለአራዳው ጊዮርጊስ ተስላ ነበር—ባሻ ቅጣው በሕይወት ከተመለሰ ለጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጧፍ ገዝታ ልታገባ ፣ እሱ በሕይወት ከመመለሱም አልፎ ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸናፊ ከሆነች እጧና ባሻ ቅጣው ድልብ በሬ ገዝተው ለአራዳው ጊዮርጊስ ለመስጠት ። ኢትዮጵያ በጦርነቱ አሸናፊ አልሆነችም ። ነገር ግን ባሻ ቅጣው በሕይወት ስለ ተመለሰ ጸሎቷ በከፊልም ቢሆን እንደ ደረሰላት በመቍጠር ነው ፣ "ምስጋና ይግባህ !" ያለችው ።

ባሻ ቅጣው ገና ወንበር ሰበ ከመቀመጡ ፣ "ምነው እስከዚህ ጨከንክብን ፣ ባሻ ?" ስትል ጠየቀችው ።

"የምን ጭካኔ ነው ደሞ ?"

"ወደዚህ የሚመጣ አንድ እንኳ ወሬ ነጋሪ አጥተህ ነው በሕይወት መኖርህን ሳትልክብን የቀረኸው? ልባችን ተሰቅሎ ነው የከረመው ፣ ባሻ" አለችና ዓይኗን ወደ ልጅዋ በማዞር ፣ "ዓለምዬ...እስቲ ና ወዲህ ። አባትህን አላወቅኸውም ?" ስትል ጠየቀችው ።

ዓለሜ አባቱን አተኩሮ ተመለከተው ። እሱነቱ ሲከሰትለት ሮጦ ሄዶ አንገቱ ላይ ተጠመጠመበት ።

"አንተ ዱዳ ! መናገር ቻልክ ወይንስ ያው ነህ ?" አለው ባሻ ቅጣው ። ዓለሜ እንደ ተለመደው ተኰላተፈለት ።

"ሽዋርካብሽስ እንዴት ነች ?"

"ደህና ነች ። ያቻትና አልጋው ላይ ። ጉንጮችዋ ብስል ቲማቲም መስለዋል ። ሄደህ እያት ፣ ባሻ ። ወይንስ እንሥቼ ላምጣልህ ?"

"አምጪአት ።"

ድንቂ ግርዶሹን አልፋ ሽዋርካብሽን ታቅፋ ይዛ መጣች ። ከፊቷ በስተቀር መላ ሰውነቷ በማይሞቅ ነጠላ ተጠቅልሎ ነበር ። ባሻ ቅጣው ሕፃኗን ተቀብሎ

ባስም ፣ ግቱን እያሸመሸ፤ አሟወታትና ፣ “እውነትም ጉንጮቿ የበሰለ ቲማቲም መስለዋል ! አንቺ ግን ከስ ተሻል ። ያጋጠመሽ ችግር ኖሯል ?” አላት ።

“ምንም ችግር አላጋጠመኝም ፣ ባሻ ። ስላንተ ወሬ ሳንሰማ በመቅረታችን ተጨንቀን ነበር እንጂ…”አለ ችና ፣ “ልጆቹ የት አሉ ለመሆኑ ? በቅሎህስ ? አህዮቹስ?” ስትል ጠየቀችው ።

“ሠርግ ቤት ደርሼ የምመለስ መሰለሽ እንዴ ?” ብሎ ነገሩ ከንክኖት ግቅ አለ ።

“ከምን ደረሱ ፣ እውነት ? ”

ጥያቄዋ ረስቶት የነበረውን ሁሉ ቀሰቀሰበት ። ሐሳቡም በቅጽበት ከጦር ግንባር ተመልሶ ሄዶ የሆነውን ሁሉ በዓይነ ሕሊናው ያይ ጀመር ። የቦምቡ ፍንዳታ…የመድፉ የመትረዬሱ ግምግምታ…ቃጠሎው… መርዙ…

“በቅሎዬ ሜዳ ላይ ግር ሲግጥ የመርዝ ጠብታ ነክቶት ተቃጥሎ ሞተ…አረሩና አህዮቹ በቦምብ አደጋ ሞቱ…”

“አረሩ ሞተ ! ?” አለች ደንግጣ ።

“እምን ሞቷል” አላት ፣ አሟሟቱ በዓይነ ሕሊናው እየታየው ።

“ተመስገንስ ? እሱም ሞቷል ? ”

“ተመስገን ከእኛ ተለይቶ ሄዶ የደረሰበት አልታወቀም…በሕይወት እንዳለ ግን ተሰፋ አለኝ ” አላት ።

“እንዴ…? እንዴ… ? አንተም ተመትተህ ኖሯል፣ ባሻ ? ወይንስ ያ የሚታየኝ ነጭ ጨርቅ ምንድነው ?”



በእርግጥም ከተበጣጠቀው ኮቱ እጅጌ ሥር የተጠመጠመ ጨርቅ ይታይ ነበር ።

“ከአንድ ቦታ ብቻ አይደለም የተመታሁት ደንቄ። ብቻ…ስለ ጦርነቱ ለማውራት አልፈልግም ። አንቺ ሕፃኗን ወስደሽ አስተኛትና ይኸንን ብረት አንስተሽ ግርግዳው ላይ ስቀዪው…ዝናሩንም ጭምር ። ”

“ውኃ አሙቂ ቁስልህን ልጠብልህ ! ”

“የምን ቁስል ? ገና ዱሮ የሻረውን ! ልብሳችንን ቀንም ሆነ ማታ አናወልቅ ስለ ነበረ ጨርቁን እዚሁ እተጠመጠመበት ተውሁት እንጂ ቁስሉ ከሻረ ውሎ አድሯል ፣ ደንቄ ። ጠባሳ እንጂ ቁስል የለብኝም ። ይልቁንስ የምታደርጊልኝ አለ ። ቶሎ ብለሽ ውኃ አሙቂልኝ ። ገላዬን መታጠብ አለብኝ… ተገማምቻለሁ ። ”

“እንግዲያውስ እስከዚያ ድረስ አረፍ በል ! ” ብላ ሕፃንዋን መስዳ አስተኝታ ውኃውን በቶሎ አሙቃ ለማድረስ ጉድ ጉድ ማለት ጀመረች ።

፲፪

ከታጠበ በኋላ ሰውነቱን ቀለል አለው ። ከሰባት ወር በላይ በሰውነቱ ላይ ተከማችቶ የነበረው ላቦትና ጭቅቅት ሲነሣለት ትልቅ ሸክም የወረደለት መሰለው ። ልብሶቹንም ቀይሮ ጋቢ ደርቦ ተዝናንቶ ቁጭ አለ ።

“እንዴት ነው የከረማችሁ ደንቄ ?” ሲል ጠየቃት።

"በሰላም ! ጦርነት መኖሩን ያወቅነው የጠላት አውሮጵላን እዚሀ አዲስ አበባ ድረስ እየመጣ ይርር በነበረበት ሰዓት ብቻ ነበር ።"

"እዚህም ዘልቆ ይበርር ኖሯል ? "

"አዎን ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ። ከመምጣቱ በፊት የማስጠንቀቂያ ቱልቱላ ይነፋ ነበር ። የቱልቱላ ድምፅ ስንሰማ ወደየዋሻውና ወደየሚካው እንድንገባ ተነግሮን ነበር ። ምልክቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁ ቀን የትም አልሄድም ብዬ ከልጆቼ ጋር እዚሁ ቆየሁ ። በሁለተኛው ቀን ግን አባተና ቸሩ ከሙሉ ጋር አብረው መጥተው አብረሽን ካልሄድሽ ብለው ወተወቱኝ ። እምቢ ብላቸውም አልለቅ አሉኝ ። እና ፣ እኔ ዓለሜን፣ ሙሉ ሽዋርካብሽን አዝለን ወደ ጋራው ወጥተን ዋሻ ውስጥ ተደበቅን ።"

"ማን ነች ሙሉ ? "

"ለኪስ አታውቃትም ፣ ባሻ ! የምታውቃት መስሎኝ...የአባተ እናት የእኅታቸው ልጅ ነች ፣ ቆንጆዬ... አንድ ቀን ቸሩ አከስቷ ዘንድ ያየትና እሷን ካላገባሁ ሞቼ እገኛለሁ አይልልህም ! "

"ልጃገረድ ነች ? "

"ኧረ እሷስ ባለባል ነች ። ላያት ግን ከልጃገረድ አትለይም ። ቆንጆዬ... ! "

"ታዲያ የሰው ሚስት ቀምቼ ካላገባሁ ነው የሚለው ? "

"አግብቷታል እንጂ ! "



"እንዴት በይ ? "

"ከቀድሞ ባሏ ጋር መፋታቱን አልተፋቱም ። ነገር ግን ጠልታው ነው ትታው አከስቷ ዘንድ ለመቀመጥ የመጣችው ። 'ይደበድበኝ ነበር' ትላለች ሙሉ ። ባሏ ቀናተኛ ኖሯል ! 'ከወንድ ጋር ስነጋገር ሲያይ አለዚያም ከወንድ ጋር ባልነጋገርም ዓይኔን ወደ ወንድ አዙሬ ሲያየኝ ቀንቶ ይደበድበኝ ነበር' ትላለች ሙሉ ። ቸሩ ታዲያ በአጋጣሚ አያትና እሷን ካላገባሁ ሞቼ እገኛለሁ አለ ። ተጋቡ ።"

"የቀድሞ ባሏስ ? "

"ምን ዐውቄ ፣ ባሻ ! "

"አዬ ጉድ ! እኒህ አውሮጳ ደርሰው የሚመጡት ወጣቶቻችን ሰው ምን ይለኛል ማለትን ትተዋል ! ብቻ አይገርመኝም " አለና ፣ "አባተስ እንዴት ነው ? እሱም አግብቷል ? " ሲል ጠየቃት ።

"አላገባም ። የተማረች ልጅ ካላገኘሁ በስተቀር አላገባም ይላል ። እንደሱ የተማረች ልጅ እስኪያገኝ ከጠበቀ ሳያገባ ማርጀቱ ነው ። ቸሩ ግን ለእንደዚህ ዓይነቱ ነገር ግድ የለውም" አለችና ፣ "እሱ...ቸሩ ነው ከእነሱ ጋር አብሬ እንድሄድ የወተወተኝ ። እና ፣ አብረን ሄደን ዋሻው ውስጥ ተደበቅን ። አውሮጵላኖቹ ከተማውን ዞረው ምንም አደጋ ሳይጥሉ ተመልሰው ሄዱ ። አደጋ ሳይጥሉ የሄዱት ከተማው ውስጥ ፈረንጆችም ጭምር ስለሚኖሩበት ነው አሉ ። የከተማው ሕዝብ ግን ያን ቀን ተረብሾ ዋለ ። ከአሁን አሁን አውሮጵላኖቹ ተመልሰው መጥተው አደጋ ይጥሉ ይሆናል ብሎ ፈርቶ ዋለ ሕዝቡ ሁሉ ። አባተ ወደ ጦር ግምባር እንዳይሄድ

መሥሪያ ቤቱ በላገደው ተበሳጨ—ያን ዕለት ። ቸሩም ፣ ‘ይህ ጉደሉ እግሬ ነው እንዳልዘምት እንቅፋት የሆነኝ ’ ብሎ ሁላችንንም አሳቀን” አለችና ፣ “አዬ የኔ ነገር ከመንገድ መግባትህን ረስቼ ቁጭ ብዬ መለፍለፍ ! ” ብላ ስትነሣ ምን ለማድረግ እንደ ፈለገች በማወቅ ፣ “ቁጭ በይ...ምንም አልፈልግም” አላት ፣ ባሻ ቅጣው ፤ “እኔና በጋሻው ስለ አዲስ አበባ ወሬ ለመጠየቅ አብዬ አላና ዘንድ ገብተን ነበር ። እማማ ወርቂቱ ለአሥር ሰው የሚበቃ ያህል ምግብ አዘጋጅተው አቅርበውልን ስለ ነበረ ጳቅ እስኪለን ድረስ በልተናል ። ”

“አብዬ አላና በሳምንት ሁለት ሦስት ቀን እየመጡ ይጠይቁን ነበር ። ትናንት እንኳ እዚህ ነበሩ ።”

“ነግሬሽ አልነበረም !” አላትና ፣ “እዚህ ብዙ እንቆይም ድንቄ ። ዕቃሽን ማዘጋጃጀት እንድትጀምሪ ። አብዬ አላና የነገሩን ወሬ እውነት ከሆነ ጣሊያኖች በዛሬና በነገው ቀን ከተማውን ሳይዙ አይቀሩም ። ጦር ግምባር የዘመትነውን የሚምሩን አይመስለኝም ። የሚምሩንስ ቢሆን ደሞ ማንነው ቁጭ ብሎ ለነሱ የሚገዛ!” አላት ።

“የት ነው የምንሄድ ? ”

“አገር ቤት ” አላትና ፣ “ዕቃሽን ፈጠን ብለሽ ማዘገጃጀት ጀምሪ ። እኔ የምሠራው ሌላ ሥራ ስላለኝ ላግዝሽ አልችልም ። ካስፈለገሽ የቀን ሠራተኛ ቀጥረሽ ያግዝሽ ። ”

“ለዘለቄታው ነው የምንሄድ ? ”

“ሳይሆን ይቀር ብለሽ ! ”

“እንግዲያው ያለንን ሁሉ ቅራቅምቦ ማጋዝ ሊኖርብን ነዋ ! ”



“አንዳችም ነገር ሳይቀር ! ወዳቂ ካልሆነ በስተቀር አንዳችም ጠቀሜታ ያለው ዕቃ ሳታስቀሪ ሰብስበሽ አስረሽ አዘጋጂ ። ”

በዚህ ጊዜ ከውጭ የሰው ኮቴ ሰሙ ። ማን ይሆን በማለት ሁለቱም ጨዋታቸውን አቋርጠው በዝምታ ሲያዳምጡ ፣ የአባተን ድምፅ የሰሙ መሰላቸው ።

በእርግጥም የሱ ድምፅ ነበረ ። አባተና ቸሩ ከእቴጌ ሆቴል ውጭ ቆመው ስለ ከተማው ሁኔታ ሲያወሩ ሳሉ በጋሻውን በዚያ ሲያልፍ አዩት ። “እንኳን በደህና ተመለስክ” ካሉት በኋላ የባሻ ቅጣውን መመለስ ነገራቸው ። ወደ ባሻ ቅጣው ቤት ከመምጣታቸውም በፊት መጠጥ ለመግዛት ሲንከራተቱ ቆዩ ። በረብሻው ምክንያት የመጠጥ መደብሮች ተቃጥለው ስለ ነበረና ያልተቃጠሉትም ዝርፊያውን በመፍራት በራቸውን ዘግተው ስለ ነበረ የፈለጉትን መጠጥ በቀላሉ ለማግኘት አልቻሉም ። በመጨረሻ ግን ከአንድ ሰዋራ ሥፍራ አንድ ከፍት መደብር አግኝተው ሁለት ጠርሙስ አልኮል ገዝተው መጡ ።

## ፲፫

አባተና ቸሩ ገና ከመግባታቸው ፣ “ሙሉስ የት አለች ? ” ሲል ጠየቃቸው ፣ ባሻ ቅጣው ። ቸሩ ደንገጥ ብሎ ፣ “ሙሉ ? ሙሉን የት ታውቃታለህ ፣ ባሻ ? ” አለውና ፣ “ሽሽ ! ሽሽ ! አሁን ገባኝ ! ” አለው ዓይኑን ወደ ድንቄ አዙሮ ።

"አዎን ፣ እሷ ነች የነገረችኝ " አለና ባሻ ቅጣው ፣ "እስቲ ድንቄ...እስቲ መለኪያ አምጪልን ። ቸሩ ሠርግ ስላላበላኝ ሊከሰኝ አስቦ ነው መሰለኝ ጠርሙስ ይዞ የመጣው " ብሉ ሣቀ ።

"እንኳን ደህና ገባህ ፣ ባሻ ። እኔና አባተ እንዲያው ተጨንቀን ነበር...ሞራልህ ወድቆ መንፈስህ ተሰብሮ በስጥትጥት ብለህ እናገኝሃለን ብለን ፈርተን ነበር ። "

"ለምን በል ? "

"በጦርነቱ ውጤት ምክንያት ነዋ ፣ ባሻ ! ደሞም እልሰማህ ይሆናል እንጂ ጃንሆይኮ አገር ለቅቀው ወጥተዋል ። "

"አብዬ አላና እንዲህ ብለው ነገሩን ። እውነት ወደ ኢየሩሳሌም ነው የሄዱት ? "

"በኢየሩሳሌም ያልፋሉ እንጂ የመጨረሻ ግባቸው ኢየሩሳሌም አይደለም ። ወደ ጀኔቫ ነው የሚያመሩት ።"

"እና ፣ እሳቸው በሌሉበት አገሪቷን የሚመራት ማን ነው ? "

አባተና ቸሩ በባሻ ቅጣው ጥያቄ ደንገርገር ብለው ዓይን ለዓይን ተያዩ ። ከዚያም በኋላ ቸሩ ዓይኑን ወደ ባሻ አዞሮ ፣ "ጦርነቱ አብቅቷል ፣ ባሻ ። አይደለም እንዴ ? ከአሁን ወዲያ አገሪቷን የሚመሩት...አገሪቱን የሚነዱት ብል ይሻላል መሰለኝ...አዎን ፣ ከአሁን ወዲያ አገሪቱን እንደ ከብት የሚነዱት ፋሺስቶች ናቸው ! " አለው ።

"ሰው ሁሉ ጦርነቱ አብቅቷል ብሎ ሲያወራ ይገርመኛል" አለ ባሻ ቅጣው ፣ ጦርነቱ ግን ገና አላለቀም ።



ሶልዳቶዎች አንዳንድ ከተሞችን ይዘዋል ። ሌሎች ከተሞችንም መያዛቸው አይቀርም ። ነገር ግን ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ነች ። ጦርነቱ በየገጠሩ መቀጠሉ አይቀርም ። ለኔ ግልጽ ያልሆነልኝና እናንተም እንድታብራሩልኝ የምፈልገው ጃንሆይ አገር ለቀው ሲሄዱ ምን ትዕዛዝ ሰጡ ? ይህንን ሳትሰሙ አትቀሩም ፤ በተለይ አንተ አባተ...»

«እሱ ምን ያረጋል ፣ ባሻ ? ቁም ነገሩ ከሱ ላይ አይደለም ።»

«ቁም ነገሩ ከምኑ ላይ ነው ታዲያ ?»

«አገር ጥለው ወደ ጀኔቭ ከመሄዳቸው ላይ ነዋ ?»

«እና ፣ ምን ምን ውጤት ያለው ይመስልሃል ?»

«አየህ ባሻ... የዓለም መንግሥታት ማኅበር የማይሰማ የማይለማ ድርጅት ነው ። ድርጅቱ የማይሰማ የማይለማ ባይሆን ኖሮ ሆርና ላቫል—የእንግሊዝና የፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች— ከድርጅቱ ውጭ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ መሐከል የተነሣውን ጠብ ለማብረድ በሚል ሰበብ ኢትዮጵያ ከግዛቷ ቆርሳ ለኢጣሊያ እንድትሰጥ ሐሳብ ባላቀረቡም ነበር ። ከዚህም በስተቀር ድርጅቱ ራሱ በኢትዮጵያና በኢጣሊያ ላይ እኩል የኢኮኖሚ እገዳ ማድረጉ ደካማ ጎኑን ነው የሚገልጸው.... ።

«እ————————————ሺ !»

«ለኔ እንደሚታየኝ ፋሺስት ኢጣሊያ አውርጳን ካልወረረች በስተቀር ከአሁን ወዲያ የዓለም መንግሥታት ማኅበር ለኢትዮጵያ የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እርዳታ ይሰጣል ማለት ዘበት ነው ።

« ነ——————————ው ?»

«እምን ፤ ነው !»

ድንቁ በዚህ ጊዜ መለኪያ ይዛ መጥታ መጠጥ ቀዳችላቸው ። ባሻ ቅጣውም በሰማው ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ባይረካም ሐሳቡን በወደፊቱ እቅዱ ላይ በማጣሉ ፤ «ከጥቂት ቀናት በኋላ ወደ ግጠር መዝመቴ ነው» አላቸው ፤ ቁርጠኛ በሆነ ስሜት ፤ «እናንተስ ምን ለመሆን አሰባችሁ ? ለጠላት ልትገዙ ነው ወይንስ ሌላ እቅድ አላችሁ ?»

የማይጨው ጦርነት በውል ከተረጋገጠበት ቀን ጀምሮ መንፈሳቸውን ሲያስጨንቅ የነበረው ጥያቄ ይኸው ነበር ። «ለኢጣሊያ ፋሺስት ሥርዓት ተንበርክከን በቅኝ ግዛት ሥር እንኖራለን ወይንስ ምን እናደርጋለን ?» የሚል ጥያቄ ።

«ለአርበኝነት መውጣትህ ከሆነ ከአንተው ጋር መሄድ አለብን ፤ ባሻ» አለው አባተ የምሩን ።

«ወደ ሜካ !»



"ወደ ሜካም ሆነ ወደ በረሃ !"

"እይሄሄ ! በአርበኝነት መኖር እስከዚህ ቀላል ሆነና! በአርበኝነት ለመኖርኮ እንደ ብረት መጠንከር ያሻል። የውጭ አርበኝነት የእናንተ ሙያ አይደለም ፤ አባተ ።"

"አንዳንድ ጊዜ ባሰበው እንደ ፈረንጅ እንጂ እንደ አገር ተወላጅ የምትቈጥረንም አይመስለኝም ባሻ። ያገር ተወላጅ እንዳልሆንን ሁሉ!"

"ታዲያ እኔ ምን ላድርግ ? የኔ ጥፋት አይደለም ። ያለበሳችሁና የገራችሁ አውሮፓ ነው ። አውሮጳን ውቀሱ።"

"ማንኛውም ሰው ችግር እንዲችል በችግር መኖር አለበት ። በሌላ ዘዴ ችግር ቻይና ጠንካራ ለመሆን አይቻልም ። እኛም ሜካ ገብተን እንደ ሌላው ሰው ሁሉ ችግር ለምደን ጠላታችንን መዋጋት አያቅተንም ።"

"አሁን ያልከው ከአንጀትህ ከሆነ ጠላትን ለመቋቋም ብዙ ዘዴ አለ ፤ አባተ ። ከዚህ ከከተማ ሳትወጡ ጠላትን ለመዋጋት ትችላላችሁ ። የውጭ አርበኝነቱን ለእኛ ተውልን…ለሙያተኞቹ ።"

"እንዴት ? ምን ማለትህ ነው ፤ ባሻ ?"

"ቁም ነገር እናውጋ ካላችሁ እናውጋ" አለ ባሻ ቅጣው ፤ ኮኛኩን ተጐንጭቶ ፤ "ከሁሉ ነገር በፊት ግን ፋሺስቶችን ለመዋጋት በእርግጥ ቆርጣችኋል ወይንስ እንዲያው ለጨዋታው ያህል ነው ?"

"እንደናንተ በጦር ሜዳ ባንሰለፍም እጃችንን አጣምረን የተቀመጥንበት ጊዜ የለም ፤ ባሻ ። በየፊናችን የተቻለንን ስናደርግ ፤ ስንጽፍ ፤ የገንዘብ መዋጮ ስንሰበስብ ፤ መሣሪያችን ስናደራጅ ፤ ፋሺስቶችን የሚ[illegible] ላላ [illegible] በሚስጥር ቆይተናል ።"

"እሱን አልጠረጥርም የማውቀው ነው ። እኔ ግን አሁን ለማወቅ የምፈልገው ከአሁን ጀምሮ በእርግጥ ፋሺስቶችን ለመዋጋት ቁርጠኛ መሆን አለመሆናችሁን እንድትነግሩኝ ነው ።"

አባት ሺፈራው በስጨት ብሎ ፣ "እስከዚህ ለምን ተጠራጠርከን ፣ ባሻ ?" አለውና "እውነት አሁን ባለው አቅሙ ጠላትን ለመቋቋም የማይፈልግ ኢትዮጵያዊ አለ ብለህ ትጠራጠራለህ ?"

"አይ ! እሱስ ሞልቷል ። የኢትዮጵያን ጀግና የጨፈጨፈው ግራዚያኒ ብቻ አይደለም ። የወገን ጠላትም ጨፍጭፎታል ። የሆነ ሆኖ ወደ ቁም ነገራችን እንመለስና..." ብሎ እንደ ገና መጠጡን ተጐንጭቶ መለኪያውን አስቀመጠና ፣ "ጠላትን ለማጥቃት ቆርጣችሁ ከተነሣችሁ ጠላትን የምትቋቋሙት ከዚሁ ይሆናል ። ግዳጃችሁም ከእኛ ግዳጅ የበለጠ አደገኛ ይሆን እንደ ሆነ እንጂ ያነሰ አይሆንም ።"

"እንዴት ?"

"የአርበኝነት ሥራ ከግልጽ ጦርነት በጣም የተለየ መሆኑን ታውቃላችሁ" አለ ባሻ ቅጣው ፤ "እኛ ጫካ የምንገባው አርበኞች የጠላትን እንቅስቃሴ ለማወቅ ፣ መቼ ማጥቃት እንዳለብንና መቼ መሸሽ እንደሚገባን ለማወቅ መረጃ ያሻናል ። ለዚህ የውስጥ አርበኞች ያስፈልጉናል ።"

"በጄ !" አለው አባት ።

"በተጨማሪም መሣሪያ ፣ በተለይም ጥይት በብዛት ያሻናል ። እነዚህን ለማግኘት የምንችለው ከሥውር ገበያ ብቻ ነው ። እነዚህንም ከጂቡቲ ወደ መሐል



ሀገር በባቡር ለማስገባት የውስጥ አርበኞች ያስፈልጉናል ። ተቀማጭነታቸው አዲስ አበባ ሆኖ በባቡር ጣቢያ የሚሠሩ ፣ ወደ ጂቡቲም የሚመላለሱ ፣ ለምሳሌ ካርኔ ቀራጮች ፣ እንዲሁም በድሬዳዋና በሐረር አካባቢ የሚኖሩ የውስጥ አርበኞች ያስፈልጉናል ። በሌላም በኩል ከምሥራቅ ድንበር ወደ መሐል አገር የሚመላለሱ ግመልና ሌላ የጭነት ከብት ያላቸው ነጋዴዎች እንዲኖሩን ያስፈልጋል ።"

"ይኸኮ ከፍተኛ ድርጅት የሚያሻው ጉዳይ ነው ፣ ባሻ ።"

"ነውና ! ከፍተኛም ወጪ የሚያስፈልገው ነው ። በመንግሥት መሥሪያ ቤቶችና በግል ኩባንያዎች ተቀጥረው ከሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ጋር ቋሚ ግንኙነት በመፍጠር በየወሩ የተወሰነ ያህል መዋጮ እንዲያደርጉ ፣ ቱጃር ነጋዴዎች እጃቸውን ፈታ አድርገው ጠርቀም ያለ መዋጮ እንዲያዋጡ የሚገፋፉና የሚመሩ የውስጥ አርበኞች ያስፈልጉናል ።"

ባሻ ቅጣው ይኸንን በሚናገርበት ጊዜ አባትና ቸሩ በአድናቆት ዓይን ይመለከቱት ነበር ። እስከዚህ በመደራጀት የሚያምን ፣ በተፈጥሮውም እስከዚህ ብልህ ባለሙያ አይመስላቸውም ነበር ።

"በጉዳዩ በጣም ያሰብክበት ይመስላል ፣ ባሻ" አለው አባት ፣ መለኪያውን እያነሣ ።

"አሰብኩበት እንጂ ! ከማይጨው ተነሥተን እዚህ እስከንደርስ ድረስ በሐሳቤ ይኸንኑ ሳውጠነጥን ነው የሰነበትኩት ። በአምባራዶምና በማይጨው ጦር ሜዳዎች ከተዋጋሁ በኋላና የፋሺስት ኢጣልያም የጦር

ኃይል እስከ ምን እንደሆነ ከተገነዘብሁ በኋላ ጣሊያናችን በግልጽ ጦርነት እንደማንቾላቸው ተረዳሁ ። በሥውር ጦርነት ግን በጊዜ ብዛት አፈር ድቤ እንደምናገባቸው ጥርጥር የለኝም ።”

በዚህ ጊዜ የጠበንጃ ተኩስ ሰሙ ። በከተማው ውስጥ የነበረው ዝርፊያና ግርግር ገና እላከተመም ነበር። ለሦስት ቀናት ሙሉ መንግሥት ስላልነበረ ሥርዓትና ሕግም አልነበረም ። ሁሉም በዘፈቀደ ነበር የሚኖር ።

ባሻ ቅጣው የሦስታቸውንም መለኪያ መልሶ ሞላና፣ “ከሕዝቡ ልዩ ልዩ ወገኖች፣ ተባባሪ የሚሆኑ ነበሬዎች፣ ካህናት ፣ የቤት አሽከሮች ፣ ወጣቶች...ያስፈልጉናል” አለ ፤ “አንዳንዶቹ በውጭ አርበኞችና በውስጥ አርበኞች መሐከል እንደ ድልድይ ሆነው የሚሠሩ ፣ አንዳንዶቹ ትምሕርት በማቀበልና ገንዘብ በመሰብሰብ የሚረዱ አንዳንዶቹም በመረጃው ክፍል የሚሠሩ ። አባተ ከተስማማህልኝ የመረጃውን ክፍል አንተ ብትመራው ሳይሻል አይቀርም ። የአእምሮ ሥራ ስለ ሆነ !” ብሎ ሣቅ አለ ፣ ባሻ ቅጣው ።

“ይኸኮ በአንድ ሌሊት ተነጋግረን የምንጨርሰው ሳይሆን ሰፋ ያለ ጊዜ ፣ ሰፋ ያለ ዕቅድ የሚያሻው ሥራ ነው ፣ ባሻ ።”

“እሱን መቼ አጣሁት !” ብሎ መጠጡን ፉት አለ ፤ “ብቻ ብዙ ጊዜ የለንም አባተ ። ሥራውን ባስቸኳይ መጀመር አለብን ። ጣሊያኖች አዲስ አበባን መያዛቸው ነው ። እኔም ወደ ገጠር ለመውጣት ተቻኩያለሁ ።”

“ለማንኛውም ምሽቱ እየገፋ ሄዷል” ባሻ ፣ አለ አባተ ፣ ሰዓቱን እያየ ፤ “ከሌሊቱ አራት ሰዓት ሊሆን



ምንም ያህል አልቀረውም ። አንተም ገና ከመንገድ ስለገባህ ዕረፍት ሳትሻ አትቀርም ። እኛም ብንሄድ ይሻላል ። ድርጅቱን ስለ ማቋቋምም ከነገ ጀምረን ጠንክረን እንሠራ” አለው ።

“በሉ እንግዲያውስ አንዳንድ ድገሙ” ብሎ ብር ጭቆአቸውን ሞላላቸውና ሦስቱም ኸው አደረጉት ። አባተና ቸሩ ባሻንና ድንቁን ተሰናብተው ወጡ ።.....

## ፲፩

የጭለማ ሌሊት ነበር ። የጅብ መንጋ በራስ መኰንን ድልድይ በኩል ወጥቶ ወደ ቀበና ፣ ወደ አራዳ ፣ ወደ እሪ በከንቱ ፣ ወደ ዶሮ ማነቂያ ፣ ወደ ሰባራ ባቡር ፣ ወደ ሠራተኛ ሠፈር ፣ ወደ ጠበንጃ ያዥ ሠፈር ፣ ወደ በቅሎ ቤት ፣ ወደ ደጃች ውቤ ሠፈር እና ወደ ተቀረውም አቅጣጫ እየተሰማራ የድመት የውሻ ያህያና የከብት ጥምብ የሚያነግቡበት ሰዓት...

የግቢ አንበሶች መልሰው መላልሰው የሚያገኙበት ፣ ሕዝቡን የሚረብሹበት ፣ ከተማውን ዱር የሚያስመስሉበት ሰዓት ...

የከተማ ውሾችም በየሠፈሩ የሚንጫጩበት ፣ ከሌሊት ጅብ ጋር የሚፋጠጡበት ሰዓት...

በዚያ ሰዓት አዲስ አበባ በጭለማ ተውጣ ነበር ። የታላቁ ግቢ አካባቢና የባቡር ጣቢያ አካባቢ እንጂ

የተቀረው ከተማ የኮሬንቲ መብራት አልነበረውም ። መንገዱም ፥ አደባባዩም ፥ መናርያ ሠፈሩም ጭለማ ለብሶ ነበር ። ከአንዳንድ ቤት በርና መስኮት ግን የኩራዝ መብራት ጭልጭል ሲል ይታይ ነበር ። መኪናዎቹ ባለቍ ቍጥር የመኪና መንገዶች ለአንድ አፍታ በርተው ወዲያውኑ ጭለማ ይለብሱ ነበር ።

አባተና ቸሩ ከባሻ ቅጣው ቤት ወጥተው ለትንሽ ጊዜ በዝምታ ከተራመዱ በኋላ ከመለያያቸው ሥፍራ ደረሱ ፥ ከአቴጌ ሆቴል አጠገብ ።

"ሽጉጥህን ይዘሃል ?" አለው አባተ ።

"ማታ ማታ ሽጉጤን ሳልይዝ ከቤት አልወጣም" አለው ቸሩ ፤ "በራስ መኰንን ድልድይ አካባቢ ከሚ ዟዟሩ 'ጽዳት ዘበኞች' ጋር ወዳጆች አይደለንም ።"

"ከጅቦቹ ጋር ? ጅቦችኮ ፈሪዎች ናቸው ። ዛሬ የሚያስፈሩት ዘራፊዎች እንጂ ጅቦች አይደሉም ።"

"እነሱም እንደ ጅቦቹ ፈሪዎች ናቸው ። መሣሪያ ያልታጠቀን ያጠቃሉ እንጂ መሣሪያ የያዘን ሰው አይ ደፍሩትም ።"

"ትንሽ ቦታ ድረስ ብሸኝህስ ?"

"ለምን ? ራሴን መጠበቅ አቅቶኝ ?"

"አይ እንዲያው...በቡድን ሆነው እንዳያጠቁህ ማለቴ ነበር ።"

"ግድ የለህም...ራሴን መጠበቅ አያቅተኝም" ብሎ ፥ "በል ደህና እደር" አለው ።

"ተው ትንሽ ቦታ ድረስ እንኳ ልሸኝህ ።"



"አንተም ስትመለስ በተራዬ ትንሽ ቦታ እንድሸ ኝህ ?" ብሎ ሣቀ ፥ ቸሩ ።

"እንደሱማ ከሆነ ስንሸኛኝ ማደራችን ነው !" ብሎ እሱም ሥቆ ፥ "ደህና እደር እንግዲያውስ" ብሎት ወደ ሆቴሉ አመራ ።

ወደ ፎቁ ለመውጣት በቡና ቤቱ ማለፍ ነበረበት ። ቡና ቤቱ ውስጥ ካለ አንድ ጠጪ አልነበረም ። ሰው ዬው በረጅም ኩርሲ ላይ ተቀምጦ ሐሳቡን ከሩቅ ቦታ ሰድዶ ሲጋራ ሲያቦንን ነበር ። ቦዩ ሰው የለም በማለት ቡና ቤቱን እንዳይዘጋበትና እሱንም እንዳያስወጣው በመፍራት ቦዩንም መጠጥ ጋብዞት ነበር ። በሌላ ጊዜ በዚህ ሰዓት ቡና ቤቱ በሰው ተመልቶ ይታይ ነበር ። በከተማው ውስጥ ረብሻ ከተነሣበት ቀን ወዲህ ግን የሆቴሉ ደምበኞች በጊዜ ወደ የቤታቸው ፥ ክፍል የተ ከራዩትም ወደየክፍላቸው ይገቡ ነበር ።

"ኤ ! አባተ !" ሲል ተጣራ ጠጪው ፥ "እንኳን መጣህ ጃል ! ብቻዬን ቁጭ ብዬ መጠጣት ሰልችቶኝ ነበር...ና እንጂ...ናና ወንበር ያዝ...ጋብዤሃለሁ...ነገ ሂያጅ ስለ ሆንኩ የወጪ ልበልህ" አለው ።

"መጠጥ እንኳ በቅቶኛል ፥ ግደይ ። አፍ አካፍተኝ ካልከኝ ግን ታዛዥ ነኝ !"

"ና እባክህን ጠጣ ። አዲስ አበባን ደህና ሰንብቺ የምልበት ምሽት ስለ ሆነ ናና ጠጣ ። ነገ ማለዳ ሂያጅ ነኝ" ብሎ ዓይኑን ወደ ቦዩ አዞሮ ፥ "ሌላ ብርጭቆ አምጥተህ ቅዳ ። ለራስህም ቅዳ" አለው ።

አሳሳፊው ጠባብ ሱሪ ታጥቋል ። በላዩ ላይ ረጅም እጀ ጠባብ አጥልቋል ። በወገቡ ላይ ሐምራዊ ቀለም ያለው ሰፊ መቀነት ታጥቋል ። ባዶ እግሩን ነው ።

“ምን ልቅና ጌታዬ ?” አለው አባተ መጥቶ ኩርሲ ላይ ሲወጣ ።

“እናንተኑ ልምሰላ !” አለው አባተ ። አሳላፊውም ከመደርደርያው ወይን ጠጅ አውርዶ ቀዳለት ።

“አሳሞቹ ከተማውን ነገ ሳይዙት አይቀሩም ይባላል” አለ ግደይ ፣ በአንድ እጁ ብርጭቆ በሌላ እጁ የተለኰሰ ሲጃራውን ይዞ “እና ፣ የአዲስ አበባ መያዝ ምን ማለት እንደሆነ ይገባሃል ፣ አባተ ?” ሲል ጠየቀው።

“ከያዙት በኋላ እናያለን እንጂ በቅድሚያ ማወቅ እንዴት ይቻላል !”

“እኔ በቅድሚያ ልነግርህ እችላለሁ ፣ አባተ ! ጣሊያኖች አዲስ አበባን ከያዙበት ሰዓት ጀምሮ ማንም አበሻ ማንም ጥቁር ከእንደዚህ ያለ ሆቴል ገብቶ መጠጥና ምግብ ለማዘዝ አይፈቀድለትም ። ይህ ታዲያ ምን ማለት እንደ ሆነ ይገባሃል ?”

“ሰውን በቆዳው ቀለም ምክንያት መናቅ ማለትህ ከሆነ በጥቂቱም ቢሆን ቀምሼዋለሁ ።”

“የት ?”

“ውጭ አገር ነዋ !”

“እኔ የምልህና በውጭ አገር ያለው ሁኔታ ለየቅሉ!”

“እንዴት ?”

“ውጭ አገር ሆነህ ‘ለጥቁር ቤት አናከራይም… ጥቁር ከዚህ ቡና ቤት እንዲገባ አይፈቀድም…ጥቁር ወንድ ከነጭ ሴት ጥቁር ሴት ከነጭ ወንድ ጋር አብረው ቢገኙ ያስወነጅላል…’ የሚል ነገር ቢያጋጥምህ



ለጊዜው ትናደድ ይሆናል ። ‘ወደ አገሬ ስገባ ነጮቹ እዚህ ሆኜ ባበሳጩኝ ልክ አበሳጫቸዋለሁ ፣ ነጭ ባየሁ ቍጥር ምሬቴን ጢቅ አልበታለሁ’ ብለህ ለራስህ ቃል ልትገባና ወደ አገርህም ከተመለስህ በኋላ ባሰብኸው ዓይነት ነጮችን ልትቀበል ትችላለህ ። ነገር ግን ፣ አለ ግደይ “ነገር ግን ፣ በገዛ አገርህ ጥቁር በመሆንህ ብቻ ስትናቅና ስትዋረድ የት ለመሄድ ይቻልሃል ? ምንስ ታደርጋለህ ?”

“ትዋጋለሃ ! ትጋደላለህ ! ”

“እንደሱ ማለቱ ቀላል ፣ ድርጊት ላይ ማሳየቱ ግን ከባድ ነው” አለው ግደይ “ፋሺስቶችን መዋጋት ቂሃ አይምሰልህ ፣ አባተ ። እነሱ መሣሪያ ታጥቀው ሕዝቡን በአረመኔነት ሲረሽኑት ፣ ሲጨፈጭፉት አንተ ባዶ እጅህን ሆነህ ልትቋቋማቸው አይቻልህም ። እንደ ባርያ አንገትህን ሰብረህ ለነሱ ከመገዛት በስተቀር ሌላ ምርጫ የለህም…ለመሆኑ ወደ አዲስ አበባ እንዴት እንደመጣሁ ነገርኩህ ? ለብዙ ጓደኞቼ ስለ ነገርኳቸው ምናልባት ለአንተም ነግሬህ እንደሆነ ድግግሞሽ እንዳይሆንብኝ…”

“እነግርሃለሁ ብለህ ቃል ከገባህልኝ ረጅም ጊዜ ሆኗል እንጂ እስከ ዛሬ ድረስ አልነገርከኝም ።”

“ቦይ …መጠጥ ጨምርልን ። ለራስህም ቅዳ ። የመጨረሻ ቀኔ ስለሆነ ምስታችንም እንጠጣ…እንደሰት” አለና ግደይ ዓይኑን ወደ አባተ አዙሮ ቀጠለ ፤ “እስከ ዛሬ ድረስ ካልነገርኩህ እንግዲያውስ አሁን ልንገርህ ። አንድ ቀን የሥራ ባልደረባዬ የሆነ ጣሊያን ጀኔራል ደቦኖ ጽ/ቤት ውስጥ አብረን እንሠራ ስለ ነበረ ነው ባልደረባዬ የምለው ። አለዚያ ጣሊያኑን ጌታዬ ማለት በተገባኝ… ! — እና ፣ አንድ ቀን ይህ ኢጣሊያዊ የሥራ ባል

ደረባዬ ሊጋብዘኝ ወደነሱ ክበብ ይዞኝ ሄደ ። በግብ
መልክ ካልሆነ በስተቀር አበሻ እነሱ ክበብ እንዲገ
ፈጽሞ አይፈቀድለትም ። እንዲህ ያለ 'ክብር' የሚ
ጣቸውም ጥቁሮች በጣም ጥቂቶች ነበሩ ። ከእነዚህ
መሐከል የምሥጢራቸው ተካፋዩና ትርጁማናቸ
አንዱ መሆኔ ፣ ነበር ። እና ፣ በምሽት ሰዓት ወደ ክበ
ቸው ይዞኝ ሄደ ። ክበቡ ውስጥ እንደ ጓበን ሁለት ወጣ
ጣሊያኖች አዩኝና ይጣለቁብኝ ፣ ከንቀታቸውም የ
ነሣ ያፏጩብኝ ጀመር ። ከማፈሬ የተነሣ ትል እን
ሰው የሆንኩ አልመሰል አለኝ ። አሰበው እንግዲህ.
ተጋብዤ ነው የሄድኩት ! እና ፣ ገና ስገባ ልጆቹ ይጣ
ቁብኝ ያፏጩብኝ ጀመር ። 'በመጣህበት እግርህ ተመለ
ሂድ ፣ አንተ ውሻ !' ቢሉኝ ኖሮ ከዚያ ይበልጥ ባላ
ርኩ ። መቼም እንዲህ ያለው ነገር በራስህ ካልደረ
ብህ በስተቀር በሐሳብህ ልትደርስበት አይቻልህም " ብ
ወይኑን ተጉንጭቶ አጣጥሞ ሲጋራውን ስቦ ጭፍ አ
ውና ፣ "ለማንኛውም የጋበዘኝ የሥራ ባልደረባዬ የል
ቹን ብልግና አይቶ ተቆጣቸው ። ከልጆቹም አንደኛ
በፈንታው ተቆጥቶ በብልግናውም እስከ ምን ድረ
ሊገፋበት እንደሚችል ለማሳየት ፈልጎ ነው መሰለኝ
በፊቱ የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ አንሥቶ እን
ቅመስ አለኝ ! "

"ወረወረብህ ? "

"አስከነመጠጡ ! "

"እና ፣ ምን አደረግህ ? "

"ልነግርህም አይደል ! መቼም ለትዕግሥት ገ
ቢያ አለው ። ሰብአዊ ክብር ሲዋረድ ስሜት ይገነ
ልና እኔም ራሴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ ሩጬ ከክበ



ወጥቼ የደህ ሸክም የሚያህል ድንጋይ አንሥቼ ወደ ክበቡ ተመልሼ ገብቼ ጠርብ በሚያህል ሮማዊ አፍንጫው ላይ ከሰከሰኩበት ። ክበቡ ውስጥ ከፍተኛ ትርምስ ተነሣ ። በግርግሩ መሐከል እኔ ሾልኬ ወጣሁና መሮጥ ጀመርኩ ። በቅዠት ዓለም እንጂ በውን ዓለም ያለሁ አልመሰል አለኝ ። ለመሆኑ በቅዠት ዓለም ሆነህ ጅብ አባርሮህ ያውቃል ? "

"እንዲያውም !"

"እንግዲያውስ እኔን ጅብ አባርሮኛል—በእንቅልፍ ልቤ...ከአንድም ሁለት ጊዜ ! ስሮጥ...ጅቡ ሲከተለኝ. ...ስሮጥ...አሁንም ጅቡ ሲከተለኝ...ፍጥነት ጨምሬ ስሮጥ...ጅቡ አሁንም እንደ ገና ሲከተለኝ...ደርሶብኝ ሊበላኝ አፉን ሲከፍት...ሳመልጠው...ከፍጥነቴ የተነሣ በቅጽበት ክንፍ አውጥቼ ስበርር...ጅቡ አሁንም እንደ ገና ደርሶብኝ እግሬን በጭቆ ሊወስድ ሲቃጣ...እኔም ሽሽቴን ስቀጥል እቆይና በድንገት ብንን ብዬ እፎይ ! የምልበት ጊዜ አለ ። ታዲያ ያን ቀን የፈረንጁን አፍንጫ በድንጋይ ከሰከሼ ልክ በቅዠት ዓለም ጅብ እንደ ተከተለኝ ያህል ስሮጥ...ስሮጥ...ስሮጥ ቆየሁና ከአንድ ቦታ ስደርስ አንድ ካሚዮን ነጂ አገኘሁ ። የአገር ልጅ ነበር ። ታሪኬን አጫወትኩትና "አበጀህ ! " አለኝ ። እስከ መረብ ድረስም በካሚዮን ይዞኝ መጣ ። የመረብን ወንዝ ከተሻገርኩ በኋላ የነጻነት አየር ተነፈስኩ" አለና ግደይ ፣ "ቦይ...መጠጥ ጨምርልን...ለራስህም ቅዳ...የመሰናበቻዬ ሌሊት ስለ ሆነ ጠጡ...ጋብዤአችኋለሁ !" ብሎ ሐሳቡን እንደ ገና ወደ አባተ መልሶ ፣ "ሸሽቼአቸው መጣሁ" አለው ። "አሁንም እሸሻቸዋለሁ ። እዚህ ቆሞ ብዬ አልጠብቃቸውም !"

ደረባዬ ሊጋብዘኝ ወደነሱ ክበብ ይዞኝ ሄደ ። በግብግ
መልክ ካልሆነ በስተቀር አበሻ እነሱ ክበብ እንዲገባ
ፈጽሞ አይፈቀድለትም ። እንዲህ ያለ 'ክብር' የሚሰ
ጣቸውም ጥቁሮች በጣም ጥቂቶች ነበሩ ። ከእነዚህም
መሐከል የምሥጢራቸው ተካፋዩና ትርጁማናቸው
እንዱ መሆኔ ፤ ነበር ። እና ፤ በምሽት ሰዓት ወደ ክበባ
ቸው ይዞኝ ሄደ ። ክበቡ ውስጥ እንደ ገባን ሁለት ወጣት
ጣሊያኖች አዩኝና ይጣለቁብኝ ፤ ከንቀታቸውም የተ
ነሣ ያፏጩብኝ ጀመር ። ከማፈሬ የተነሣ ትል እንጂ
ሰው የሆንኩ አልመሰለ አለኝ ። አሰበው እንግዲህ...
ተጋብዤ ነው የሄድኩት ! እና ፤ ገና ሰገባ ልጆቹ ይጣለ
ቁብኝ ያፏጩብኝ ጀመር ። 'በመጣህበት እግርህ ተመልሰህ
ሂድ ፤ አንተ ውሻ ! ' ቢሉኝ ኖሮ ከዚያ ይበልጥ ባላፈ
ርኩ ። መቼም እንዲህ ያለው ነገር በራስህ ካልደረሰ
ብህ በስተቀር በሐሳብህ ልትደርስበት አይቻልህም " ብሎ
ወይኑን ተጐንጭቶ አጣጥሞ ሲጋራውን ስቦ ጭፍ አለ
ውና ፤ "ለማንኛውም የጋበዘኝ የሥራ ባልደረባዬ የልጆ
ቹን ብልግና አይቶ ተቆጣቸው ። ከልጆቹም አንደኛው
በፈንታው ተቆጥቶ በብልግናውም እስከ ምን ድረስ
ሊገፋበት እንደሚችል ለማሳየት ፈልጎ ነው መሰለኝ ፤
በሔቱ የነበረውን የመጠጥ ጠርሙስ አንሥቶ እንካ
ቅመስ አለኛ ! "

"ወረወረብህ ? "

"እስከነመጠጡ ! "

"እና ፤ ምን አደረግህ ? "

"ልነግርህም አይደል ! መቼም ለትዕግሥት ግለ
ቂያ አለው ። ሰብአዊ ክብር ሲዋረድ ስሜት ይገነፍላ
ልና እኔም ራሴን መቆጣጠር ስላልቻልኩ ሩጬ ከክበቡ



ወጥቼ የድሀ ሸክም የሚያህል ድንጋይ አንሥቼ ወደ
ክበቡ ተመልሼ ገብቼ ጠርብ በሚያህል ርግዊ እፍን
ጌው ላይ ከሰከስኩበት ። ክበቡ ውስጥ ከፍተኛ ትር
ምስ ተነሣ ። በግርግሩ መሐከል እኔ ሾልኬ ወጣሁና
መሮጥ ጀመርኩ ። በቅዠት ዓለም እንጂ በውን ዓለም
ያለሁ አልመሰል አለኝ ። ለመሆኑ በቅዠት ዓለም ሆነህ
ጅብ አባርሮህ ያውቃል ? "

"እንዲያውም !"

"እንግዲያውስ እኔን ጅብ አባርሮኛል—በእንቅልፍ
ልቤ...ከአንድም ሁለት ጊዜ ! ስሮጥ...ጅቡ ሲከተለኝ
...ስሮጥ...አሁንም ጅቡ ሲከተለኝ...ፍጥነት ጨምሬ
ስሮጥ...ጅቡ አሁንም እንደ ገና ሲከተለኝ...ደርሶብኝ
ሊበላኝ አፉን ሲከፍት...ሳመልጠው...ከፍጥነቴ የተነሣ
በቅጽበት ክንፍ አውጥቼ ስበርር...ጅቡ አሁንም እንደ
ገና ደርሶብኝ እግሬን ቦጭቆ ሊወስድ ሲቃጣ...እኔም
ሽቴን ስቀጥል እቆይና በድንገት ብንን ብዬ እርይ !
ምልበት ጊዜ አለ ። ታዲያ ያን ቀን የፈረንጁን እፍ
ጌ በድንጋይ ከሰከሼ ልክ በቅዠት ዓለም ጅብ እንደ
ተከተለኝ ያህል ስሮጥ...ስሮጥ...ስሮጥ ቆየሁና ከአንድ
ታ ስደርስ አንድ ካሚዮን ነጂ አገኘሁ ። የአገር ልጅ
በር ። ታሪኬን አጫወትኩትና "አበጀህ ! " አለኝ ።
ስከ መረብ ድረስም በካሚዮን ይዞኝ መጣ ። የመረብን
ንዝ ከተሻገርኩ በኋላ የነጻነት አየር ተነፈስኩ" አለና
ደይ ፤ "ብይ...መጠጥ ጨምርልን...ለራስህም ቅዳ...የመ
ናበቻዬ ሌሊት ስለ ሆነ ጠጡ...ጋብዤአችኋለሁ !"
ሎ ሐሳቡን እንደ ገና ወደ አባቱ መልሶ ፤ "ሸሸቼአ
ው መጣሁ" አለው ፤ "አሁንም እሸሻቸዋለሁ ። እዚህ
ጭ ብዬ አልጠብቃቸውም !"

"ከአሁን ወዲያ የምትሸሸበት አገር የለህም ፣ ግደይ። ሽሽትህን ትተህ ቆመህ ብትዋጋ ይሻልሃል ።"

"መቼም ስሜን አያውቁትም" አለ ግደይ ፣ ለገዛ ራሱ እንደሚናገር ሁሉ ፤ 'አሥመራ በነበርሁ ጊዜ 'ማርዮ' ብለው ነበር የሚጠሩኝ ። ሌሎቹን 'ሉዊጂ ፣ ሎሬንሶ ፣ አንቶንዩ ፌዴሪኮ...' እያሉ ይጠሯቸዋል ። እኛ ጣሊያኖች አይደለንም ንጹሕ አበሾች እንጂ ! የእኔም ትክክለኛ ስሜ 'ማርዮ' አይደለም ። እነሱ ግን 'ማርዮ' ነበር የሚሉኝ ። አሁንም ቢሆን በትክክለኛ ስሜ ሊያውቁኝ አይችሉም ። 'ማርዮ' አይደለሁም! እኔ 'ማርዮ' አይደለሁም...ግደይ ነኝ...ግደይ ገብረ እግዚእ !" ብሎ ደረቱን መታታና ቀጠለ ንግግሩን ፣ "በስሜ ለይተው ባያውቁኝም ግን በመልኬ ያውቁኛል። የደቦና ሰዎች ። እዚህ ተወዝፌ እንዲገድሉኝ ዕድል አልሰጣቸውም ። እሸሻለሁ ። ወደ ጂቡቲ...የባቡር ትኬት አስቆርጬ በኪሴ ይዣለሁ ። ወደ ጂቡቲ...ትሰማኛለህ አባተ ? ወደ ጂቡቲ መሸሼ ነው ።"

"ምን ለመሆን ? ጂቡቲስ ቅኝ ግዛት እንጂ ነጻ አገር አይደለም ።"

"ቅኝ ግዛት ቢሆን የፋሺስት ቅኝ ግዛት አይደለም ። ፈረንሳዮች ፋሺሽቶች አይደሉም ።"

"ሸሽትህን አቁመህ ተዋጋ ፣ ግደይ ። ከፋሺስቶች ጋር መጋደሉ ይሻልሃል ።"

"የትም ብሄድ ፋሺስቶችን እዋጋቸዋለሁ ። እነሱም በቀላሉ የሚለቁኝ አይመስለኝም ። እንደ ነገርኩህ ምሥጢረኞቸውና አስተርጓሚአቸው ነበርኩ ። የአማርኛ ቋንቋም አጣርቼ ስለማውቅ ብዙ ምሥጢር እንዳ



ባከንኩባቸው አድርገው እንደሚከታተሉኝ አትጠርጥር ። ስለዚህ እዚህ ተቀምጬ እንዲገድሉኝ ዕድል ልሰጣቸው አልፈልግም ። ገባህ የምልህ ?" አለና ፣ "ባሪስታ... መጠጥ ጨምርልን ። ለራስህም ቅዳ ። የዛሬውን ምሽት በደስታ ማሳለፍ አለብን" አለ ።

"ኧረ ይብቃህ እባክህን ፣ ግደይ ። ሄደህ ብትተኛ ይሻልሃል ። ኢይ...ማንጐላጀት ጀምረሃል ፣ ግደይ ። ነቃ በል እንጂ !" ብሎ ትከሻውን መታታው ።

"ሰክረሃል ማለትህ ከሆነ የመጠጥ ልምዴን አታውቅም ፣ አባተ ። በፍጹም አታውቅም ። ግደይ ገብረግዚእ ይጠጣል እንጂ ከቶም አይሰክርም ። ገባህ የምልህ ? ካላመንከኝ ደግሞ እንወራረድ ።"

"ውርርድ አልፈልግም ። ብቻ ቢበቃህ ይሻላል ።"

"ግደይ ገብረግዚእ የሚያንጐላጀው ስለ ሰከረ አይደለም ፣ አባተ ሺፈራው ! ግደይ ገብረግዚእ የሚያንጐላጀው መጠጥ ስላልበቃው ነው ። በይ...ቅዳ ። ለእኔም ለአባተም ለራስህም ቅዳ ። ይህች የመጨረሻ ሌሊቱ ነች በአዲስ አበባ..."

"እውነት ወደ ጂቡቲ ለመሄድ አስበክ ለመሆን ? ወይንስ... ?"

ግደይ ገብረግዚእ አይዋሽም ፣ አባተ ሺፈራው ! ወደ ጂቡቲ እሄዳለሁ ስል ወደ ጂቡቲ እሄዳለሁ ማለት ነው። ካላመንከኝም ቲኬቱን ላሳይህ" ብሎ ኪሱን ይደባብስ ጀመር ። "ይኸውልህ...እየው...ወደ ጂቡቲ ሂያጅ ነኝ ነገ ማለዳ ።"

"ስማኝ ግደይ ። አንድ ነገር አስታወሰከኝ ። ብቻ ጉዳዩ ምን እንደሆነ አሁን ልገልጽልህ አልችልም ።"

"አሁን ካልገለጽህልኝ መቼ ልትገልጽልኝ ነው ?"

"ጂቡቲ ስትደርስ ወዲያውኑ ጻፍልኝ ። ከዚያ በኋላ ጉዳዩ ምን እንደሆነ አብራርቼ እጽፍልሃለሁ ።"

"እዩ ጉድ !" አለ ግደይ ገብረግዚአ ፡ "አሁንም የሰ ከርሁ መስሎሃል !"

"በፍጹም ! ሰክረሃል ብዬ አይደለም ።"

"ታዲያ አሁኑኑ ለምን አትነግረኝም ?"

"ጉዳዩ በጅምር ላይ ያለ እንጂ ያለቀለት አይደ ለም ። ጂቡቲ ደርሰህ ደብዳቤ እስክትጽፍልኝ ድረስ ጉዳዩ ይበልጥ እየጐላ ስለሚሄድ ዝርዝር ሁኔታውን ያኔ እገልጽልሃለሁ ።"

"ይሁና እንግዲያው ! በምን አድራሻ ልጻፍልህ ?"

"የወደፊት አድራሻዬን ገና አላውቀውም ። ጣሊ ያኖች አዲስ አበባን ከያዙ በኋላ ውጭ ጉዳይ ሚኒስ ቴር እቆያለሁ የሚል ሕልም የለኝም ። ስለዚህ በቀኛ ዝማች ሺፈራው በኩል የሚሰጥ ብለህ ብትጽፍልኝ ይደርሰኛል ። አለዚያም አስተማማኝ ሰው ስታገኝ የቃል መልዕክት ላክልኝ ። ልነግርህ የምፈልገው ጉዳይ በም ስጢር የሚያዝ ፋሺስቶችንና እኛን የሚመለከት ብርቱ ጉዳይ ነው ።"

"ገብቶኛል ! በይ...ብርጭቆአችንን ሙላልን ። ያን ተንም ብርጭቆ ሙላው ። እንጠጣ ! አዲስ አበባን የም ሰናበትበት ሌሊት ስለ ሆነ እንደሰት !"

ግደይ ገብረግዚአ ቀደም ብሎ እንደ ተናገረው ሁሉ ይበልጥ በጠጣ ቁጥር ማንጐላጀቱን አቁሞ ይበልጥ እየነቃ ሄደ ፡ የእያንዳንዱ ሰው ልምድ የተለያየ ነውና። እንዲሁ ሲጠጡ ፡ ሲጫወቱ ቆዩና መንፈቀ ሌሊት ሲሆን ቦዩ ቡና ቤቱን መዝጋት እለብኝ ስላለ ግደይ ሒሳቡን ከፍሎ እሱና አባተ ተነሥተው ወጡ ።



# ክፍል አራት

## ተጋድሎ

የጣሊያን ታንኮች...ብረት ለበሶች...ካሚዮኖች... እና ፡ ሌሎች ሌሎችም ተሽከርካሪዎች በምሥራቅ በር በኩል አድርገው አዲስ አበባ ከተማ መግባት በጀመ ሩበት ሰዓት የአዲስ አበባ ምድር ተነቃነቀች ። ታን ኮቹ...ብረት ለበሶቹ...ካሚዮኖቹ...እና ፡ የተቀሩትም ከበ ድበድ ያሉ ተሽከርካሪዎች በሺህ የሚቈጠሩ በመሆናቸ ውና የሚሽከረከሩትም ተራርቀውና ዝግ ብለው በመሆኑ ማለቂያ ያላቸው አይመስሉም ነበር ።

የጣሊያን ወታደሮች ነጮችም ጥቁሮችም ተሽከ ርካሪዎቹ ላይ ሆነው የድል መዝሙር እየዘመሩ ማለ ፋቸውን ቀጠሉ ። የአዲስ አበባ ሕዝብ ራቱ ጥቀርሻ ለብሶ ልቡ በኀዘን ደምቶ የጠላት ጦር በሚያልፍበት መንገድ ግራና ቀኝ ቆሞ ሰልፉን ይመለከት ነበር ። ከሕ ዝቡ መሐከል ተንሰቅስቀው የሚያለቅሱ ወንዶችም ሴቶችም ነበሩ—ነጻ ኢትዮጵያ ድል ሆና የኢትዮጵያ ባን ዲራ ወድቆ የጣሊያን ባንዲራ በኢትዮጵያ አየር ላይ መውለብለብ ጀምሮ ነበረና ።

የጣሊያን አውሮፕላን አብራሪዎች በበኩላቸው በአዲስ አበባ ሰማይ ላይ እያንዣበቡ ፡ "ጦርነቱ አብቅቷል..

ከአሁን ወዲያ ከተማው ውስጥ ሰላምና ጸጥታ ይከበራል...ባለፉት ሦስት ቀናት በዝርፍያ የተሳተፉ ሁሉ አይቀጡ ቅጣት ይቀጣሉ...ከዚህች ሰዓት ጀምሮ ማንኛውም አበሻ መሣሪያ እንዳይዝ ተከልክሏል...” የሚል ጽሑፍ ይበትኑ ነበር ።

ያን ሰሞን ማርሻል ባዶሊዮና ጄኔራል ግራዚያኒ ውድድር ተጋጥመው ነበር—ማርሻል ባዶሊዮ በድል አድራጊነት አዲስ አበባን ለመያዝ ፣ ጄኔራል ግራዚያኒ በበኩሉ ሐረርን ለመያዝ ፤ እኔ እቀድም እኔ እቀድም ነበር ውድድሩ ። አሸናፊው ማርሻል ባዶሊዮ ሆነ ። ምክንያቱም እሱ በድል አድራጊነት አዲስ አበባ እየገባ በነበረበት በዚያ ሰዓት ጄኔራል ግራዚያኒ ከኦጋዴን በረሃ ገና አልወጣም ነበር ። ለዚህ ነው በዚያን ቀን ግደይ ገብረግዚአ በሐረርጌ ባቡር ተሳፍሮ ድሬዳዋን ባለፈበት ሰዓት አንዳችም አደጋ ያላጋጠመው ።

፪

ፋሺስቶች አዲስ አበባን ከያዙ በኋላ በየቤቱ እየሄዱ ፍተሻ ማድረግ ጀመሩ ። ፍተሻ በጀመሩበት በሦስተኛው ቀን አንድ ፈረንጅና አራት ጥቁር ወታደሮች ከባሻ ቅጣው ቤት ከቸች አሉ ። ባሻ ቅጣው በዚያ ሰዓት እቤት ውስጥ አልነበረም ።

ፈረንጁ ባርዚኒ የተባለ ፣ ቁመቱ ዘለግ ያለ ፣ ሰውነቱ የዳበረ ፣ ጸጉሩ የቀይ ዶሮ ላባ የመሰለ ፣ አፍንጫው



እንደ ሰይፍ ቀጥ ያለ ፣ በግምት የሠላሳ ዓመት ጐልማሳ ነበር ። አራቱ ጥቁር ወታደሮች ባለመርገፍ ጠርቡሽ ቆብ የደፉ ፣ ቀይ መቀነት የታጠቁ ጥቁር የባሱቲክ መሣሪያ የተሸከሙ ነበሩ ። ከአራቱ አንደኛው በኩቱ እጅጌ ላይ የማዕረግ ምልክት ለጥፎ ነበር ። ማዕረጉ ከአምባ ዕልቅና የሚነጻጸር “ሹምባሽ” በሚል ስያሜ የሚታወቅ ነበር ።

“እናንተ ሦስታችሁ ምድረ ግቢውን ፈትሹ ። አንተ ሹምባሽ እስጢፋኖስ እዚህ ውስጥ የሚገኘውን ፈትሽ” የሚል ትዕዛዝ ሰጡ ባርዚኒ በጣሊያንኛ ።

የቤቱ ግርዶሽ ቀደም ብሎ ተነሥቶ ነበር ። ድንቄ ሽቦ አልጋው አጠገብ ቆማ ፈታኞቹን ታስተውላቸው ነበረች ። ሕፃኗ ልጅ አልጋው ላይ ተኝታ እንቅልፍ ወስዷት ነበር ። ዓለሜም ባርዚኒን ፈርቶ ራቅ ብሎ ቆሞ ያስተውለው ነበር—ከዚያን ቀን በፊት ነጭ ሰው አይቶ አያውቅ ነበርና ።

“እነዚህ ታስረው የተቀመጡ ዕቃዎች ምንድናቸው፤ ገመዶቹን ፍቷቸው” አለ ሹምባሽ እስጢፋኖስ ።

ዕቃዎቹን ሰብስባ ለማሰር ብዙ ጊዜ ቢወስድባትም ድንቄ የሹምባሽ እስጢፋኖስን ትዕዛዝ በመቀበል ገመዶቹን ትፈታ ጀመር ። እያንዳንዱ ጥቅል በተፈታ ቍጥር ሹምባሽ እስጢፋኖስ ዕቃዎቹን እየበታተነ በውስጣቸው የተደበቀ መሣሪያ ፣ ጥይት ፣ አለዚያም የተዘረፈ ዕቃ መኖር አለመኖሩን ይፈትሽ ገባ ። ባሻ ቅጣው የተኰሰና የስለት መሣሪያዎቹን ቀደም ብሎ ወደ አባና ቤት አሸሽቶ ነበር — ከከተማ ክልል ውጭ ያሉ መኖሪያ ቤቶች አይፈተሹም ብሎ በማመን ። ነገር ግን

ሹምባሽ እስጢፋኖስ ምንም ዓይነት መሣሪያ ሊያገኙ አልቻሉም ። ቀጥሎም ድንቄን በጥያቄ ያዋክባት ጀመር ።

"እነዚህ ሕፃናት ያንቺ ልጆች ናቸው ?"

"አዎን ።"

"አባታቸው ወዴት አለ ?"

"አላወቅሁም . . ምናልባት ወደ ገበያ ወርዶ ይሆናል ።"

"ገበያ ?"

"አዎን ። ባለቤቴ ነጋዴ ነው ።"

"ነጋዴ ?"

"አዎን . . . የጨርቃጨርቅ ነጋዴ ። የመብሩቅና የአቡጀዲ ጣቃ ከዚህ ከከተማ ገዝቶ ወደ ባላገር ገበያ ወስዶ ይሸጣል ። ከባላገር ሲመለስም እግረ መንገዱን እህልና ቡና ገዝቶ እዚህ አምጥቶ ለቸርቻሪዎቹ ይሸጣል ። በዚህ ዘዴ ነው የምንተዳደረው" አለችና በሹምባሽ እስጢፋኖስ ገጽታ ላይ ጥርጣሬ ያለ መስሏት ፣ "ካላመንከኝም እሱ ወደ ቤት ሲመለስ ልትጠይቀው ትችላለህ አለችው ።

"ለምንድነው የማላምንሽ ?"

"እይ እንዲያው ካላመንከኝ ብዬ . . . እኔ እንኳን እውነቱን ነው የነገርኩህ ።"

"በምን ሰዓት ነው የወጣው ?"

"ቀደም ብሎ ነው የወጣው ። ትክክለኛ ሰዓቱን አላውቅም ። እኔ ሰዓት የለኝ !"

ድንቄ ራሷ በፈጠረችው ታሪክ እየተገረመች አንዴም ወደ ሹምባሽ እስጢፋኖስ አንዴም ወደ ባርዚኒ ሥረቅ



አድርጋ ትመለከት ነበር ። እሷና እስጢፋኖስ ቃል በሚለዋወጡበት ጊዜ ባርዚኒ ዓለሜን ሲያባብል ነበር ። በጣት ምልክት ወደ እሱ እንዲጠጋ አድርጎ ከኪሱ ከረሜላ አውጥቶ ሰጠው ። ዓለሜ ፈረንጁን ስለፈራው ወረቀቱን ሳይልጠው ከረሜላውን በእጁ ይዞ ዝም ብሎ ቆመ ። ባርዚኒም ጐንበስ ብሎ ከረሜላውን ከዓለሜ እጅ ወስዶ ወረቀቱን ልጦ ሰጠውና እንዲጐርሰው በጣት ምልክት አሳየው ። ድንቄ ይህንን አስተውላ እስጢፋኖስን ባለበት ትታው ወደ ዓለሜ ሄዳ ከረሜላውን ከእጁ መንጥቃ ወሰደችበት ። ባርዚኒም ተገረመ ፣ "ለምን ድን ነው የወሰደችበት ?" ሲል ሹምባሽ እስጢፋኖስን ጠየቀው ።

"መርዝ ነው ብላ ይሆናል ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ !" አለው ሹምባሽ እስጢፋኖስ ።

"መርዝ ?" ሲል ጠየቀው ባርዚኒ ፣ ከበፊት ይልቅ ተገርሞ ።

"የዱቼ መንግሥት አበሻን ለማሠልጠን መምጣቱን አታውቅም . . .አይገባትም ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ ።"

ባርዚኒ ሌላ ከረሜላ ከኪሱ አውጥቶ ወረቀቱን ልጦ አፉ ውስጥ ወረወረውና ፣ "ለልጁዋ የሰጠሁት ጣፋጭ ከረሜላ እንጂ መርዝ አለመሆኑን ንገራት" አለው፤ "የድል አድራጊው የዱቼ መንግሥት ወደዚህ የመጣው አበሻን ለማሠልጠን እንጂ ሕፃናትን ለመመረዝ አይደለም ብለህም ንገራት ።"

ሹምባሽ እስጢፋኖስ አለቃው ያለውን ለድንቄ ተረጐመላት ።

"የፋሽስት ሰላምታ አስጣጥም አሳያት ፣ ሹምባሽ እስጢፋኖስ" አለው ባርዚኒ ።

"ሹምባሽ እስጢፋኖስ ቀኝ እጁን ወደ ላይ እን ሥቶ የሰላምታ አሰጣጡን አሳያትና የፋሽስትን ሥርዓት መቀበሏንና ለፋሽስት መንግሥት መንበርከኳንም ለማ ረጋገጥ ያህል የፋሽስት ሰላምታ እንድትሰጥ አዘዛት ። ድንቁ አመነታች ። "ሰላምታ ስጪ" አላት ሹምባሽ እስጢፋኖስ በድጋሚ ። እሷ ግን ልቧ አልቆርጥ ብሏት አሁንም አመነታች ። ሹምባሽ እስጢፋኖስ ቆጣ ብሎ ሰላምታ እንድትሰጥ ለሦስተኛ ጊዜ ካዘዛት በኋላ ድንቁ ፈርታ እጇዋን እንስታ ሰላምታ ሰጠች ።"

ምድረ ግቢውን ሲፈትሹ የነበሩት ሦስት ጥቁር ወታደሮች በዚህ ጊዜ ተመልሰው ወደ ቤቱ ገቡና ምንም እንዳላገኙ ለአዘዛቸው ነገሩት ። ፍተሻው በዚህ አብቅቶ ባርዚኒና አራቱ ፈታሾች የባሻ ቅጣውን ቤት ለቅቀው ወጥተው ለጥቆ ወደ ነበረው ቤት አመሩ ። ድንቁ ተከ ትላቸው ደጅ ወጣች ። ለትንሽ ጊዜ በዓይኗ ስትከተ ላቸው ቆየችና እነሱ የጐረቤቷን ቤት ለመፈተሽ ሲገቡ ከዓለሟ ነጥቃ የወሰደችውን ከረሜላ ባለ ኃይሏ ወደ አጥር ውጭ ወረወረችው ። "መርዝ አለመሆኑን ግን አጣው !" አለች እራሷ ለራሷ ፤ "ከመርዝ አለመሻሉንስ ግን አጣው ! የሰንቱን ኢትዮጵያዊ ሕይወት አጥፍ ተው ፤ ባሻን ሳይቀር አደምተው ፣ ዕርቅ ፣ ሳይደረግ ጉማ ሳይከፍሉ ፣ አገር ሳይለቁ ፣ ሰብአዊ ርኅራኄ አለን ፣ አበሻንም እናሠለጥናለን በማለት ማነን ሲደልሉ . . .!" ስትል አሰበችና ዕቃዎችዋን መልሳ ለማሰር ወደቤቷ ተመልሳ ገባች ።



# ፲

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አንድም መኖሪያ ቤት ከፍተሻ አላመለጠም ።

ፈታሾቹ ሁሉ እንደነ ባርዚኒ ልል አልነበሩም ። በፍተሻውም ሆነ በሚቀጡት ቅጣት በጣም ጥብቅ ነበሩ። መሣሪያ ፣ ጥይትና የተዘረፈ ዕቃ ሲያገኙ ባለቤቱን በቤ ተሰቡ ፊት በጥይት ደብድበው ይገድሉት ነበር ። በዚህ ሁኔታ ከተገደሉት መሐከል አንዱ የአባቱ አባት ፣ ቀኛ ዝማች ሺፈራው ነበሩ ።

ቀኛዝማች ሺፈራው አምስት ጠበንጃዎችና በር ከት ያሉ ጥይቶች ነበሯቸው ። እነዚህን ሁሉ ከቤታ ቸው በስተጓሮ በኩል ጉድጓድ አስቆፍረው ቀብረዋ ቸው ነበር ። ፈታሾቹ መሣሪያ እንዳላቸው እንዲናዘዙና እንዲያስረክቡ በጠየቋቸው ጊዜ ምንም መሣሪያ የለ ኝም ሲሉ ካዱ ። ከአሽከሮቻቸው አንዱ በጉን ሄዶ ተን ፍሶ ኖሮ ፋሺስቶቹ ቦታውን አስቆፍረው መሣሪያዎቹ እንዲወጡ ካደረጉ በኋላ ቀኛዝማች ሺፈራውን የፊጥኝ አስረው በጥይት ደብድበው ገደሏቸው ። ቀኛዝማች ሺፈራው በከተማው ውስጥ በጣም የታወቁ ሰው ስለ ነበሩ በሳቸው መገደል ሰው ሁሉ ተረበሸ ። ቸሩም በበ ኩሉ ወሬውን ሲሰማ ተርበተበተ ። የታጠቀውን ሽጉጥ በእጁ እየዳሰሰ ፣ ዓይኑን ወደ ሙሉ መልሶ ፣ "ወዴት ላድ ርገው ? ወዴት ላድርሰው ይህንን ሽጉጥ ?" ሲል አማ ከራት ።

"ለኔ ስጠኝ ። ጋን ውስጥ ጨምሬው በላዩ ላይ ጩፍ ብጠቀጥቅበት አያገኙትም" አለችው ሙሉ ።

"ያገኙታል...እኒህ አረመኔዎች !"

"እንግዲያው" አለች ዓይኖቿን ወደ ቤቱ ጣሪ ሰቅላ ፣ "ያ ቀዳዳ ይታይሃል? እዚያ ውስጥ ብትወረውረው አያገኙትም ።"

"የአረመኔ እጃቸውን የማያሳርፉበት ቦታ አለ ብለሽ፣ ሙሉ!" አለና ፣ "ወይ ደሞ...ለምን እዚሁ እኖረዋለሁ ውኃ ጉድጓድ ውስጥ ብጨምረውስ? እነሱ ከሄዱ በኋላ ዘዴ ፈልጌ ላወጣው እችላለሁ...ብቻ ውኃ ሲነካው ይዝግ ይሆናል ። ምን አባቱ! የት ባደርገው ይሻል ይመስልሻል ፣ ሙሉ ?"

"ኮርኒሱ ቀዳዳ ውስጥ ብትወረውረው አያገኙትም"

"ያገኙታል ስልሽ! የሚደብቅልኝ ሰው ባገኝ... ብቻ ማን አለ!"

ቸሩና ሙሉ እንዲሁ ሲመካከሩ ሳሉ ፈታኞቹ በድንገት ከቸች አሉ ። ባርዚኒና አራቱ ጥቁር ወታደሮች ነበሩ ።

ቸሩና ሙሉ የመንፈስ ጭንቀት እንደ ያዛቸው በፊታቸው ይነበብ ነበር ። ሆኖም ግን ባርዚኒ ይኸንን አላስተዋለም ። ዓይኖቹ ቀድመው ያረፉት በሙሉ ውበት ላይ ነበር ። ውብ ሴት አይቶ እንደማያውቅ ሁሉ ከራስ ጸጉሯ እስከ እግር ጥፍሯ ያስተውላት ጀመር ፣ የሐር ጥቅል የመሰለ ጸጉርዋ...የፈካ ገጽታዋ...ጉላ ጉላ ብለው የሚንከራተቱ ዓይኖቿ...ለምለም ከናፍሯ...ሸጋ ቁመናዋ...

አራቱ ጥቁር ወታደሮች በባርዚኒ መነሁለል ሲገረሙ፡ ቆዩና ፣ "ፍተሻውን እንጀምር ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ?" ሲል ጠየቀው ሹምባሽ እስጢፋኖስ ፣ ሲፈራ ሲቸር ።

"ጀምሩ!" አለው ባርዚኒ ።



ሹምባሽ እስጢፋኖስ ዓይኖቹን ወደ ቸሩ መልሶ ጥያቄ ይደረድርለት ገባ ።

"መሣሪያ አለህ ?"

"እ... ?

"መሣሪያ አለህ ወይንስ የለህም ?"

"ምን ዓይነት መሣሪያ ?"

"ማንኛውም ዓይነት...ለምሳሌ ቦምብ ።"

"ኧረ የለኝም !"

"ከባድ ጠበንጃ !..."

"የለኝም ።"

"ምንም የለህም ?"

"ቦምብም ሆነ ከባድ መሣሪያ የለኝም ።"

"ቀላል መሣርያስ ?"

"የለኝም ።"

"ሽጉጥ እንኳ ?"

"አይ ! ሽጉጥስ አለኝ...አንድ አነስተኛ ሽጉጥ ።"

"ወዴት አለ ?"

ቸሩ ሽጉጡን ከአፎቱ አውጥቶ ፣ ይኸኮ መሣሪያ አይባልም" አለው ።

"ታዲያ ምን ይባላል ?"

"ሽጉጥ ።"

ሹምባሽ እስጢፋኖስ ሳይወድ ሣቅ ብሎ ፣ መልሶም ፊቱን አክብዶ ፣ "እስካሁን ድረስ ለምን አላስረከብከም ?" ሲል ጠየቀው ።

"መሣሪያ ሲባል ከባድ ጠበንጃና ቦምብ የመሳሰለውን እንጂ ሽጉጥን የሚጨምር አልመሰለኝም" አለው

ቸሩ ። "በዚያ ላይ ራሴን ከሌሊት ጅብና ከዘራፊዎች ልጠብቅበት እንጂ ሰውን ላጠቃበት አስቤ አይደለም የገዛሁት ።"

ቸሩና ሹምባሽ እስጢፋኖስ እንዲሁ ቃል ይለዋወጡ በነበረበት ጊዜ የባርዚኒ ዓይኖች አሁንም በሙሉ ላይ ነበሩ ። ከአገሩ ወጥቶ ከሰባት ወራት በላይ በጦር ሜዳ በቆየበት ጊዜ ሐሳቡን የምትከፍልለት ፥ የምታዝናናው ፥ የምታስደስተው ሴት አላጋጠመውም ነበር ። በጣሊያን አገር በየከተማው መንገድ ጊዜአዊ ፍቅር ለመቸርቸር የሚቆሙ ሴቶች ወታደሮቹን ተከትለው የመጡ ቢሆንም ፥ ባርዚኒ ለእነዚህ ዓይነቶቹ ፍላጎት አልነበረውም ። የሱ ፍላጎት ሌላ !

የተራበ ጅብ ይመስል ሙሉን ሲጕርሳት እንደ ጕመጀ ሁሉ አተኩሮ ሲመለከታት ቆየና ዓይኑን በግድ ነቅሎ ወደ ሹምባሽ እስጢፋኖስ አዙሮ ፥ "መሣሪያውን ሳያስረክብ ለምን ቀረ ?" ሲል ጠየቀው ።

ባርዚኒ አላወቀም እንጂ ቸሩ ጣሊያንኛ ይሰማ ነበር ። ይናገርም ነበር ።

"እንደዚህ ያለውን ትንንሽ መሣሪያ ትቆጣጠራላችሁ ብዬ ስላላሰብኩ ነው ሳላስረክብ የቀረሁት" አለው ቸሩ በጣሊያንኛ ቋንቋ ።

"ኢ... ? ጣሊያንኛ ትችላለህ ?"

"አዎን ፥ በመጠኑም ቢሆን እችላለሁ" አለው ቸሩ ።

"የተማርክ ሰው ነሃ !" አለና ዓይኑን እንደ ገና ወደ ሙሉ አዙሮ ፥ "አንቺስ ? ጣሊያንኛ ትናገሪያለሽ?" ሲል ጠየቃት ባርዚኒ ።



"እሷ ጣሊያንኛ አትችልም" አለው ቸሩ ።

"አንተ ጣሊያንኛ የተማርከው የት ነው ? ሥራህስ ምንድነው ?"

"ትምህርት ቤት በነበርኩበት ዘመን ነው ጣሊያንኛ የተማርኩት ። በሙያም ሠዓሊ ነኝ ።"

"ሠዓሊ ? ሥዕሎችህን ልታሳየኝ ትችላለህ ?"

"በደስታ እንጂ !" አለው ቸሩ ቀለል ብሎት ።

የቸሩ መኖሪያ ቤት እንደ ባሻ ትጣው ቤት ክብ ጎጆ አልነበረም ። ግድግዳው አራት ማዕዘን ፥ ጣራው ቆርቆሮ ፥ ወለሉ ሳንቃ የሆነ ዘመናዊ ቤት ነበር ። ከውጭ በኖራ ከውስጥ በተለያዩ ቀለማት ያጌጠ ነበር ። የእንግዳ መቀበያው ክፍል ሰፋ ያለ ሆኖ ክብ ጠረጴዛና ምቹ ወንበሮች ነበሩበት ። በወለሉም ላይ መለስተኛ ምንጣፍ ተነጥፎበት ነበር ። ከሳሎኑ አልፎ የመተላለፊያ በረንዳ ፥ ከበረንዳው በስተግራ አንድ መኝታ ቤት ፥ ከበስተቀኙ የቸሩ እስቱድዮ ነበሩበት ። አራቱ ጥቁር ወታደሮች ሳሎኑን ፈትሸው በረንዳውን አልፈው ከመኝታ ክፍል ሲገቡ ሙሉ ተከተለቻቸው ። ቸሩ ባርዚኒን አስከትሎ ወደ እስቱድዮው አመራ ።

እስቱድዮው ውስጥ በአራቱም ግድግዳዎች የተንጠለጠሉና በአንድ ሰፊ ጠረጴዛ ላይ የተከማቹ በርካታ ሥዕሎች ነበሩ ። አንዳንዶቹ በባለቤቱ በሙሉ ሞዴልነት የተሣሉ ነበሩ ። ሹርባ ተሠርታ የተሣለችው ሥዕል... ጸጉሯን አጕፍራ የተሣለችው ሥዕል...ከወገቧ በላይ ራቁቷን ሆና የተሣለችው ሥዕል...

አንዳንዶቹ የገጠር ትርዒቶች ነበሩ ፥ የንጋት ሰማይ... የምሽት ሰማይ... የጋሸበ የጤፍ ማሳ... የበቆሎ

እሸት ማሳ...ነጫጭ ወፎች የሠፈሩበት የረጋ ኩሬ ሥዕል... እንስራ የከበዳት የገጠር ሴት ሥዕል...

ባርዚኒ እነዚህን እየት እየት አድርጎ ጠቅላላ መን ፈሱን ሙሉ ከወገቧ በላይ ራቁቷን ሁና በተሣለችው ሥዕል ላይ ጣለ ። በልብስ ተሸፍና የሚኖር እውነተኛ ውበቷ ከዚያ ላይ ነበር ። "ይህንን ልግዛህ" አለው፣ ባርዚኒ ።

"የሚሸጥ አይደለም" አለው ቸሩ ።

"ለምን ?" ሲል ጠየቀው ባርዚኒ ።

"ባለቤቴን እንደዚህ እንደምታያት ሆና በሳልኳት ጊዜ ሥዕሉን እንዳልሸጠው ቃል አስገብታኛለች ። እኔም ብሆን ልሸጠው ፈቃደኛ አይደለሁም ።"

"አርቲስት ሆነህ ሥዕሎችህን ካልሸጥህ ምን ያደ ርግልሃል ?"

"አንዳንድ የማይሸጡ ሥዕሎች አሉ ፣ ካፒታኖ ባርዚኒ...ለሠዓሊው በጣም ግላዊ የሆኑ ሥዕሎች ።"

"ጥሩ ዋጋ ልስጥህ...ሽጥልኝ" አለው ባርዚኒ ። ቸሩ ግን አልተስማማለትም ።

ባርዚኒ ቅር ተሰኝቶ ፊቱን ሲያዞር ዓይኖቹ በሌላ ሥዕል ላይ ዐረፉ ። በቅጽበት መላ ገጽታው ልውጥውጥ አለ ። ቸሩም የባርዚኒን ቁጣ አይቶ ተደናገጠ ። ባርዚኒን ወደ እስቱድዮው ባስገባው ጊዜ የምኒልክ ሥዕል በዚያ መኖሩን አላስታወሰም ነበር ። ለዘመቻው ገንዘብ ለመ ሰብሰብ የሥዕል ኤግዚቢሽን ካሳየ በኋላ የምኒልክን ሥዕል አልሸጠውም ነበር ። በሐውልቱ ላይ እስ ያለ ውን ቅንብርና ጥበባዊ ሚዛን በሥዕሉም ላይ አንጸባርቆት ስለ ነበረ ሥዕሉን በጣም ይወደው ነበር ።



"ይህንን ሥዕል በቤትህ በማኖርህ ብቻ ላስረሽ ንህ በተቻለኝ!" አለው ባርዚኒ ፣ ጆሮና አፍንጫው እንደ ደም ቀልተው ፣ "ነገር ግን ጨካኝ ሰው ስላልሆንኩ አላደርገውም" ብሎ ሥዕሉን ከነበረበት አንሥቶ ፣ የሥ ዕሉን ፍሬም ሰባብሮ ፣ ሰንጢውን ከኪሱ አውጥቶ ሥዕሉ የተሣለበትን ሸራ ሸረካክቶ ጣለው ። ይህንን በሚያደ ርግበት ጊዜ ቸሩ ግንባሩን ቋጥሮ ፊቱን ኮሶ አስመስሎ ያስተውለው ነበር ። የሰንጢውም ስለት የገዛ አካለ ሥጋውን ቆርጦ የገባ መሰለው እንጂ እውነትስ ሥዕሉን የሸረካከተው አልመሰል አለው ።

የሚገዘግዝ... የሚሠቀጥጥ... የሚነዝር... ውስጣዊ ሥቃይ ተሰማው ። "ለምን ሸረካከትህ ጣልከው ?" ብሎ ሊጠይቀው ግን በቂ ድፍረት አላገኘም ።

ባርዚኒ ወታደሮቹን ጠርቶ ቸሩን ይዘው እንዲሄዱ አዘዛቸው ። ሙሉ ጣሊያንኛ ባትሰማም ባርዚኒ ምን እንዳለ ከገጽታው ልታነብ ስለቻለች ፣ "ምን አደረግን? ምን አጠፋን ? ባሌን አትውሰዱብኝ" ብላ ትማጸናቸው ጀመር ። ምን እንዳለች ሹምባሽ እስጢፋኖስ ለባርዚኒ ተረጐመለት ።

"ባልሽ የጣሊያን ጠላት ነው ብለህ ንገራት ሹም ባሽ እስጢፋኖስ" አለው ባርዚኒ ፣ "ከምርመራ ጣቢያ ሄዶ ቃሉን እንዲሰጥ ይደረጋል ። እሷ ግን ሚስቱ ብት ሆንም አንዳችም ጉዳት እንደማይደርስባት ንገራት ። የድል አድራጊው የዱቼ መንግሥት ይቅርታ አድራጊ መሆኑንም ጭምር ግለጽላት" አለው ። ሹምባሽ እስ ጢፋኖስ ቃሉን ተረጐመላትና ቸሩን እየነዱ ከቤቱ ወጥ ተው ሄዱ ።